# ብሄራዊ የአምራች ዘርፍ ተኪ ምርት ስትራቴጂ

## የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ህዳር 2016

# ማውጫ


**አጠቃላይ ዳራ ........ 4**

**1 ክፍል አንድ ........ 8**

1.1መግቢያ እና ዳራ ........ 8

1.2ዓላማ እና ወሰን ........ 9

**2 ክፍል ሁለት ........ 10**

2.1የኢትዮጵያ ተኪ ምርት ፖሊሲዎች ........ 10

2.1.1 **አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ** ........ 10

2.1.2 **ድህረ 1991** ........ 10

2.2የኢትዮጵያ የገቢ ንግድ አፈጻጸም ........ 13

2.3የተኪ ምርት ስትራቴጂ አስፈላጊነት ........ 17

2.4የተኪ ምርት ስትራቴጅ ገለጻ እና ቁልፍ መርሆች ........ 19

**3 ክፍል ሶስት ........ 22**

3.1ተወዳዳሪ ንዑስ ዘርፍ እና የምርት ልየታ ........ 22

3.1.1 **የስትራቴጂው ማዕቀፍ** ........ 22

3.2የአምራች ዘርፍ ገቢና ምርት ነባራዊ ሁኔታ ........ 23

3.2.1 **የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ** ........ 23

3.2.2 **የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ** ........ 25

3.2.3 **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ** ........ 27

3.2.4 **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ** ........ 29

3.2.5 **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ** ........ 31

3.2.6 **ስትራቴጂያዊ ምርቶች አመራረጥ እና ዘርዝር** ........ 34

**4 ክፍል አራት ........ 36**

4.1የንዑስ ዘርፍ ተግዳሮቶች ........ 36

4.1.1 **የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ** ........ 36

4.1.2 **የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ** ........ 38

4.1.3 **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ** ........ 39

4.1.4 **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ** ........ 40

4.1.5 **የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ** ........ 42

4.2ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ዳሰሳ ........ 44

4.2.1 **አርጀንቲና** ........ 44

4.2.2 **ጃፓን** ........ 44

4.2.3 **ሩስያ** ........ 45

4.2.4 **ደቡብ ኮሪያ** ........ 46

4.2.5 **ቬቴትናም** ........ 46

4.2.6 **ጀርመን** ........ 47

4.2.7 **አሜሪካ** ........ 47

4.2.8 **ኢትዮጵያ የምትወስዳቸው ቁልፍ ትምህርቶች** ........ 48

**5 ክፍል አምስት ........ 51**

5.1የተኪ ምርት ስትራቴጂክ የመፍትሄ ሃሳቦች ........ 51

5.2የተለዩ ስትራቴጂክ መፍትሄዎችን ትግበራ ስልቶች ........ 51

5.3ስትራቴጂውን ከአዲሱ የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ እና የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ጋር መጣጣም ........ 53

5.4የተኪ ምርት ስትራቴጂ ማስተባበሪያ እና የክትትልና ድጋፍ ማዕቀፍ ........ 54

5.5የበጀት ማሰባሰብ መስፈርት ........ 55

**6 አባሪ ........ 58**

## መቅድም

የሀገር ውስጥ አቅምን በተገቢው መንገድ በመረዳትና በመገንዘብ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን እና በገቢ ምርት ላይ የሚታየውን ጥገኝነት ለመቀነስ እና ለአምስት አምራች ዘርፎች የሀገር ውስጥ ምርት አቅምን ለማሳደግ የሚያስችል አጠቃላይ ብሄራዊ የአምራች ዘርፍ ተኪ ምርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል። ይህ ስትራቴጂ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ፣ የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት እና የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሻሻልና ለማጠናከር ለምናደርገው ጥረት ጉልህ ምዕራፍ ይኖረዋል።

ከውጭ በሚገቡ እቃዎች ላይ ከመጠን በላይ ጥገኛ ከመሆን ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ስትራቴጅውን መንደፍ እና ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ሂደት ነው። የአምራች ዘርፉን በመደገፍ ዕምቅ ሀብታችንን፣ ውስጣዊ አሰራሮችን እና አቅማችንን በመጠቀም የሀገር ውስጥ ፍላጎቶችን ለማሟላት እና በውጪ ምንጮች ላይ ያለንን ጥገኝነት ለመቀነስ ዓላማ እናደርጋለን፣ ተያይዞም የወጪ ንግድ አፈፃፀማችንን ሊያሳድግና ሊያበረታታ የሚችል ነው ብለን እናምናለን።

ይህ ስትራቴጂ ዋና ዋና የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎችን ማለትም የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የምግብና መጠጥ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግንባታ ግብአቶችን፣ እና የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ ምርቶችን በመለየት አጠቃላይ ማዕቀፍ ይዘረዝራል። እንደ መሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ ኢንቨስትመንት እና ምቹ የንግድ አካባቢን ማሳደግን በመሳሰሉ ቁልፍ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጓል። ለሀገር ውስጥ ተወዳዳሪ ምርት አምራቾች የታለመ የመፍትሄ አቅጣጫ፣ የአገር ውስጥ ምርትን የሚያበረታታ፣ ፈጠራን እና ለአምራች ኢንዱስትሪው እሴት መጨመርን የሚያበረታታ ሥነ-ምህዳር ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

እንደ "ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ" ባሉ ኢኒሼቲቮችና ትግበራዎች ቀጣይነት ያለው ዘርፈ ብዙ ዓላማዎችን ለማሳካት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል። ይህ ደግሞ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት በማስገባት ኢኮኖሚያችንን ለማጠናከር ብቻ ሳይሆን የስራ እድል ለመፍጠር፣የቴክኖሎጅ ሽግግርን ለማፋጠን እና የአምራች ዘርፉን አጠቃላይ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የተዘጋጀ ንቅናቄ ፕሮጀክት ነው። ሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና የኢንዱስትሪ ተዋናዮች ለስትራቴጅው ተፈፃሚነት ጠንክረው እንዲሰሩ፣ የያዘውን ትልቅ አቅም እንዲገነዘቡ እና ወደ ተጨባጭ ተግባራት እንዲተረጉሙት አብረው እንዲሰሩ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የተኪ ምርት ስትራቴጅ ትግበራ ለሚደረገው ጉዞ ውጤታማነቱን እና የረጅም ጊዜ

ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ የተቀናጀ ጥረቶችን፣ ደፋር ውሳኔዎችን እና ተከታታይ ግምገማን ይጠይቃል። ስለሆነም በጋራ ይህንን የለውጥ ጎዳና እንድንጓዝ እና አዲስ የኢኮኖሚ መሻሻልና መነቃቃት፣ የኢንዱስትሪ እድገት እና ለኢትዮጵያ የብልጽግና ምዕራፍ እናምጣ።

በዚህ አጋጣሚ ለስትራቴጅው ዝግጅት መሳካትና ድጋፍ የቶኒ ብሊየር ኢንስቲትዩት (TBI) አማካሪ ባለሙያዎች፣ ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስድስት የምርምርና ልማት ማዕከላት የባለሙያዎች ቡድን፣ ባለድርሻ አካላትና የኢንዱስትሪ አመራሮች በሙያቸውና በግንዛቤያቸው ላበረከቱት የማይናቅ አስተዋፅዖ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

መላኩ አለበል

ሚኒስትር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## አጠቃላይ ዳራ

**የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተኪ ምርት ስትራቴጂ ሰነድ አላማ የኢትዮጵያን የአምራች ኢንዱስትሪ የሀገር ውስጥ የገበያ እድልን በመጠቀም የማምረት አቅምና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማጎልበት የተመጣጠነ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ ነው።** ባለፉት አስርት ዓመታት በአማካይ 8 ቢሊየን የአሜሪካ ዶላር የነበረው የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን ጉድለት የሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ ከፍተኛ የሚባል ጫና በመፍጠር የሀገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርትን፣ ምርታማነትን እና ፈጠራን በማቀጨጭ የኢኮኖሚ ሚዛን እንዲሁም እንደሃገር ያላትን ሉዓላዊነት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሯል። ከዚህም በመነሳት የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሙን ተከትሎ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ የአምራች ዘርፎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የፖሊሲ መሳሪያዎችን በመንደፍ፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ለማብዛት እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመቀነስ ያለመ ሁለት ገጽታ ያለው የዘርፍ ልማት ስትራቴጂን ተግባራዊ ማድረግ አስፈልጓል። ስትራቴጅው በዋናነት የምግብና መጠጥ፣ የጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብአቶች፣ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጂ ምርቶችን በመለየትና ዋና ዋና ተግዳሮቶችን በመገምገም ለአምስት ዓመታት የተዘረጋ የትግበራ ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ነው። በዚህም መሰረት ይህ ስትራቴጂ የተዘጋጀው በአገር ውስጥ የሚመረቱ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን የገበያ ድርሻ ለማሳደግ እና የውጭ ምንዛሪ እጥረቱን ለማረጋጋት ወቅታዊ የመፍትሄ አቅጣጫን በማመላከት ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ የሚያተኩር የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ (Inward Looking Industrialization Strategy) ነው።

**ስትራቴጂው ሲዘጋጅ ተወዳዳሪ የሆኑ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን ለመለየት የተለያዩ ስልቶችን ተከትሏል።** ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተወዳዳሪ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች ለመለየት ከውጪ የሚገቡትን ምርት በመጠን፣ በዋጋ እና በአገር ውስጥ ምርታማነት ለመገምገም ዝርዝር የተወዳዳሪነት መለያ መስፈርት እና መመዘኛ ተጠቅሟል። ለተወዳዳሪ ምርት ትንተና የተጠቀምናቸው መረጃዎች በጉምሩክ የተሳለጠ ምርት መግለጫና ምደባ ስርዓትን (HS-Code) እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ በኢንዱስትሪ ምርቶች ተቀባይነት ያላቸው አጠራሮችና ምደባዎች (Nomenclature) የተከተለ ሲሆኑ ይህም ተኪ ምርቶችን ከተለያዩ አገሮች የንግድ ግንኙነት አንጻር ለማየት አስችሏል። በተጨማሪም ተወዳዳሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለመለየት ከ197 አምራች ኢንዱስትሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል። የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ከኢትዮጵያ ስታትስቲክ አገልግሎት (ቀደም ሲል ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ከሚባለው) የ2019/2020 የአምራች ኢንዱስትሪ ብሄራዊ መረጃ፤ በዳልበርግ

አማካሪዎች ከተዘጋጁ የዘርፍ ተኮር ጥናቶችን እና የተለያዩ የዘርፍ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በተጨማሪም የስትራቴጂካዊ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለመለየት ዘጠኝ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ታይተዋል።

**የአሥር ዓመት የገቢ ንግድ አፈጻጸምና የአገር ውስጥ ምርታማነት ትንተናን በመጠቀም በአምስት የአምራች ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች 93 ተወዳዳሪ ተኪ ምርቶች ተለይተዋል።** ከ2011 እስከ 2021 እ.ኤ.አ የነበረውን የገቢ ዕቃዎች መረጃ፣ የሀገር ውስጥ ምርታማነት መረጃ እና የአምራቾች አቅም ላይ የተመሰረተ መረጃን በመጠቀም 11 ቅድሚያ የሚሰጣቸው የምግብ እና መጠጥ ምርቶች እስከ መካከለኛ ጊዜ ድረስ ሊተኩ የሚችሉ የተለዩ ሲሆን፤ የነዚህን ምርቶች ተወራዳሪነት የበለጠ ለመጨመር ስንዴ፤ ስኳር እና የምግብ ዘይት እንደ ዋና የስትራቴጂካዊ ምርቶች ተለይተዋል። 33 ቅድሚያ የሚሰጣቸው የጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርቶች 49% የሀገር ውስጥ ገበያ ድርሻ ያላቸው የተለዩ ሲሆን፤ ጥጥ ጨምሮ ሌሎች ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ጭራዎች የነዚህን ምርቶች ተወዳዳሪነ የበለጠ ለማፋጠን እንደ ስትራቴጂካዊ ምርቶች ተለይተዋል። በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ 66% የሀገር ውስጥ ገበያ ድርሻ ያላቸው 8 ምርቶች ተለይተዋል። በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዘርፍ 23 ምርቶች የተለዩ ሲሆን የነዚህን ምርቶች ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል ፔትሮኬሚካል እንደ አንድ ስትራቴጂካዊ ምርት ተለይቷል። ቀሪውዎቹ 18ቱ ምርቶች ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሲሆን የብረት ማዕድን፣ ኒኬል፣ መዳብ እና ታንታለም የነዚህን መርቶች ተወዳዳሪነት ለማሳደግ እንደ ስትራቴጂካዊ ምርቶች የተለዩ ሲሆን በዚህም መሰረት የግብርና ልማት እና የማዕድን ልማቱ ለአምራች እንዱስትሪዎች ዘላቂ ጥሬ ዕቃ በማምረት እና በማቅረብ የዘርፉን ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

**ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ 71 ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች በአምስት ቁልፍ ምሰሶዎች ማለትም በህግ እና በደንብ፣ በገበያ፣ በፋይናንስ፣ በመሠረተ ልማት እና በምርት ተወዳዳሪነት በሚል ተለይተዋል ።** የእነዚህ የትኩረት መስኮች አላማ ለሀገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ ምርቶችን የሚያቀርቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምቹ የማክሮ እና የንግድ ከባቢያዊ ሁኔታ ለመፍጠር ነው። የትኩረት መስኮቹ ለምሳሌ አምራች ተኮር ማበረታቻዎችን፣ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች፣ ቀጥተኛ በሆኑ የመንግስት ድጋፍችን፣ ጥንቃቄ የተሞላበት የቀረጥ ከለላ እና የትብብር የግብይት መድረኮች እና ስርዓቶች መቅረጽ በሚሉ ቁልፍ የማስፈጸሚያ መሳሪያዎች የተዋቀሩ ሲሆን፣ ይህም ዘላቂ እና በዉጭ ንግድ ላይ ብቻ ያልተመሰረ ሚዛናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ዕድገትን ለመፍጠር ይረዳል።

**ይህን ስትራቴጂ ለማስፈጽም ሁለት አይነት የሀብት ማሰባሰባሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሰዋል፤**

1. በመጀመሪያ ደረጃ ከተለዩት ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች ውስጥ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የሶስት አመት የትኩረት መስኮች ጋር የሚመሳሰሉትን በመለየት በንቅናቄው ስር ከተጠቀሰው የበጀት ድልድል ጋር በማጣጣም ሲሆን በዚህም መሰረት 18,753,904.18 የአሜሪካ ዶላር የማስፈጸሚያ በጀት እንደሚያስፈለግ ተለይቷል። ለቀሪዎቹ ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች በየደረጃው ዝርዝር የበጀት እቅድ በየአስፈጻሚ ተቋማቱ ይዘጋጃል። በተጨማሪም በንቅናቄው ውስጥ የተቋቋሙት አምስቱ ሀገር አቀፍ የክላስተር የቅንጅት መዋቅሮች የመንግስትን ድጋፍ እና ግብዓትን ለማስተባበር የሚያገለግሉ ሲሆን ስትራቴጂውንም በቅንጅት ለማስተግበር ይረዳሉ።

2. በሁለተኛ ደረጃ የስትራቴጂክ ሀብቶችን እምቅ አቅም ማሳደግ እና ከማዕድን እና ተፈጥሮ ሀብት ዘርፎች ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የእውቀት ሽግግር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ስትራቴጂው አጽንኦት ሰጥቷል። ይህንንም ለማሳካት ስልቱ ስትራቴጂካዊ የምርቶች እሴት ሰንሰለቶችን በማዘጋጀት ከመካከለኛ እስከ ረጅም ጊዜ የሚተግበሩ የትኩርት መስኮችን ያስቀምጣል፤ ይህም ወደ ላይ (vertical) እና አግድም (horizontal) ትስስሮችን ማጠናከር፤ መፍጠር እና ማቀናጀትን ያካትታል። በተጨማሪም የረዥም ጊዜ ስትራቴጂካዊ ፕሮጀክቶችን እና ኢንቨስትመንቶችን በመቀረጽ በመንግሥትና በየግሉ ዘርፍ በጋራ በመሆን የሚመራ ኢኮኖሚ እና አምራች ማኅበረሰብ ለመገንባት ያስችላል። እነዚህን ግንኙነቶች ማሰስ እና ማዳበር ውጤታማ የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ መሰረትን ሊፈጥር ይችላል።

**ወቅቱ ኢትዮጵያ ከጥሬ ዕቃ እና እሴት ካልተጨመረባቸው የኢንዱስትሪ ልማት እና የንግድ ሞዴል ወደ ከፍተኛ እሴት ጭማሪ እና የተፈጥሮ ሀብትን መሰረት ያደረገ ኢንዱስትራላይዜሽን መሸጋገር የግድ የሚላት ነው።** ይህ ለውጥ ሀገሪቱ ያላትን ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል እና እምቅ አቅሟን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንድትጠቀም ያስችላል። ትስስርን እና የእሴት ሰንሰለት እድገትን የሚያጎለብት ስትራቴጂን በመተግብር የራስን ፍላጎት በራስ ከመሸፈን ባለፈ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን መጨመር ያስችላል።

**በመጨረሻም ይህ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ተጨማሪ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ስትራቴጂ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ለአምራች ዘርፉ ተጨማሪ የገበያ ዕድሎችን በመፍጠር የዘርፉን እድገት ያፋጥናል።** በወጪ ንግድ አፈጻጸም ላይ የተመዘገበው ውስን ዕድገት መነሻው ዝቅተኛ አቅም አጠቃቀም፣ ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ከፍተኛ ጥገኛ መሆን እና በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ ገበያ ተደራሽነት ላይ ባሉ ተግዳሮቶች የተነሳ ነው። ይህ ስትራቴጂ የሀገር ውስጥ አምራቾችን የማምርት

አቅም በማሳደግ ገበያውን በማያዛቡ መርሆዎች ላይ በመመስረት የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን በማነቃቃት እና በማልማት እንዲሁም በመጠበቅ የዘርፉን ተወዳዳሪነት ማሻሻል እና ፈጠራን ማሳደግ ነው። በዚህም መሰረት በዋናነት የዚህ ስትራቴጂ ግብ የመንግስት ድጋፎችን በማጠናከር የሀገር ውስጥ ገበያ ተኮር ፖሊሲዎች እና የሀገር በቀል የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት በማድረግ የላቀ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እና ለዘርፉ የተፋጠነ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ዕድገት ማምጣት ነው። ስልሆነም የኢትዮጵያን አምራች ኢንዱስትሪ ለመደገፍ እና ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ ቅንጅታው አሰራር፣ አመራር እና የማያወላውል ቁርጠኝነት ከሁሉም አስፈጻሚ አካላት የሚጠበቅ ነው።

# 1 ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ እና ዳራ

**የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን የሚተገበር የ18ኛው ክፍለ-ዘመን የኢንዱስትሪያላይዜሽን ጽንሰ-ሃሳብ ነው።** የተኪ ምርት ስትራቴጂ የፖሊሲ መሳሪያዎችን እና ስልታዊ የልማት መንገዶችን ይተገብራል። ሀገራት ለሀገር ወስጥ ገቢያ የሚያቀርቡ አምራቾችን በታለመ ድጎማ ለመደገፍ እና የገበያ ድርሻቸውን ለመጠበቅ የስትራቴጂና የፖሊሲ ድጋፍ የሚሰጡበት ስልት ነው። ለምሳሌ፣ በዩናይትድ ስቴትስ በትራምፕ አስተዳደር የአሜሪካን የምርት እና የስራ ፈጠራ እድልን ለማስፋት በመኪና፣ በሴሚኮንዳክተሮች እና በሌሎች የተመረጡ ዘርፎች ላይ "የአምራች ኢንዱስትሪ ስራ ፈጠራ" በሚል ወይም (Re-shore and create manufacturing jobs) መርህ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል። ስልሆነም ተኪ ምርት ስትራቴጂ መንግስታት ፋይናንስን ጨምሮ በጊዜ የተገደበ የአፈፃፀም መለኪያዎችን የተቀናጁ አሰራሮችን ነድፈው የሚተገብሩበት የልማት ስልት ነው። በሃገራችን የተኪ ምርት ስትራቴጂ አተገባበር በተለያዩ የኢኮኖሚ ሥርዓቶች የተለያዩ የፖሊሲ መሳሪያዎችን በመጠቀም በተለያዩ ዘርፎች ሲተገበር ቢቆም በአሁኑ ጊዜ ላይ የተሻለ እምርታ ለማምጣት፤ ትኩረት ለመለየት፤ ከሃገራዊ እና ከአለም አቀፋዊ ኢኮኖሚያዊ ነበራዊ ሁኔታዎች ጋር ለማነበብ እና ሀገራዊ እቅዶችን ለማሳካት በብሄራዊ ደረጃ ይህን ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈልጓል። ከ1930-1974 በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በግል የሚመራ ገበያን ያማከለ የኢኮኖሚ ፖሊሲን በመከተል የተኪ ምርት ስትራቴጂው የሰው ኃይል ተኮር ኢንዱስትሪዎችን ማስተዋወቅ ላይ ያነጣጠረ ነበር። ንጉሱን የተካው ስርአት የሀገር ውስጥ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት በቀረጥ ስርዓት በመደገፍ በመንግስት የሚመራ ኢንቨስትመንቶችን በስትራቴጂክ ዘርፎች በማስፋት ጉልበትን በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ ትኩረቱን ባደረገ እና የኮታ ገደቦችን በመጣል የነበረውን የኢኮኖሚ መርህ ላማሳካት ታልሞ የተዘጋጀ እና የተተገበረ ነበር።

**የዚህ ሰነድ ዋና ዓላማ ለአምስት የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች የተኪ ምርት ስትራቴጂ ማዘጋጀት ነው።** ይህ ሰነድ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በሌሎች ተቋማት ለወደፊት ተወዳዳሪ የሚሆኑ ምርቶችን ለመለየት እና በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ መተግበር የሚገባቸው የትኩረት መስኮች፤ የተሰራዉን ለመገምገም እና የወደፊቱን ለማሻሻል የሚዉል መዋቅር (framework) የያዘ ነው፤ ሀገሪቷ ለምታቀደውም የንግድና የውድድር ፖሊሲዎችም ለግብአትነትም የሚዉል ነው። ሰነዱ በዋናነት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚቀጥሉት አመታት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን በተመረጡ ምርቶች ለመተካት የሚወሰደውን ስልታዊ አቅጣጫ ይገልጻል። ይህንንም ተከትሎ ለሌሎች ዘርፎች እና የአምራች

ኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎች ተመሳሳይ ስልቶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፣ ለዚህም በቀጣይ ዝርዝር የዕቅድ ትግበራ ሰነዶችን ማዘጋጀትን ይጠይቃል፡፡

## 1.2 ዓላማ እና ወሰን

**በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ ሶስት ዋና አላማዎች ተካተዋል፡-**

I. የመጀመሪያው አላማ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪያላይዜሽን አስፈላጊነቱን በመተንተን የተኪ ምርት ስትራቴጂ ምንነት እና ዋና ዋና መርሆችን ማስቀመጥ ነው፡፡

II. ሁለተኛው አላማ ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በጨርቃጨርቅና በአልባሳት፣ በቆዳና በቆዳ ውጤቶች፣ በኬሚካልና በኮንስትራክሽን ግብአቶች፣ በብረታ ብረትና በኢንጂነሪንግ እና በቴክኖሎጂ ዘርፎች ለመየት ሲሆን ይህም የሀገር ውስጥ አቅምን ለማሳደግ ኢኮኖሚው ከዓለም አቀፍ ገበያ መለዋወጥ ለመጠበቅ እና ከውጭ የኢኮኖሚ እና የገበያ ቀውስ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ያስችላል፡፡

III. ሶስተኛው አላማ በማደግ ላይ ያሉ ተወዳዳሪ ምርቶችን የሚያመርቱ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንተርፕራይዞችን በመለየት፤ የተወዳዳሪነት ተግዳሮቶቻቸውን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሄ ሃሳቦችን በመንደፍ የተለየ የከለላ እና የድጋፍ ማእቅፎችን መለየት እና ማዘጋጀት ነው፡፡ ይህም የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን እድገት በማጎልበት በጠባብ የወጪ ንግድ ላይ ጥገኛ ከሆነውን የሃገራችን ኢኮኖሚ ወደ ብዝሃ የኢኮኖሚ ስብጥር የሚውስድ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመቀነስ የኢዮጵያን አሉታዊ የንግድ ሚዛንን ወደ አዎንታዊ የንግድ ሚዛን መመለስ ነው፡፡

# 2 ክፍል ሁለት

## 2.1 የኢትዮጵያ ተኪ ምርት ፖሊሲዎች

### 2.1.1 አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ

**እ.ኤ.አ. ከ1950ዎቹ እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያ ተከታታይ ኢንደስትሪላይዜሽን ፖሊሲዎች የነበራት ቢሆንም በመንግስት ባለቤትነት እና ቁጥጥር በማድረግ ላይ ያተኮረ ኢንዱስትሪ በመሆኑ አምራች ዘርፉ የዋዠቀ ውጤት ሲያስመዘግብ ቆይቷል።** ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ግልፅ የተኪ ምርቶች ስትራቴጅ ባይኖራትም የሃገር ዉስጥ ገበያን በመደገፍ የዉጭ አቅርቦትን እንዲቀንስ በማድረግ፣ የካፒታል ዕቃዎችንና ግብዓቶችን ወደሃገር ዉስጥ በሚገቡበት ጊዜ ማበረታቻ በማድረግ፣ በመንገድ ዝርጋታ፣በሃይል አቅርቦትና ዉሃ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ኢንቨስት በማድረግ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ ዉስጥ የተኪ ምርቶች ማበረታቻ ቁልፍ መገለጫዎች ይገኙበታል።

### 2.1.2 ድህረ 1991

**ከ1991-2018 በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግስት ሚና ላይ አጠቃላይ ማሻሻያ በማድረግ፣ለግሉ ዘርፍ ትኩረት በመስጠትና ለአምራች ዘርፉ ተገቢ ድጋፍ በመደረጉ የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ዕድገት በነፃነት መንቀሳቀስ የጀመረበትን ጊዜ ያሳያል።** በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የፋብሪካ ምርት በከፍተኛ ደረጃ ያደገው በዋናነት በመንግስት ኢንቨስትመንት ሲሆን፣ የባንክ ዘርፍንና ኢንዱስትሪዎችን ነፃ ማድረግ፣ በመንግሥት የሚመራ የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅዶችን እና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ፣ በግል ዘርፍ የሚመራ የወጪ ንግድ አቅጣጫ መቀየስ የአምራች ዘርፉን ድርሻን ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ድርሻ ማሳደግ ከ1991ዓ.ም. በኋላ የተወሰዱ ዋና ዋና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ነበሩ። ከእነዚህ የተወሰኑ ነፃ የሆኑ የህዝብ ድርጅቶች መካከል የምግብ ማቀነባበሪያና ጨርቃጨርቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ለአገር ውስጥና ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ማድረግ ይገኙበታል። ለነዚህ የፖሊሲ አቅጣጫዎች መዉጣት እንደምክንያት የሚጠቀሰዉ የመንግስት የቀድሞ የኢንዳስትሪ ዕድገት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች የማስቀጠል እና የመከተል ብቃቱ ዝቅተኛ መሆኑ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት ገዳቢ የነበረዉ የተኪ ምርቶች ኢንዳስትሪ ልማት ስትራቴጂ በደጋፊና አበረታች የተኪ ምርቶች ኢንዳስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሊተካ ችሏል፣ ይህም ቅድሚያ የሀገር ዉስጥ ዕሴት መጨመርን እና ተወዳዳሪነትን መሰረት በማድረግ የቀረጥ ከለላ እቅዶችን ያካተተ እንዲሆን ተደርጓል።

**ብሄራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመደረጉ በአምራች ዘርፉ ላይ ተጨባጭ ለዉጥ አምጥቷል።** በተጨማሪም ለአምራች ዘርፍ የታክስ ክለሳ እና የባንክ ዘርፉን ነፃ በማድረግ የግል ባንኮችን ጭምር በኢኮኖሚው ውስጥ በማስተዋወቅ ብድር ፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማድረግ በአገር ውስጥ ምርትን

ለመተካት የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ በማቀላጠፍ በገቢ ምርት ላይ ያላትን ጥገኝነት መቀነስ አስችሏል።

**የ1994ቱ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ "የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ" በመባል የሚታወቀው ሲሆን፣ ገቢ ምርትን የመተካት ሂደት የሀገሪቱ የአምራች ዘርፍ ልማት ቁልፍ አካል መሆኑን አፅንዖት የሰጠ ስትራቴጅ ነው።** ስትራቴጂው ቀደም ሲል ከዉጪ ወደ ሀገር ውስጥ ይገቡ የነበሩ በሀገር ውስጥ የተመረቱ ምርቶችን በማስተዋወቅ ሀገሪቱ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላትን ጥገኛ ለመቀነስ እና የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ያለመ ነው። ይህንን ግብ ለማሳካት ስትራቴጂው ጉምሩክ ቀረጥ ላይ ማስተካከያ ማድረግን ጨምሮ በርካታ እርምጃዎችን ይዟል። ከፍ ያለ ቀረጥ እንዲጣልባቸዉ ከተጠቀሱ የተወሰኑ ምርቶች መካከል ከዉጭ የሚገቡ እንደ ቡና፣ ሻይ እና ቅመማ ቅመም እንዲሁም እንደ የምግብ ዘይትና ስኳር ያሉ የግብርና ምርቶች፣ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳት፣ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ጫማዎች፣ ቦርሳዎች እና ቀበቶዎች እንዲሁም ለማቀነባበር ጥሬ ቆዳ; መድኃኒት፣ ማሽነሪዎች፣ ኤሌክትሮኒክስ እና አውቶሞቢሎች; የኬሚካሎች እና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ከፍተኛ ቀረጥ ከተጣለባቸዉ ምርቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

**በገቢ ምርቶች ላይ የሚጣለዉ የጉምሩክ ቀረጥ በየጊዜዉ ተቃያያሪ በመሆኑ በእያንዳንዱ ምርት ላይ በተለያዩ ጊዚያት የተጣለዉን የቀረጥ ምጣኔ በዝርዝር ለመግለፅ አስቸጋሪ ነዉ።** መንግስት ትልቅ የሆነ የቀረጥ መዋቅር ዘርግቷል፣ይህም ዓላማ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ለመጠበቅ እና የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ ያለመ ነው። የቀረጥ አወቃቀሩ ለተለያዩ የምርት አይነቶች የተለያየ የቀረጥ ምጣኔዎችን ያካተተ ሲሆን በቅንጦት እቃዎች ላይ እና በአካባቢ ወይም በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ በሚችሉ እቃዎች ላይ ከፍ ያለ ቀረጥ የሚጥል ነዉ። ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ የጉምሩክ ታሪፍ ምጣኔን ለአገር ውስጥ አምራቾች እንደ ከለላነት መጠቀሟን ቀጥላለች። ለአብነት ያህል የሀገሪቱ የ2020/2021 በጀት አመት የታሪፍ መፅሃፍ የግብርና ምርቶች፣ የኢንዱስትሪ ግብአቶች እና የፍጆታ እቃዎችን ጨምሮ በተለያዩ ምርቶች ላይ የተለያየ የታሪፍ ምጣኔ አካቷል። በተለያዩ ምርቶች ላይ የተጣለው ታሪፍ ምጣኔ በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ፍላጎቶች እና በሀገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ሊለዋወጥ የሚችል ነዉ። ነገር ግንበ በጥቅሉ የኢትዮጵያ መንግስት የታሪፍ ምጣኔን፣ የአስመጮነት ፈቃድ እና ሌሎች እርምጫዎችን በመጠቀም ለሀገር ዉስጥ አምራቾች ከለላ በመስጠት ፖሊሲዉን ጠብቆ ዘልቋል።

**በ1994ቱ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ገቢ ምርትን መተካት በተግባር ላይ መዋል ሌላኛዉ ምክንያት ልዩ የፖሊሲ ትኩርት ለሚፈልጉ የተመረጡ ዘርፎችና ማህበረሰቦች ለመስጠት ነበር።**

በአዋጅና ደንብ ለገጠር አካባቢዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና የኮንስትራክሽንና አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፎችን ጨምሮ ለተመረጡ ዘርፎች ሁሉን አቀፍ አካታች የኢኮኖሚ ልማት እና የአምራች ዘርፍ ዕድገት አላማ ያደረገ ነበር።

**ስትራቴጂው የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የኢኮኖሚ እድገት በማምጣትና የስራ እድል በመፍጠር ያለዉን ጠቀሜታ ዕዉቅና በመስጠት፣ መንግስት የታክስ ማበረታቻን ጨምሮ በአገር ውስጥ ገበያ እንዲያገኙና እንዲወዳደሩ የሚያግዙ ፖሊሲዎችንና የድጋፍ እርምጃዎችን ሲተገብር ቆይቷል።** አነስተኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ ከተተገበሩ ቁልፍ ፖሊሲዎች አንዱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲን በ1997 ዓ.ም ማቋቋም ሲሆን፤ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ የአነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ልማት የስልጠና፣ የቴክኒክ ድጋፍ፣ የብድር አቅርቦት እና ሌሎች የድጋፍ አይነቶችን የማስፋፋት ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ኤጀንሲው የንግድ ምዝገባ ሂደቶችን በማቅለል፣ የገበያ መዳረሻ መረጃዎችን በማቅረብ እና በአነስተኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችእና በትልልቅ ኩባንያዎች መካከል ያለውን ትስስር በማስተዋወቅ ለአነስተኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ትልቅ ሚና ተጫዉቷል። የ1994ቱ ስትራቴጂ እና ተከታዮቹ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂዎች መሰረት የኢንዱስተሪ ልማት ለማስፋፋት መንግስት በተኪ ምርት ፖሊሲዎች ላይ ብቻ ጥገኛ አልነበረም። ይልቁንም የውጭ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ቁልፍ በሆኑ ኢንዱስትሪዎች ማለትም በአበባ፣በሲሚንቶ ጨርቃጨርቅና ቆዳ እንዲሁም የዉጪ ገበያ ተኮር ኢንዱስትሪዎች ልማትን በማነቃቃት በኢኮኖሚ ዞን በወጪ ንግድ ማቀናበሪያ ዞኖችና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም የማበረታቻና የድጋፍ አገልግሎት በመስጠት ኢንዱስትሪዎች እንዲያድጉና በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል ያለመ ነበር።

**በአጠቃላይ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የ "ልማታዊ መንግሥት" ስትራቴጂ፣ የተኪ ምርት ፖሊሲዎች፣ ወጪ ንግድ ተኮር ኢንዱስትሪ ልማት፣ የሕዝብ ኢንቨስትመንት ግብርናና በአምራች ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር።** የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከለላ እንዲያገኙ ለማድረግ ከውጭ በሚገቡ ላይ የጉምሩክ ቀርጥ/ታሪፎችን ተግባራዊ ቢያደርግም፣ ቁልፍ ኢንዱስትሪዎችን በማልማት ላይ ያተኮረና በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ዕድገትን በማፋጠን ላይ ያተኮረ አካሄድን ተከትሏል።

**በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ትልቅ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረግ በአገር ውስጥ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ስር፣ አጠቃላይ የ10-አመት አካታች እቅድ አዘጋጅቷል።** ከዕቅዱ ቁልፍ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸዉ መካከል የአምራች ዘርፍ ሲሆን መንግስት ልማቱን ለመደገፍ ተከታታይ አላማዎችን አስቀምጧል። በአምራች ኢንደስትሪ ውስጥ ያለውን አማካይ የኢንዱስትሪ አቅም አጠቃቀም

በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ አንዱ ዋና ትኩረት ሲሆን ይህም አሁን ካለበት 50% ወደ 85% ከፍ ለማድረግ ነው። በተጨማሪም መንግስት ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ኢንቨስትመንቶች በመሳብ እና የተራቀቁ ቴክኖሎጂዎችን በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ በማተኮር አነስተኛ እና መካከለኛ የአምራች ኢንተርፕራይዞችን እድገት ከፍ ለማድረግ ያለመ ነው። በዚህም የኢንተርፕራይዞችን ቁጥር ከ2,000 ወደ 11,000 በማሳደግ በአምራች ዘርፉ 5ሚሊዮን አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር አቅዷል። ይህም በየአመቱ የሚፈጠረውን የስራ እድል ፈጠራ በከፍተኛ ደረጃ በማሳደግ በዓመት ከ175 ሺህ ወደ 850 ሺህ ገደማ የስራ እድል ዕድገት ለማሳካት ታስቧል።

**ከዉጪ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለዉን ጥገኝነት ለመቀነስ በማለም መንግስት ስትራቴጂካዊ የሆኑ ከዉጪ ገቢ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን የማስፋፋት እቅድ አውጥቷል።** በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ተወዳዳሪነት በማጎልበት የእነዚህን ምርቶች የአገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ከ30 በመቶ ወደ 60 በመቶ ለማሳደግ አቅዷል። በተጨማሪም ከዚህ ከጨመረው የሀገር ውስጥ ምርት ዉስጥ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን በማሳደግ አጠቃላይ ወደ ዉጪ የሚላኩ ምርቶችን አሁን ካለበት 3 ቢሊዮን ዶላር ወደ 18 ነጥብ 3 ቢሊየን ዶላር ለማሳደግ ያቀደ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ ወደ 9ቢለየን ገደማ ከአምራች ዘርፍ ለማግኘት ዉጥን ተይዟል። መንግስት በእነዚህ እርምጃዎች የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ እና ስትራቴጂካዊ እና አዋጭ የሆኑ የኢንዱስትሪ ምርቶችን እድገት በማምጣት ኢትዮጵያ በአለም አቀፉ የአምራችነት ምኅዳር ላይ ያላትን ቦታ ማጠናከር ይፈልጋል።

## 2.2 የኢትዮጵያ የገቢ ንግድ አፈጻጸም

**እ.ኤ.አ በ2012 የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን (የገቢና ወጪ ምርት ልዩነት) 7 ቢሊየን ዶላር የነበረው በ2014 ወደ 13 ቢሊዮን ዶላር ያደገ ሲሆን በ2020 በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች መጠን ስለቀነሰ ልዩነቱ ወደ 6.8 ቢሊዮን ዶላር ዝቅ ብሏል።** በአለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ ለረጅም ጊዜ በማገገም፣ በዩክሬንና በሩሲያ ጦርነት እና በሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ያለው ግጭት ምክንያት እ.ኤ.አ ከ2020 መጠነኛ ጭማሪ ቢኖርም በ2021 ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ዝቅተኛ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት በገቢ ምርቶች ላይ የተመሰረተው በመሆኑ ያለፉት አመታት የታየው የንግድ ሚዛን ጉድለት ዋና ምክንያት ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. በ2011 በጠቅላላ ወደ ውጭ የሚላከው ምርት 12.2% የነበረው በ2020 ወደ 6.7% ዝቅ በማለቱ በውስን የአገልግሎት ዘርፍ ወደ ውጭ የሚላኩ እና ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ምርቶች መካከል ያለው አለመመጣጠን ተባብሷል። የወጪ ንግድ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ሚና እያሽቆለቆለ በመሄዱ በ2011 ከነበረው 12.2 በመቶ እድገት በ2020 ወደ

6.7 በመቶ የቀነሰ ሲሆን በገቢ ምርት በ2011 ከነበረበት 22.5 በመቶ ወደ 12.8 በመቶ በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል።

**የኢትዮጵያ የንግድ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ አበባዎች እና አትክልቶች የሚያካትት ሲሆን፣ በከፍተኛ ደረጃ ከውጭ የሚገቡት ምርቶች መካከል ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መድኃኒት እና ነዳጅ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።** ወደ ኢትዮጵያ ከሚገቡት ምርቶች ከጠቅላላ የገቢ ምርቶች የተጣራ ፔትሮሊየም (12.4%)፣ መድሀኒት (6.5%)፣ ማዳበሪያ (4.5%)፣ ስንዴ (4.4%)፣ መኪናዎች (4.1%)፣ ፓልም ዘይት (3.6%)፣ የቴሌኮም መሳሪያዎች (3.4%)፣ ሩዝ (2.9%)፣ የኤሌክትሪክ ማሽነሪዎች (2.8%) እና ሌሎች የቤት እቃዎች (2.5%) የሚሸፍኑ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡት ሌሎች ጉልህ ምርቶች ሲሚንቶ፣ ስኳር፣ ብረታ ብረት እና ጨርቃ ጨርቅ ይገኙበታል።

**በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የንግድ ሚዛን ጉድለት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ተጽዕኖ እያሳደረ ሲሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ የውጪ ንግድ ተወዳዳሪነትን ማጎልበት፣ የገቢ ምርት ጥገኝነት መቀነስ እና ተጨማሪ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ ይጠይቃል።** እ.ኤ.አ. በ2021፣ መንግስት አስፈላጊ የሆኑ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን እና ሴክተርን መሰረት ያደረጉ የነዳጅ፣ የምግብ፣ የህክምና አቅርቦቶች እና የሜጋ ፕሮጀክቶች ፍላጎት ለማሟላት 30 ቢሊዮን ዶላር ብድር ከአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ተበድሯል። ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የምርቶች እና የአገልግሎት ፍላጎትን ለማሟላት አብዛኛው ወጪ የሚሸፈነው ከልማት ፖሊሲዎች ጋር የተጣጣመ በመንግስት የሚመራውን የኢኮኖሚ ኢንዱስትሪ ልማት ሞዴል እና በውጭ መንግስት ዕርዳታ እና ብድር ነው።

**የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በ2021 ወደ 8 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሲሆን፣ በአገልግሎት ዘርፉ በተለይም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ማግኘቱ የሚታወቅ አስተዋጽኦ አለው።** የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ዕድገት ዝቅተኛ ሲሆን በ2010 የነበረው የውጪ ንግድ 5.3 ቢሊዮን ዶላር በዓመት ከ5 በመቶ በታች ዕድገት በማስመዝገብ በ2021 ወደ 8 ቢሊዮን ደርሷል። ከዋና ዋና የውጪ ንግድ ምርቶች በተጨማሪም የአገልግሎት ዘርፉ በተለይም የትራንስፖርት ዘርፍ በውጪ ምንዛሬ ግኝት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው ሲሆን በ2021 ከ4 ቢሊየን ዶላር በላይ ገቢ በማስገኘት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአገልግሎቱ ዘርፍ ቀዳሚ ነው። ኢትዮጵያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) ብትስብም ለስራቸው ድጋፍ የሚሆኑ ግብዓቶች፣ አግልግሎቶችና መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ ባለመኖሩ ከውጪ ይገባል። ይሁን እንጂ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ሦስተኛው ደረጃ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ግኝት ሲሆን ይህም ለኢኮኖሚው እና ለገቢ ንግድ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና የመንግስት ተቋማት መረጋጋትን ጨምሮ በርካታ ምክንያቶች

ከአመት አመት እየጨመረ የመጣው ከውጪ የሚላከክ እና ድጎማዎች የመጨረሻው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ናቸው።

**በብዛት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ምርቶች የካፒታል እና የፍጆታ ዕቃዎች ሲሆን በበቀታ አመታት እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል።** የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ 2019/2020 ሪፖርትን መሰረት በፍጥነት እያደገ በመጣው የህዝብ ቁጥር፣ የኢኮኖሚ እና ከተሜነት መስፋፋት ምክንት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ምርቶች በከፊል ያለቀላቸው (22.4%)፣ የካፒታል እቃዎች (29.7%)፣ ነዳጅ (15.9%) እና የፍጆታ እቃዎች (28.9%) ሲሸፍኑ የተሽከርካሪ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ አልባሳት፣ ምግብ እና መጠጥ እና ሌሎች የፍጆታ እቃዎች ገበያ በፍጥነት እየሰፋ ነው። ከአጠቃላይ ገቢ ምርቶች 96.3 በመቶው ለአምራች አገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ እቃዎች  ሲሆን ቀሪው 3.7 በመቶው ደግሞ የግብርና እና ትራንስፖርት ዘርፍ ይሸፍናሉ። በተጨማሪም ጥቂት ወደ ኢትዮጵ የሚገቡ የፍጆታ ዕቃዎች መካከል እየጨመረ የመጣውን የትራንስፖርት ፍላጎት ለማሟላት አዳዲስ እና ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ይገባሉ። እንዲሁም ቴክኖሎጂ የመጠቀም ፍላጎት በማደጉ እንደ ስማርት ስልኮች፣ ላፕቶፖች እና የቤት/ቢሮ እቃዎች በጣም ተፈላጊ ናቸው። የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶች ከፍተኛው ወደ ሀገር ውስጥ ከሚገቡት ምርቶች ሲሆኑ የምግብና መጠጥ እና የመዋቢያ ዕቃዎች ይከተላሉ።

**ኢትዮጵያ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ማሽኖች፣ እቃዎች እና ጥሬ እቃዎች እንዲጨምሩ አድርጓል።** በዚህም ከ2010-2020 በነበሩት አስር አመታት የአምስቱም ዘርፎች ገቢ ምርቶች ተደምሮ ከፍተኛው ውጤት የተመዘገበው እ.ኤ.አ በ2014 ሲሆን ከአጠቃላ ገቢ ምርት 14 ቢሊዮን ዶላር 85% የሚሆነው 12 ቢሊየን ዶላር ሲሸፍን በተለይም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ዘርፍ ከአጠቃላ ገቢ ምርት በአማካይ 49% እና የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአት ዘርፍ በአማካይ 34% በማስገባት በቀዳሚነት ይቀመጣሉ።

**ያልተዳበረ እና በጥቂት ሸቀጦች ላይ ያተኮረ ምርት የውጪ ንግድ ፖርትፎሊዮ የኢትዮጵያ በሁሉን አቀፍ እድገት የምታደርገውን ጉዞ ላይ ተፅእኖ ፈጥሮባታል።** የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ድርሻ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ከ15 በመቶ በታች ሲሆን ከውጭ ከሚገባው 25 በመቶ በታች ነው፡ ፡ ይህም ከሚጠበቀው የውጪ ንግድ ~24 በመቶ አንጻራዊ ንፅፅር ሲታይ ሩዋንዳ እና ህንድን በቅደም ተከተል ያስመዘገቡት 21% እና 18% ጨምሮ ከአብዛኞቹ ሀገራት በታች በሆነ መጠን ላላት ሀገር ያስመዘገበው በጥቂት ዘርፎችና እና በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ያተኮሩ ነው። በሌላ በኩል እንደ ቬትናም እና ቻይና ያሉ ሌሎች ወደ መካከለኛ ገቢ ደረጃ ያደጉ አገሮች  የሚላክ የውጪ ንግድ እድገት ንፅፅር እጅግ

የላቀ ሲሆን በ2020 በቅደም ተከተል 106% እና 18% አስመዝግበዋል። በዚህም በኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈታኝ እየሆነ በመምጣቱ እና የአምራች ዘርፍ እንዲመራ በመከተለው ሞዴል የውጪ ንግድ በመንግስት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

**እ.ኤ.አ. በ2020 ኢትዮጵያ ከፍተኛ ከውጪ የገቡ ምርትና አገልግሎቶች፡ የትራንስፖርት፣ የአይሲቲ አገልግሎት፣ ተሽከርካሪዎችን፣ የአውሮፕላን ክፍሎች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እቃዎች እና የኮምፒውተር ሃርድዌርን ያካተተ ነበር።** በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ከሚገቡት ዋና ዋና ተሽከርካሪዎች ለምሳሌ መኪኖች፣ አውቶቡሶች፣ የጭነት መኪናዎች፣ ሞተር ሳይክሎች)፣ የአውሮፕላን እቃዎችና እቃዎች፣ መርከቦች እና ጀልባዎች፣ የባቡር ሀዲድ እና ትራም ዌይ ሎኮሞቲቭስ፣ ሮል ስቶክ እና ክፍሎች እንዲሁም የብስክሌትና የብስክሌት እቃዎች ዋና ዋና ናቸው። እንዲሁም ሀገሪቱ በተለይም በሶፍትዌር ልማት የራሷን የአይሲቲ ዘርፍ በማጎልበት ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ በማቀድ እየሰራች ቢሆንም አይሲቲ፣ የኮምፒውተር ሃርድዌር እና የሶፍትዌር እቃዎች፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እቃዎች እና መለዋወጫዎች (ለምሳሌ፡ ሞባይል ስልኮች፣ ሲም ካርዶች፣ ራውተሮች፣ ስዊች፣ ሞደሞች)፣ የሳተላይት እቃዎች እና አገልግሎቶች፣ የኤሌክትሮኒካዊ ክፍሎች (ማይክሮፕሮሰሰር፣ ሚሞሪ ቺፕስ፣ ትራንዚስተሮች) እና የአይቲ ማማከር እና ሌሎች ሙያዊ አገልግሎቶች በ2020 ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ናቸው።

**ውስን የምርት ስብጥር፣ በሸቀጦች ላይ ያለው ዝቅተኛ እሴት፣ የዋጋ ንረት እና የአገራዊ የማምረት አቅም ውስንነት የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ እድገት እንቅፋት ሆኗል።** እ.ኤ.አ. በ 2020 ሀገሪቱ 7.05 ቢሊዮን ዶላር ወደ ውጭ በመላክ -0.88 ነጥብ የኢኮኖሚ ውስብስብነት (Economic Complexity Score) በማስመዝገብ ከ146 አገራት 97ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ይህ እንደ ኬንያ ባሉ የጎረቤት ሀገራት ጋር ሲነፃፀር -0.47 ነጥብ የኢኮኖሚ ውስብስብነት ሲኖራት በአጠቃላይ 6.52 ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ያለው 103 ምርትና አገልግሎት ወደ ውጭ ልካለች።

**በኢትዮጵያ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ባለፉት አስር አመታት አሉታዊ የንግድ ሚዛን ይዘው (ማለትም ወደ ውጭ ከሚላከው ምርትና አገልግሎት ወደ ሀገር የሚገባው ምርት እጅግ በልጦ) ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።** ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ቀዝቅዘው እና የገቢ ንግድ አዝማሚያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። በተለይም በ'UNCOMTRADE' በ2013-2014 እንደዘገበው የሸቀጦች የውጪ ንግድ ጉልህ እድገት ቢያሳይም ነገርግን ከ2015 በኋላ ወደ ውጭ የተላከው ከአለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማት (IMF) ሪፖርት ከደረጃ በታች መሆኑን ያሳያል። በመንግስት ድጋፍ፣ ለአምራቾች በተመጣጣኝ የሰው ኃይል ወጪ፣ በተመረጡ የንግድ ስምምነቶች የተመቻቸ የገበያ ተደራሽነት እና የመሠረተ ልማትና የኢንዱስትሪ

ፓርኮች ልማት መመቻቸቱ ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች መጨመር ትልቅ አስተዋጽዖ አለው። ከተመረተው ምርት ከፍተኛ ወደ ውጭ ከሚላከው ከምግብና መጠጥ ዘርፍ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደ ቡና፣ የዘይት እህል ፣ጥራጥሬ፣ ሻይ፣ ቅመማቅመም እና የተከተፈ አበባ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ። የእነዚህ ምርቶች ዋና የመዳረሻ ገበያዎች ቻይና 16.6 በመቶ ስትይዝ፥ ከአሜሪካ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ጀርመን እና ኔዘርላንድ 11%፣ 10.4%፣ 7.6% እና 4.7% በቅደም ተከተል ይሸፍናሉ።

## 2.3 የተኪ ምርት ስትራቴጂ አስፈላጊነት

1. በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት የተኪ ምርት ስትራቴጂ እንደ አንድ የፒሊሲ ስልት መተግበር የምንዛሪ እና የወለድ ተመንን ለመመጥን፣ የዋጋ ግሽበትን ለማረጋጋት፣ የንግድ ሚዛንን ለመጠበቅ እና የአንድ ሀገር እራስን በራስ የመቻል ፕሮግራሞችን ለማሳካት ይረዳል። የተኪ ምርት ስትራቴጂ በምንዛሪ ተመን እና በንግድ ሚዛን ላይ የሚያሳድረውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ለመፈተሽ በተደረገ ጥናት መሰረት የተኪ ምርት ስትራቴጂ ትግበራ በጋና ያለውን የሀገር ውስጥ ምንዛሪ ዋጋ መጠንን በማዳበር የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን ለማረጋጋት አስችሏል ። ከ1990 እስከ 2021 ባለው የሩብ ዓመት መረጃ መሰረት የጋና የሀገር ውስጥ የምርት ተወዳዳሪነት አቅምን እና የንግድ ሚዛንን በማሻሻል የዋጋ ግሽበትን እና የወለድ ምጣኔን በተገቢው ደረጃ ማስተዳደር እና የማምረት አቅምን መጨመር አስችሏል። በተመሳሳይ በአርጀንቲና የተኪ ምርት ስትራቴጂ ትግበራ ውጤታማነት ጥናት መሰረት አንድ ሃገር የውጭ የኢኮኖሚ ጫናን በአግባቡ መቋቋም ከቻለ፣ የተኪ ምርት ስትራቴጂ በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ያላ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ታይቷል።

   **ስለሆነም በመከከለኛ እና በረዥም ጊዜ ውስጥ የማክሮ ኢኮኖሚውን ከማረጋጋት አንፃር የተኪ ምርት ስትራቴጂ እንደ አንድ ስልት መንደፍ የኢትዮጵያን የውጪ ምንዛሪ እጥረት ከመቀነስ እና የንግድ ሚዛንን ከማስተካከል አንጻር ተገቢ እና ወቅታዊ ስለሆነ፤**

2. ዘላቂ የፖለቲካ ሉዓላዊነት ከማረጋገጥ አንጻር እንደ ሃገር በመሰረታዊ ጉዳዪች ላይ እራስን ለመቻል የተኪ ምርት ስትራቴጂ አንዱ ስልት በመሆኑ ይህን ስትራቴጂ ማዘጋጀት አስፈልጓል። የተባበሩት መንግስታት የምግብ እና ግብርና ድርጅት (FAO) በአለም አቀፍ የምግብ ዋስትና ላይ ባወጣው ሪፖርት መሰረት በ2050 የአለም ፖለቲካ ዋና አሽከርካሪዎች ከሚሆኑት ጉዳዎች መከከል የምግብ ዋስትና እና እራስን መቻል ይገኙበታል። ስለሆነም የተኪ ምርት ስትራቴጂ ሊተገበር የሚችል የመንግስት የድርጊት መርሃ ግብር በማቅረብ የምግብ ዋስትና እና በምርት እራስን በመቻል የሀገርን የፖለቲካ ሉዓላዊነት እንዲያረጋግጥ ያስችላል።

**የምግብ እና የምርት ዋስትናን በተኪ ምርት ስትራቴጂ ማሳካት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ደህንነት እና ሉዓላዊነት ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን በተለይ በአለም አቀፍ የምግብ እና የምርት ገበያ ችግር ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው ምግብ እና ጥራት ያለው ምርት በማምረት የህዝብን የምግብ ፍላጎት እንዲሁም የኢንዱስትሪውን የጥሬ እቅ ፍላጎት በቅድሚያ በማርካት ተወዳዳሪ ምርቶችን ለአለም ገበያ ማቀረብ ስለሚያስችል፤**

3. ቀድሞ የተጀመሩ ሀገራዊ የልማት ዕቅዶች እና ፕሮግራሞችን ለመተግበር እንዲሁም ለማሳክት ስልታዊ መሆን በማስፈለጉ የተኪ ምርት ስትራቴጂን ማዘጋጀት አስፈልጓል (ለምሳሌ የጸጥታ አካላት የደምብ ልብስ ፕሮጀክትን መጥቀስ ይቻላል)። በ2030 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን እሴት መጨመር በኢንዱስትሪው ዘርፍ እና በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት በቅደም ተከተል መሰረት ከ 5.8% እና 6.9% ወደ 13.2% እና 17.2% ማድረስ ብውአስር አመቱ የልማት እቅድ (TYDP) ግቦች የተለዩ ናቸው። ከቀደሙት የኢንዱስትሪ ዕቅዶች በተለየ TYDP ለሀገር ውስጥ ተኪ ኢንዱስትሪዎች እና ተኪ ምርቶች እንዲሁም የውጪ ንግድን በማጠናከር በኩል ተመጣጣኝ ትኩረት ይሰጣል። ይህም ምርታማ ሴክተሮች የአምራች ኢንዱስትሪውን ጨምሮ ፖሊሲዎችን፣ፕሮግራሞችን፣ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን መንደፉ እና አገራዊ ቁርጠኝነትን ከግብ ለማድረስ የተግባር እቅዳቸውን መዘርዘር እንዲሁም ስልቶችን መቀየስን ይጠይቃል።

**የኢትዮጵያ መንግስት የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ከ30 በመቶ ወደ 60 በመቶ የገበያ ድርሻ ለማሳደግ ሀገራዊ ግብ አስቀምጧል፤ ይህንን ግብ ተግባራዊ ለማሳካት የአገር ውስጥ አምራቾችን የተኪ ምርት ስትራቴጂን በማዘጋጀት ዝርዝር ስልት መንደፍ ያስፈላጋል።**

4. የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪያላይዜሽን እንቆቅልሽ ለመቅረፍ እና የተሻሻለ ተወዳዳሪነትን ለማምጣት የተኪ ምርት ስትራቴጂን ማዘጋጀት አስፈልጓል። ኢትዮጵያ በአንድ መልኩ በመሰረተ ልማት ዝርጋታ በተለይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንድስትሪ በመሳብ እና የምርት ልማትን በማምጣት በኩል አምርቂ የሚባል ውጤት እያስመዘገበች ቢሆንም ከአገሪቱ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ እና የኢኮኖሚ እድገት አንጻር በተለይም ስራ ከመፍጠር አንጻር ብዙ ክፍተት አለ። በዩ/ኤ/ን/ሲ/ቲ/ድ በተሰራው የኢትዮጵያ የብሔራዊ የምርታማነት አቅም ክፍተት ግምገማ መሰረት በ2018 ኢትዮጵያ ከአጠቃላይ የPCI ደረጃ ከ184 አገራት በ169ኛ ላይ በዝቅተኛ የምርታማነት አቅም ተርታ ተቀምጣለች ። ይህም በማኑፋክቸሪንግ ዝርፉ በዝቅተኛ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ አምራችነት፤ ዝቅተኛ እሴት በመጨመር እና በዝቅተኛ ደረጃ ወደ ውጭ

በመላክ የሚመጣ ነው። በተለይም የአምራች የኢንዱስትሪው ዝቅተኛ ዋጋ ያለው መሰረታዊ የሚባሉ ምርቶችን በመላክ እና ትንሽ ወይም ምንም የቴክኖሎጂ ውስብስብነት የሌላቸው ምርቶችን በማመረት ይገለጻል። ስለሆነም ለረጅም ጊዜ የተከተልነው የዉጪ ንግድን መር ያደረገ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ፓሊሲ በአንድ መልኩ አመርቂ የሚባለ የበላ ሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት እንዲመዘገብ ቢረዳም በሌላ በኩል "እንቆቅልሽ" በሚመስል ሁኔታ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡትን ምርቶች በመቀነስ፣ ተኪ ምርቶችን በማምረት፤ የንግድ ሚዛኑን በመጠበቅ እንዲሁም የስራ እድል በምፍጥር መዋቅራዊ ሽግግን ማምጣት በኩል እጅግ ደካማ ነው።

**ስለሆነም የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥም ሆነ በወጪ ገበያ ላይ ያላቸው ድርሻ እና ተወዳዳሪነት ዝቅተኛ መሆን የተኪ ምርት ስትራቴጂን ማዘጋጀት የኢትዮጵያን ኢንዱስትሪያላይዜሽን እንቆቅልሽ ከመፍታት አንጻር አስፈላጊ ያደርገዋል።**

## 2.4 የተኪ ምርት ስትራቴጅ ገለጻ እና ቁልፍ መርሆች

**የተኪ ምርት ስትራቴጂ ስልቱን ለመግለጽ የማስፈጽሚያ መንገዱን ለመለየት እና የማስፈጽሚያ መርሆዎች ለማስቀመጥ የሀገር ውስጥ እና የአለም አቀፋዊ የዘት ያላቸውን እሳቤዎችን በዝግጀቱ ዳሷል።** ለኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ከውጭ የሚገቡትን መተካት ምን ማለት እንደሆነ የሚገልጽ ልዩ የሕግ ማዕቀፍ የለም፣ ወይም የሚገቡትንም የሚከለክል ገደብ የለም። ሆኖም የተለያዩ የመንግስ የፓሊሲ አስፈጻሚ የፌደራል ተቋማት፤ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የህግ ማእቀፎች የሀገር ውስጥ ምርትን እና ገበያን የመጠበቅ፤ የመቆጣጠር እንዲሁም አምራቾችን የመደገፍ ግዴቶዎችን ያስቀምጣሉ፣ ይደነግጋሉ፣ በየደረጃዉም ያስተገብራሉ።

**የአለም አቀፍ እሳቤዎችን በምንዳስስበት ወቅት ሁለት እሳቤዎችን ከግምት ማስገባት ተገቢ ነው።** አንደኛው ታዋቂው ኢንዱስትሪያል ኢኮኖሚስት ዳኒ ሮድሪክ ታዳጊ አገሮች ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ የሚያተኩር የኢንዱስትሪ ስትራቴጂዎችን (Inward Looking Industrialization) ሲነድፉ መመስረት የሚገባቸው አሥር የንድፍ መርሆዎች አሉ ብሎ ያስቀምጣል። በነዚህ መርሆች መሰረት ኢንዱስትሪያላይዜሽን የእድገት መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለዉ የማስመጣት አቅምን ለመቀነስ እና የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪነትን መሰረት ባደረገ መልኩ ጊዜው የተገደበ የመንግስት ድጋፍ/ማበረታቻን በመተግበር እንዲሁም አፈጽጸሙንም በመከታተል መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል።

**እንደ አይኤምኤፍ ገለፃ ሁለተኛው እሳቤ ደሞ በሚገባ የታሰበ እና በውጤታማነቱ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ትግበራው በተወዳዳሪ ምርቶች እና ገበያዎች ላይ ካተኮረ ከዛም ባሻገር**

**በተመሳሳይም ስልታዊ የኤክስፖርት ማስፋፊያ መርሃ ግብሮችን ጎን ለጎን ማስተገበር ከተቻለ ዘርፉ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል እሳቤ ነው።** አገሮች በጊዜ የተገደቡ ስልቶችን ሲነድፉ በመጀመሪያ ወደ ሀገር ውስጥ በከፈተኛ ደረጃ የሚገቡትን የፍጆታ ዕቃዎችን በመለየት በሀገር ውስጥ በማመረት ከውጪ የሚገቡትን በአገር ውስጥ ምርትና ጥሬ ዕቃ በመተካት ይጀምራሉ። ይህንንም ለማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የፍጆታ እቃዎች እና ጥሬ እቃዎች ላይ ታሪፍ በመጣል እና የሃገር ውስጥ አምራቾችን ከለላ በማድረግ እንዲሁም ለተመረጡ የፍጆታ እቃዎች አምራቾች ድጋፍ መስጠት ዋነኛ ናቸው። በሁለተኛ ደረጃ የሚነደፈው ስትራቴጂ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚዉሉ የካፒታል እቃዎችን እና ግባቶችን መተካት አገሮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለባቸው ስትራቴጂካዊ መርሆዎች ናቸው።

**በዚህም መሰረት ይህ ተኪ ምርት ስትራቲጂ ማለት፡**

የአምራች ኢንዱስትሪን ለማስተዋወቅ እና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ከሌሎች ስልቶች እና ፓሊሲዎች ጋር በማይጣረስ መልኩ ስተራቲጂክ የተኩ ምርቶችን ማሳደጊያ ስልቶችን በተመረጡ ምርቶች እና ኢንዱስትሪዎች ላይ የጊዜ ገደብ ያለው የመንግስት የማበረታቻና ድጋፍ ማስተግበሪያ አንድ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ስልት ነው።

**የስትራተጂው ግብ፡** በተመረጡ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፎች ራስን በመቻል የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ለዘላቂ የስራ እድል ፈጠራ፤ ለላቀ የገበያ ድራሻ እና ለተመጣጠነ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እድገት ማመቻቸት ነው።

**ስትራተጂካዊ መርሆዎች፡-** ያልተጣረሰ የተኪ ምርት ትግበራ ማለት የሀገር ውስጥ ምርትን እና የሀገር ውስጥ የምርት ፍጆታን ከግምት በማስገባት የአምራች ኢንዱስትሪውን ገበያን በማያዛባ መኩ በማስተዋወቅ እና የምንግስት ድጋፍ ማድረግ ነው።

የሚከተሉት ዝርዝር ስትራቴጂካዊ መርሆች ናቸው፤

i. **ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮረ፡-** የውጭ ሸቀጦችን በእኩልነት የመወዳደር አቅም ያላቸውን የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች እና ምርቶች ላይ ያተኮረ፤
ii. **በጊዜ የተገደበ የመንግስት ጣልቃገብነት፡-** ለተመረጡት ኢንዱስትሪዎች በጊዜ የተገደበ እና በአፈጻጸም ላይ የተመሰረተ የመንግስት ድጋፍ፣

iii. **የሸማቾች ምርጫ ላይ ክፍተት የማይፈጥር፡-** ማንኛውም ጣልቃገብነት የሸማቾችን ምርጫ ሳይገድብ ለሸማቾች የሀገር ውስጥ እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ጨምሮ ሰፋ ያለ አቅርቦትን በማያኮስስ መልኩ መተግበር የሚኖርበት፣

iv. **የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ፡-** የስትራቴጂ እንደ የዋጋ ንረት ወይም የክፍያ ሚዛን ችግሮች ያሉ ማክሮ ኢኮኖሚ ሚዛኖችን አይፈጥርም እና ከሌሎች የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ የመንግስት የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲዎች እና የንግድ ፖሊሲዎች ጋር በተዛመደ መልኩ መተግበር አለበት፣

v. **ጎጂ ያልሆነን የአለም አቀፍ ንግድን የሚያበረታታ (Non-Extractive International Trading)፡-** ይህ ስትራቴጂ ማግለል ወይም ጥበቃን ለማስፋፋት ጥቅም ላይ መዋል የለበትም ይልቁንም አለም አቀፍ ንግድንና ትብብርን የሚያበረታታ ሰፊ ስትራቴጂ አካል ሆኖ ሀገሪቱን ከዝቅተኛ እሴት እና ከሀብት ብክነት በመጠበቅ ተግባራዊ መሆን አለበት።

# 3 ክፍል ሶስት

## 3.1 ተወዳዳሪ ንዑስ ዘርፍ እና የምርት ልየታ

### 3.1.1 የስትራቴጂው ማዕቀፍ

**ስትራቴጂው በአምስት ንዑስ ዘርፎች የተዋቀረ ሲሆን በአምስቱ ስር ያሉ ቁልፍ ምርት ምድቦች ላይ ማተኮር አስፈላጊ በመሆኑ ከምግብና መጠጥ፣ ከጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ከኬሚካልና ከኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንኡስ ዘርፎች ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች ተለይተዋል።** እነዚህን ምርቶች በትንታኔ ማዕቀፉ ላይ በመመስረት ቅድሚያ የመስጠት ስራው የተካሄደው i) ከውጪ የሚገቡ ምርቶች የአገር ውስጥ ፍላጎትን በማየት፣ ii) ከውጪ የሚገቡ ምርቶች የሀገር ውስጥ አቅርቦት (የምርት ደረጃ) በማየትና ጥገኝነቶችን በመለየት፣ iii) በአገር ውስጥ የሚመረቱ ዕቃዎች ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦች ጋር ሲወዳደሩ ማሟላት ያለባቸው የጥራት ደረጃዎችን ማሟላት ይችሉ እንደሆነ መገምገም እና የመተካት አቅምን በማየት፣ እና iv) የመንግስት አሰራርና፣ የደንብና ቁጥጥር እንቅፋቶችን፣ ቅድሚያ ምሚሰጣቸው የመንግስት ተነሳሽነቶችን እና ፖሊሲዎችን፣ እና የእሴት ሰንሰለት ልማት ሁኔታን ጨምሮ በመተንተን ነው።

**የምርቶችን ትንተና ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ ይህ ክፍል የንዑስ ዘርፉን አጭር መግለጫ፣ የተወዳዳሪ ምርቶች ትንተና ውጤት እና በዚህም መሰረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ዝርዝር ያብራራል።** አጭር የንዑስ ዘርፎች ቅኝት ከተደረገ በኋላ ከውጪ የማስገባትና የአጠቃላይ ፍላጎትና የአምራች ዘርፉን የእድገት ደረጃ ትንተና ለእያንዳንዱ ንዑስ ዘርፎች ይከተላል። ሁለተኛው ክፍል በዋናነት የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን፣ የጥሬ ዕቃ አጠቃቀምን እና ወጪ ቆጣቢነትን በተመለከተ ከስራ ፈጠራና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ቀለል ያለ እይታ ያሳያል። በመጨረሻም ቅድሚያ የተሰጣቸው ተወዳዳሪ ተኪ ምርቶች በየንዑስ ዘርፍ ክፍል መጨረሻ ላይ ተዘርዝረዋል።

**ቅድሚያ ለተሰጣቸው የምርት ምድቦች ያለውን ፍላጎት ከመጠቀም በተጨማሪ ስትራቴጂው በአገር ውስጥ ለሚመረቱ ምርቶች አዲስ ፍላጎት መፍጠርን እንደ አንድ አላማ የያዘ ነው።** እየጨመረ የመጣው የሀገር ውስጥ ፍጆታ ብቻውን የአምራች ዘርፉን እድገት በዘላቂነት ለመደገፍ በቂ ላይሆን ስለሚችል፣ ስትራቴጂው ለውጭ ገበያ የሚሆኑ ዕድሎችን ለመፈተሽ እና የተጠቃሚዎችን መሰረት ለማብዛት ይፈልጋል። ስትራቴጂው የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማርካት እንዲሁም ለማለፍ በቂ ምርት እንዲኖር በሃብት አቅርቦት ላይ የተመሰረተ የማምረት ስራዎችን ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ ለመመደብ የኢንዱስትሪ ኮሪደሮችን መፍጠር እና ማሳደግ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የአገር ውስጥ ፍላጎትን ለማርካት የተቃረቡ ምርቶችን ሀገር ውስጥ ከመጠቀም ባለፈ ወደ ውጭ

ለመላክ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማሸጋገር ስትራቴጂው ቅደም ተከተል የጠበቀ አካሄድ ተጠቅሟል። አንዳንድ የምርት ምድቦች ቀድሞውኑ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ፍላጎት እንዳላቸው እና በአሁኑ ጊዜ በአገር ውስጥ እንደሚመረቱ በመገንዘብ ስትራቴጂው ያለውን የማምረት አቅም በማጎልበትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የሀገር ውስጥ ገበያን ሰፊ ድርሻ በመያዝ ቀስ በቀስ ወደ ወጪ ንግድ ተኮር የምርት ሽግግር ለማድረግ ያለመ ነው። ይህ አካሄድ ኢትዮጵያ ያላትን ጠንካራ ጎኖች ተጠቅማ አሁን ያላትን የማምረት አቅሟን እንድትገነባ ከማስቻል አልፎ ስትራቴጂካዊ በሆነ መልኩ የወጪ ንግድ መሰረቱን በታለመ መልኩ እንድታሰፋ ያስችላታል። ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ፍላጐትና ያልተነካ የወጪ ንግድ አቅም ባላቸው የምርት ምድቦች ላይ በማተኮር ስትራቴጂው በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፍላጎትን ለማነቃቃት የአምራች ዘርፉን እድገት ለማጎልበት እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅዖ ለማድረግ ያለመ ነው።

**በተጨማሪም የተኪ ምርት ስትራቴጂው ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠር እና ማሳደግ ያለውን ጠቀሜታ አጽንኦት ይሰጣል።** እንደ ፋይናንስ፣ መሠረተ ልማት፣ ግብአት ወዘተ ባሉ ዘርፎች ላይ ያሉ ችግሮችን ከመፍታት ጀምሮ በተመረጡት ምርቶች ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎችን እስከመንደፍ እና የምርት ሂደቶችን ለማመቻቸት እና ቅልጥፍናን ለማሳደግ ቅንጅትን ማጎልበት፣ ትብብርን ማሻሻል እና ለአምራች ስራዎች ምቹ ሁኔታን መፍጠርን ያቅዳል። ይህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለዘርፉ እና በውስጡ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ እርምጃዎችን በትብብር ለመለየት ይደገፋል። ይህ አካሄድ የስትራቴጂው መፍትሄዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ የኢትዮጵያን ልዩ ጥንካሬዎች በብቃት ለመጠቀም እና መተግበር ከሚያስችሉ ሀገራዊ እና የዘርፍ እቅዶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

## 3.2 የአምራች ዘርፍ ገቢና ምርት ነባራዊ ሁኔታ

### 3.2.1 የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ

**የምግብና መጠጥ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪው የግብርና ምርታማነትን እና የገጠር ኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን የማስኬድ አቅም ያለው ቢሆንም የመንግስት ድጋፍ የሚሹ የእሴት ሰንሰለቶች ውስጥ የስርዓት አግሮ ፕሮሰሲንግ ተግዳሮቶች አሉ።** በዘርፉ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታትና የወጪ ንግድ እድገትን እና የገቢ ንግድን በተለይም በምግብ እና መጠጥ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለማስተዋወቅ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል። በኢንዱስትሪው ዘርፍ ከቆዳና ጨርቃጨርቅ ንኡስ ዘርፎች ቀጥሎ በሰስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም፣ የምግብና መጠጥ ምርት ደረጃ ከፍላጎት በታች በመሆኑ፣ የምግብና የመጠጥ ምርቶች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡና የገቢ መጠኑም

እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል። በምግብ እና መጠጥ ንኡስ ዘርፍ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ምርቶች በተጠራቀመ ዓመታዊ የእድገት መጠን (a cumulative annual growth rate) እ.ኤ.አ ከ2017 እስከ 2021 በ24% የተቀነባበሩ ምርቶች ፍላጎት እያደገ በመምጣቱ እና በአካባቢው የማምረት አቅም ውስንነት ፍላጎቱን ለማርካት አድጓል። እ.ኤ.አ. በ2017 ከ1.82 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላርና በመጠን ከ3.09 ሚሊዮን ቶን ከነበረበት እ.ኤ.አ በ2021 እስከ 4.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በመጠን ደግሞ 6.97 ሚሊዮን ቶን ድረስ የምግብ ዘይት፣ ሩዝ እና ስኳር፣ አትክልትና ፍራፍሬ እና የእንስሳት ተዋጽኦዎች ጭምር በብዛት ከሚገቡት የምግብ እና የመጠጥ ምርቶች መካከል ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። ይህ ደግሞ ቀድሞውንም እጥረት ለነበረው የውጭ ምንዛሪ ክምችት መመናመን አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ በየጊዜው እያደገ የመጣውን የህዝቡን ፍላጎት ለማሟላት ከውጭ ለማስገባት ግልፅ እድል ይሰጣል። በ2021/22 የኢትዮጵያ የስኳር ፍላጎት የነፍስ ወከፍ 11 ኪ.ግ/ካፒታል፣ በአጠቃላይ 1.3 ሚሊዮን ቶን ፍጆታ ሲኖረው በሀገር ውስጥ በስራ ላይ የሚገኙት 12 የሚደርሱ የስኳር አምራቾች የማምረት አቅማቸው በዓመት 450,000 ቶን ስኳር አካባቢ ነው። በአገር ውስጥ የሚመረተው ስንዴ በተለይም ፓስታ ለማምረት የሚውለው የዱረም ስንዴ ምርት በቂ ባለመሆኑ ኢትዮጵያ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡት የስንዴ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ጥገኛ ነች። ይሁን እንጂ መንግስት ዘላቂ የግብርና ልማትን በማስፋፋት የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል። በኢትዮጵያ የምግብና መጠጥ ንኡስ ዘርፍ የእህል ውጤቶች፣ ዳቦ መጋገሪያ እና ጣፋጮች፣ እናሌሎች.

**በአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር እያደገ በመምጣቱ የምግብ እና መጠጥ ዘርፍ የጥሬ ዕቃ ፍላጎት እያደገ በመምጣቱ የምግብ እና መጠጥ ዘርፉ የገቢ መጠን ጥምርታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨምሯል።** በ2020 በኢትዮጵያ ከ1,100 በላይ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ተቋማት ተፈጥረዋል። መንግስት የኢንዱስትሪውን እድገት በተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። በዚህም ምክንያት በንዑስ ዘርፉ ከውጭ የሚገባው የጥሬ ዕቃ ድርሻ ከ22% በ2001-02 ወደ 30% በ2019-20 ዕድገት አሳይቷል። ይህም የሆነው የአምራቾች የማምረት አቅም በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ነው። ነባር አምራቾች በሙሉ አቅማቸው እየሰሩ አይደሉም፣ ናሙና የተወሰዱ አምራቾች በአማካይ 49% የአቅም አጠቃቀማቸውን ብቻ እየተጠቀሙ መሆኑን ያሳያል። ምንም እንኳን የሀገር ውስጥ አቅርቦቱ እያደገ ከመጣው የምግብና መጠጥ ዘርፍ ፍላጎት ያነሰ ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ለግብርና ምርት ተስማሚ የአየር ንብረት እና የአፈር ሁኔታዎችን ጨምሮ ምቹ ሁኔታዎች አሏት። የሰብል ምርትና ሌሎች ጥሬ ዕቃዎችን በማስፋፋት የአገሪቱን የገቢ ጥገኝነት ለመቀነስ እድሎች አሉ። የኢትዮጵያ መንግስት በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ፖሊሲዎችንና ማበረታቻዎችን ተግባራዊ አድርጓል። እንደ ከቀረጥ ነፃ

ማስመጣት፣ ማሽነሪዎችና ጥሬ ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ፋይናንስ ማግኘት የመሳሰሉትን ኢንቨስትመንቱንና ዘርፉን ለመደገፍ ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ነገር ግን የምግብና መጠጥ ዘርፍ ያለውን እምቅ አቅም ሙሉ በሙሉ እውን ለማድረግ በአገር ውስጥ ምርት፣ ፈጠራ እና መሠረተ ልማት ላይ ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንት ይጠይቃል። የንግድ ጉድለቱን በመቀነስ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት መተካት የሀገሪቱን ተወዳዳሪነት ከማሳደግ ባለፈ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለድህነት ቅነሳና ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለሁሉም ምርቶች ቅድሚያ የመስጠት አቅም ያለው የትግበራ ጊዜ እና ምክንያታዊነት በአባሪ I ውስጥም ተካትቷል።

**ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት ባላቸው ተወዳዳሪነት 11 የምግብ እና የመጠጥ ምርቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸዋል።** እነሱም የቢራ ብቅል፣ ፓስታና ማካሮኒ፣ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ማንጎ ጁስ፣ የምግብ ዝግጅት፣ የበቆሎ ውጤቶችና ስናክስ፣ የዳቦ መጋገሪያ ምርቶች፣ ልዩ ልዩ የዱቄት እይነቶች፣ የእንስሳት ውጤቶች እና የበለፀጉ ምግቦችን (አልሚ ምግቦች) ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች አቅም አለው። ስኳር ከፍተኛ የመንግስት ድጋፍ አለው ነገር ግን ዋናው ፈተና ረጅም የሸንኮራ አገዳ ምርት ጊዜ እና ጊዜ ያለፈባቸው ማሽኖች ናቸው። ማንጎ ጁስ ማቀነባበርም የውድድር ቦታ ነው፣ ነገር ግን ከተለያዩ ማንጎ ዝርያ መረጣ ወይም ምርጫዎች ጀምሮ እስከ ማንጎ ፍሬ ብስለት ድረስ ያለው ረጅም ጊዜ ይወስዳል። የምግብ ዝግጅት ገበያው አልሞላም እና ለአዳዲስ ባለሀብቶች እርሾን፣ ቤኪንግ ፓውደር፣ ፈጣን እርሾን (instant yeast)፣ ማኮፈሻን (leaving agent) እና ባይ-ካርቦኔትን በማዘጋጀት ረገድ ዕድሎችን ይሰጣል። የበቆሎ ማቀነባበር ዘርፉ ለበቆሎ ዱቄት፣ ስታርች፣ የበቆሎ ቅንጣቢ ወዘተ ለአዳዲስ ኢንቨስተሮች ገበያንና ዕድሎችን የሚያቀርብ ሌላው አማራጭ ነው:: የዳቦ መጋገሪያ ምርቶች ገበያ ችሎታ እና ቴክኖሎጂ ያላቸው በርካታ አምራቾች አሉት፣ ነገር ግን ፕሮሰሰሮች በቂ ያልሆነ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ምክንያት ከአቅም በታች እየሰሩ ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ገበያ ባለሀብቶች የምግብና የመጠጥ ንኡስ ዘርፍን በመከታተል የምግብ ፍላጎት እያደገና ጠንካራ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል አቅም አለው።

### 3.2.2 የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ

**በሀገራችን የጨርቃጨርቅና አልባሳት የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ታሪክ ከ1930ዎቹ ጅማሪ ያለው ቢሆንም አጠቃላይ እድገቱ ሲታይ እንደ አመሰራረቱ ፈጣን እመርታን ያሳየ አልነበረም።** ሆኖም ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላ መንግስት የተከተለው የርዕዮተ-ዓለም አቅጣጫ ለውጥ በኢኮኖሚው ላይ የተነቃቃ ሁኔታን በመፍጠሩ በንዑስ ዘርፉ ላይ የተሻለ ኢንቨሰትመንት በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ መሳብ ተችሏል። አዳዲስ ኢንቨሰትመንቶችም እንዲያቆጠቁጡ በምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አነስተኛ

ዋጋ የሚጠየቅበት የሰው ጉልበት መኖሩ፣ ርካሽ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት መቻሉ፣ የተሻለ የገበያ ተደራሽነትና ተፈላጊነት ወዘተ መኖራቸው በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ መካከለኛና ከፍተኛ ፋብሪካዎች ቢከፈቱም፤ ከእነዚህ ውስጥም ቀላል የማይባሉ ፋብሪካዎች አምራች ላኪዎችን ቢፈጥሩም፤ ሀገሪቱ ያለባትን የጨርቃጨርቅና አልባሳት ፍላጎት ክፍተት የሚያሟሉ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡ በዚህም የተነሳ ከ2017-2021 (እ.አ.አ) ያለውን ጠቅላላ የዘርፉ የገቢ ንግድ መጠን ሲታይ በአንድ በመቶ እደገት የነበረው እና የመግዣ ዋጋው ግን በተነፃፃሪነት በሁለት በመቶ ቅናሽ የነበረው ነው፡፡ ይሁንና ከጠቅላላው የወጪ-ገቢ ንግድ ንፅፅር ሲታይ 75 በመቶ የሚያህል የንግድ ጉደለት የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ዓመታት አማካይ ዓመታዊ ጠቅላላ የገቢ ንግዱ 600 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይደረሳል፡፡

**በሀገር ውስጥ ያሉ አምራቾች ከክር ማምረት ጀምሮ፣ በሽመና፣ በቴክስታይል ፕሮሰሲንግ (ማንፃት፣ ማቅለምና ማጠናቀቅ ወዘተ) እና በስፌት ላይ እየተሳተፉ ያሉ ናቸው፡፡** እነዚህ ፋብሪካዎች ምርቶቻቸውን በአብዛኛው ለሀገር ውስጥ ሽያጭ የሚያውሉ ቢሆኑም፤ ከውጭ በአነስተኛ ዋጋ እየገባ ያለው ምርት እንደ ወጭ ንግዱ ሁሉ በሀገር ውስጥም ተወዳዳሪ ሆነው እንዳይቆዩ እያደረጋቸው ነው፡፡ ጥቂት የሚሆኑት ፋብሪካዎችም ጥራታቸውን የጠበቁና ተፈላጊ ምርቶችን አምርተው እያቀረቡ ያሉ ቢሆንም ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቆዩ ለማድረግ እየጠየቃቸው ያለው የክህሎትና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጉዳይ በቀላሉ የሚታለፍ እየሆነ አይደለም፡፡

**ይህ ንዑስ ዘርፍ ለየት የሚያደርገው በየደረጃው ያሉትን ምርቶች ለማምረት የሚጠቀማቸው ግብዓቶች መብዛታቸው ብቻም ሳይሆን አብዛኛውን ጥሬ ዕቃዎች ከውጭ የሚያስገባ መሆኑ ነው፡፡** ምንም እንኳን የተወሰኑት ምርቶች የተለመደውን የጥጥ ምርት በግብዓትነት የሚጠቀሙ ቢሆንም፤ ከተጠቃሚው ፍላጎትና ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች አንፃር ከዚህ ውጭ የሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ጭረቶችን የሚፈልግ መሆኑ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ እንዳይገኙ አድርጓል፡፡ ከዚህም በላይ የአልባሳት ተለጣጣፊዎች (trims and accessories)፣ ለጨርቃጨርቅ የሚውሉ ቀለማቀለሞችና ኬሚካሎች ከሞላ ጎደል ከውጭ የሚመጡ መሆናቸው የሀገሪቱን የንዑስ ዘርፉ የገቢ ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ከጠቅላላ ጠቅላላ የጥሬ ዕቃ ዋጋ አንፃር ከ50 በመቶ በላይ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህንን ሂደት ከመሰረቱ ለመቀየር ትልቅ ልፋትና ውስብስብ ቴክኖሎጂ የማይጠይቁ አዳዲስ የተፈጥሮ ጭረቶችን ማምረት ከመጀመር፤ የጥጥ ምርትን በጥራትና በብዛት እንዲቀርብ ልዩ ትኩረት ከመስጠት፤ የገበያውን ፍላጎት ወደነዚህ ምርቶች ከመሳብና በቀጣይ ወደ ሰውሰራሽ ጭረቶችና ቀለማ ቀለሞች ለማምረት ወደ መሸጋገር

ከማሰብ ይልቅ ሁሉንም ምርቶች ያለ ገደብ እያስገባን መቆየታችን ለዚህ ከፍተኛ የገቢ ጥሬ ዕቃዎች ከጠቅላላ ዋጋ አንፃር እንዲጎር በር ከፍቷል።

**ንዑስ ዘርፉ እየፈጠረ ያለውን የሰራ ዕድል፣ የደረሰበት የአቅምና፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለመመልከት ያህል፤ ያለውን እድገት መሰረተ በማድረግ በ2025 (እ.አ.አ) 683,441 ቋሚ፣ 867,970 ጊዜያዊ በድምሩ1,551,411 ለሚሆኑ ሰራተኞች የሰራ ዕድል ይፈጠራል ተብሎ ይገመታል።** ከማምረት አቅም አጠቃቀም አኳያ ፋብሪካዎች ያሉበት ደረጃ ሲታይ ከ50 በመቶ ያልበለጠ ሲሆን፣ በዳሰሳ ጥናት የተረጋገጠውም ከዚህ በታች ሊሆን እንደሚችል ነው። በቴክኖሎጂ አጠቃቀምም ቢሆን በእሴት ሰንሰለቱ ያለው መጠነኛ ልዩነት እንደለ ሆኖ አብዛኛው የሰው ሃይልን ከማሽን ጋር አጣምሮ የሚጠቀም ነው።

### 3.2.3 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ

**የኢትዮጵያ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንኡስ ዘርፍ ለሀገር ልማት ቀዳሚ ዘርፍ ሆኖ ተለይቶ መንግስት የዘርፉን እድገት በንቃት እየደገፈ ይገኛል።** ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ ቀዳሚ ስትሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ስምንተኛ ደረጃ ትገኛለች። በዚህም ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ እሴት ለመጨመር፣ የስራ እድል ፈጠራ እና የውጪ ንግድ አንቀሳቃሽ ሆኖ ተለይቷል። ኢትዮጵያ ካላት የእንስሳት ሀብት ብዛት የተነሳ የቆዳ ኢንዱስትሪው ቆዳ፣ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች በማምረትና ወደ ውጪ በመላክ ከቀዳሚዎቹ ተርታ ሊመደብ የሚችል ነው። እንዲሁም ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስትመንትን የሚስብ ሰፊና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀይል አላት።

**በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ 32 የቆዳ ፋብሪካዎች፣ አነስተኛና መካከለኛም ጨምሮ ከ200 በላይ የጫማ እና ከ100 በላይ የቆዳ ውጤቶች አምራቾች አሉ።** በዚህም የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንኡስ ዘርፍ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ የምርት እድገት እና ለዘርፉ ያለው አጠቃላይ የምርት ዋጋም ከ2015/16-2019/20 በ19% CAGR ቢጨምርም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ እንደሚያመለክተው በ2010/2021 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ገቢ የቆዳ ዘርፍ የያዘው 1 በመቶ ብቻ ነው። ይህም ከባለፈው ዓመት ከነበረው 2.4% ድርሻ ጋር ሲነፃፀር የ49.4% ቅናሽ ያሳየ ሲሆን ካለፈው ዓመት በፊት ከነበረው 4.4% የቆዳ የውጪ ንግድ ድርሻ የ77 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል።

**ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የቆዳ ምርቶች ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ በመለዋወጣቸው ምክንያት መቀነሱን አሳይቷል።** ከ 2017 እስከ 2021 ድረስ በቆዳው ንዑስ ዘርፍ የገቢ ምርቶች ዋጋ የ 2% ቅናሽ ሲያሳይ በቆዳ ምርት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ፍላጎት መለዋወጥ በምክንያት ከ2020

እስከ 2021 ድረስ በጠቅላላ ከገባው 121 ሚሊዮን ዶላር እቃዎች በ12 በመቶ ሲጨምር የዚህም ዋና ምክንያት የጫማ ንዑስ ዘርፍ ከቻይና እና ታይላንድ የሚገቡ በፕላስቲክ፣ በጨርቅና በሴንቴቲክ የሚሰሩ ጫማዎች በሀገር ውስጥ በሰፊው አለመመረት ነው።

**ኢትዮጵያ በቆዳና ቆዳ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ቀላል የማይባል የእንስሳት ሀብት አላት።** በ2021 ኢትዮጵያ 65 ሚሊዮን የቀንድ ከብቶች፣ 47 ሚሊዮን ፍየሎች እና 38 ሚሊዮን በጎች ነበሯት። ሰፊ የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የቆዳ ኢንዱስትሪው በአጠቃላይ የገበያ ድርሻውን በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ እንዲሁም እንደ ጫማ፣ቆዳ አልባሳት እና እቃዎች ያሉ የተጠናቀቁ የቆዳ ምርቶችን ቀዳሚ አቅራቢ ሆኖ ራሱን ችሎ የመቆየት አቅም አለው። ነገር ግን የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ምርት በአብዛኛው የአገር ውስጥ ፍላጎትን ማሟላት ያልቻለው በዋናነት ከቆዳ ውጭ በሚመረቱት ምርቶች ውስንነት እና የአቅም አጠቃቀም ችግሮች ምክንያት ነው።

**ኢትዮጵያ ከፍተኛ መጠን ያለው የቆዳ ግብአት ከውጭ ታስገባለች።** በቆዳ ማልፋት ሂደት ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉት አብዛኛዎቹ ኬሚካሎች ከውጭ የሚገቡ ናቸው፤ ለጠቅላላው የምርት ዋጋ 43% ያበረክታሉ። ያለቀለት ቆዳ ከውጭ በሚገቡ መለዋወጫዎች እና ሌሎች መካከለኛ ግብዓቶች ላይ ጉልህ የሆነ የውጭ ጥገኝነት አለ። በመሆኑም ከውጭ የሚገቡት ጥሬ ዕቃዎች እና አጠቃላይ የግብዓት ጥሬ ዕቃ ጥምርታ በከፍተኛ ደረጃ በንዑስ ዘርፉ 61% እና 50% ለቆዳ እና የጫማ ምርት በቅደም ተከተል ይውላል።

**ምርት ቢያድግም የቆዳ ኢንዱስትሪው ለሥራ ስምሪት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ውስን ነው።** እ.ኤ.አ. በ 2018 በዘርፉ 53,000 የሚጠጉ ሰዎች ተቀጥረው ነበር፤ ይህም በአምራች ውስጥ ከጠቅላላ የስራ ስምሪት 2 በመቶውን ብቻ ይይዛል። በቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለው የሥራ ስምሪት በ 85 በመቶ በ 2025 እንደሚያድግ የተተነበየ ሲሆን ከ 45,000 በላይ አዳዲስ ቀጥታ ስራዎች እና ከ 57,000 በላይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ስራዎች ተፈጥረዋል።

**ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ቴክኖሎጂን ወደ ሥራው በማስገባት ምርታማነትን፣ ቅልጥፍናን እና የምርት ጥራትንም በማሻሻል ላይ ይገኛል።** እንደ አውቶሜትድ የጨርቃጨርቅ መቁረጫ ማሽኖች በቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ አውቶሜትድ በማድረግ ሂደት ውስጥ የቆዳ አመራረትን እና የውሃ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን ለማሻሻል የውሃ ፍጆታን እና የቆሻሻ ውሃ ፍሳሽን መቀነስ። በዘርፉ የቆዳ ኢንዱስትሪው በተለይም በምርት ወቅት በቴክኖሎጂ አተገባበር ላይ መሻሻል አሳይቷል። በምርት ጊዜ በአብዛኛው በከፊል ቴክኖሎጂዎችን በሚጠቀሙ የመካከለኛ እና ትላልቅ ጫማ እና የቆዳ ምርቶች አምራቾች የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ላይ ይህ በተወሰነ መልኩ ታይቷል።

**በኢትዮጵያ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ተወዳዳሪነት በተለያዩ ሁኔታዎች ማለትም በቴክኒካል ብቃት፣ በጉልበት ምርታማነት እና ጥራቱን የጥሬ ዕቃ ግብአት ላይ የተመሰረተ ነው።** ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በዝቅተኛ የሰው ኃይል ወጪ፣ በአነስተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል ታሪፍ፣ መንግሥት ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችንና ከታክስ ነፃ የማድረግን የመሳሰሉ ማበረታቻዎችን በማቅረብ ተወዳዳሪነት አላት። የንዑስ ዘርፉ የሰው ኃይል ምርታማነት መሻሻል ያሳየ ሲሆን በአገር ውስጥ ገበያ ያልተሠራ ምርትና ገቢን መተካት የሚያበረታታ አቅም አለ።

### 3.2.4 የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ

**የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ንዑስ ዘርፍ የአምራች ዘርፉ የጀርባ አጥንት እና ለበርካታ ኢንዱስትሪዎች ግብአት በማቅረብ የትትስር ሰንሰለቱ ሰፋ ያለ መሰረታዊ ዘርፍ ነዉ።** ኢንደስትሪው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወሳኝ እየሆነ በመምጣቱ ለሌሎች የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ማለትም ጨርቃጨርቅ፣ቆዳ፣ምግብና መጠጥ እንዲሁም የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ግብአቶችን ጨምሮ የኢንዱስትሪዎችን የእርስበርስ ትስስር ሂደት የሚያጠናክር ዘርፍ ነዉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያለው የኬሚካል ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ገና በጅምር ላይ በመሆኑ እያደገ የመጣውን የኢኮኖሚ ፍላጎት ለማሟላት የሃገር ዉስጥ የኬሚካል ግብዓት ፍላጎት ከዉጭ በማስመጣት የሚሸፈን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የሆነ የኬሚካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ፍላጎት አለ።

**የኢትዮጵያ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንኡስ ዘርፍ ሰፊና የተለያዩ የምርት ስብጥሮችን የሚይይዝ ሲሆን** መሰረታዊ ኬሚካል፣ ፐላስቲክ እና ጎማ፣ ወረቀት እና ፐልፐ፣ እንጨትና የቤት እቃዎች፣ የመስታወት እና የመስታወት ዉጤቶችን ጨምሮ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን ያቀፈና በስሩ የተለያዩ ንዑስ ዘርፎችን ያካተተ ነው። በኬሚካል ንኡስ ዘርፍ እንደ ሳሙና እና መሰረታዊ ኬሚካሎች ሰልፈሪክ አሲድ፣ ካስቲክ ሶዳ እና ክሎሪን ጨምሮ አንዳንድ ምርቶች ቢመረቱም የኢትዮጵያ ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ዘርፍ በአንፃራዊ መልኩ ያልዳበረ በመሆኑ ለግብአትነትም ሆነ ያለቀላቸዉ የፍጆታ ምርቶች ከውጭ በማስገባት ከፍተኛ ጥገኛ ነው።

**የዘርፉ ዉጤቶች ለሌሎች ንዑስ ዘርፍ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት እንደ ዋና ጥሬዕቃ የሚያገልግሉ ግብዓቶች ከመሆናቸዉ ጋር ተያይዞ፣ ከውጭ የሚገቡ የንዑስ ዘርፉ ዉጤቶች ከ2017 እስከ 2021 ባለው የ 3በመቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ጭማሪ አሳይቷል።** እ.ኤ.አ. በ2021 ኢትዮጵያ ከውጪ ካስገባቻቸዉ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ምርቶች አብዛኛዎቹ የፐላስቲክ እና የፐላስቲክ እቃዎች፣ ማዳበሪያዎች፣ ልዩ ልዩ ኬሚካሎች እና ጎማዎች ከሌሎች በርካታ ምርቶች ማለትም ከወረቀትና ፐልፐ፣ ከመስታዎት፣ ከእንጨት እና የቤት እቃዎች መካከል በብዛት ወደ ሃገር ዉስጥ የገቡ

ምርቶች ናቸዉ፡ በዚህም በሀገሪቱ ዉስን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ ከ2.3 ቢሊዮን ዶላር በላይ ጭማሪ ወደ ሀገር ውስጥ ምርቶችን ለማስገባት ወጪ አድርጋለች።

**የኬሚካል እና የኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪዎች በ2014/15 ከነበረበት 522 በ23% በማደግ በ2019/20 ወደ 643 ኢንዱስትሪዎች ከፍ ብሏል።** በዚህም ከውጭ የሚገባው የንዑስ ዘርፉ የጥሬ ዕቃ ድርሻ ጨምሯል።ለምሳሌ እንደ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች ሁሉ በንዑስ ዘርፉ ከዉጪ የሚገባዉ ግብዓት ወጪ አጠቃላይ ጥቅም ላይ ለዋለዉ ግብዓት ወጪ ሲነፃፃር በ2015/16 ከነበረበት 49 በመቶ በ2019/20 ወደ 58 በመቶ ከፍ ብሏል። እ.ኤ.አ. በ2019/20 የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ምርት አስገኝቷል። 13.89 ቢሊየን ብር ለንዑስ ዘርፉ በማቅረብ ከፍተኛውን የገቢ መጠን ያስመዘገበው የፕላስቲክ እና ጎማ ኢንዱስትሪ ሲሆን፣ 11.58 ቢሊዮን ኬሚካል፣ እንጨትና ፈርኒቸር 6.56 ቢሊየን ብር፣ የጥራጥሬና ወረቀት 6.54 ቢሊየን ብር፣ የመስታወት እና የመስታወት ምርቶች 2.24 ቢሊዮን ብር ገቢ እንደቅደም ተከተላቸዉ አሰገኝተዋል። እንደ አለም ባንክ መረጃ ኬሚካል (በአምራች ዘርፍ ውስጥ ያለዉ እሴት ጭማሪ በመቶኛ)- በኢትዮጵያ በ2006 ከነበረበት 5 በመቶ በ2015 ወደ 11 በመቶ ከፍ በማለት በ120% ጨምሯል።የኢትዮጵያ የኬሚካል ኢንዱስትሪ በተለይም ደረቅ ሳሙና፣ ፈሳሽ ሳሙና እና ቀለም ከፍተኛ የሰዉ ጉልበት የመጠቀም ባህሪ ያለዉ በመሆኑ ለስኬታማነት የዋጋ ተወዳዳሪነት ወሳኝ አለዉ። የኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የደመወዝ ስትራክቸር እና በቀላሉ ሊሰለጥና የሚችል የሰው ሃይል ሀገሪቱን ከሌሎች ብዙ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት የተሻለ ጠቀሜታ ሰጥቷታል። በዚህም የስራ ዕድል ፈጠራ በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ንዑስ ዘርፍ በ60% ማለትም በ2015/16 ከነበረዉ 64,000 በ 2019/20 ወደ 103,430 አድጓል።በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ዘርፍ የአገር ውስጥ ምርትና የስራ ቅጥር ዕድገት ቢያስመዘግብም፣ አብዛኞቹ አምራቾች አሁንም ዝቅተኛ የማምረት አቅም አጠቃቀም ችግር አለባቸው። ከዚህ ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እቃዎች በሚያመርቱ 52 ፋብሪካዎች ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው አማካይ የአቅም አጠቃቀም 50% ሲሆን የወረቀት ምርት ዝቅተኛው 16 በመቶ እና የእንጨትና የቤት እቃዎች ከፍተኛ የአጠቃቀም መጠን 76% ደርሷል።

**ኢትዮጵያ የተረጋገጠ የጋዝ ክምችት ያላት በመሆኑ ፔትሮ ኬሚካሎችን የማምረት አቅም አላት ፣ይህም ገቢ ምርትን ለመተካትና ኢንዱስትሪዎችን ለመደገፍ ያስችላታል፡፡** ነገር ግን ሀገሪቱ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ምርቶች ለመሰረታዊ ነዳጂ ፍጆታና ኬሚካሎች ላይ ጥገኛ በመሆኗ በግብዓት አቅርቦት በኩልና ደካማ በሆኑ ኢንዱስትሪዎች ላይ የፊትና የኋልዮሽ ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል። በመጨረሻም ኬሚካሎች በባህሪያቸዉ ለሌሎች ዘርፎች ወሳኝ ግብዓት በመሆናቸው እና ከውጭ

የሚገቡ ምርቶችን ሙሉ በሙሉ ለመተካት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ስለሚያስፈልጋቸው ለመሠረታዊ ኬሚካሎች ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በፕላስቲክ እና የጎማ ኢንዱስትሪ ውስጥ አንዳንድ ምርቶች እንደ የፕላስቲክ ሳህኖችና ጥፍጣፎች, የፕላስቲክ ቱቦዎችና ፊቲንግ፣ቮልካኒዝድ ረበር እና ፎም ፍራሾች የምርት ቴክኖሎጂው በአገር ውስጥ ስለሚገኝ በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ሊተኩ ይችላሉ።ለብዙ ዘርፎች ወሳኝ ግብአት የሆነውና የተራቀቀ ቴክኖሎጂ እና ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ካፒታል የሚያስፈልገው ፖሊአስቴል ከውጭ አገር የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት የረዥም ጊዜ ፕሮጀክት ያደርገዋል ነገር ግን የፍጆታ ዕቃዎች ለሚያመርቱ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች ያለው ጠቀሜታ ቅድሚያ እንዲያዝ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ጎማዎች እና ጥርሳቸዉ የሚቀየሩ ጎማዎች ነባር ኢንዱስትሪዎችንና የጎማ ዛፍ ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም በአጭር ጊዜ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት አቅም አላቸው።

**በሦስተኛ ደረጃ በወረቀት እና በፐልፕ ኢንዱስትሪ ውስጥ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ዋና ዋና ምርቶች መካከል የወረቀት ማሸጊያ/ካርቶን ሲሆን ይህም ሌሎች ዘርፎችን የሚደግፍ ቁልፍ ረዳት ምርት ቢሆንም አሁን ላይ ጥሬ ዕቃዎች በአገር ውስጥ ስለማይገኙ/ስለማይመረቱ እና ቴክኖሎጂው ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቅ በመሆኑ አዲስ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ነው።** ሌላው ምርት የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ ፓድ፣ ዳይፐር እና የፊት መጥረጊያ/ዋይፐር ሲሆን ይህም ከፍተኛ ፍላጎት ያለው እና በመጠኑም ቢሆን ጥሬ እቃዎች እና አምራቾች ያሉ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊተኩ ይችላሉ። በመጨረሻም የእንጨት፣ የቤትና ቢሮ እቃዎች ኢንዱስትሪው ባለዉ ተወዳዳሪነት ገቢ ምርትን ለመተካት ለማድረግ ቅድሚያ ተሰጥቶታል። ለምርት የሚያስፈልጉት ሀብቶች በአካባቢው የሚገኙ በመሆኑ ነባር ኢንዱስትሪዎችን እና ቀጣይ ፕሮጀክቶችን በመጠቀም በአጭር ጊዜ ዉስጥ መተካት ይቻላል።

### 3.2.5 ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ

**የኢትዮጵያ ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን በሁለት ሰፊ የኢንዱስትሪ ምድቦች ሊገለፅ ይችላል።** የመጀመሪያው የመሰረታዊ ብረታብረት ምርቶችን የሚያመርቱት ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ የብረት ማዕድንን በመጠቀም እንዲሁም የወዳደቁ ብረቶችን በማቅለጥ ምርት የሚያመርቱ ሲሆን ሁለተኛው ምድብ ደግሞ የኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ሲሆኑ የመሰረታዊ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ውጤቶች እንደግብዓት በመጠቀም እንደ ማሽነሪዎች፣ የትራንስፖርት መሣሪያዎች እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የሚያመርቱ ናቸው። ይህ ንዑስ ዘርፍ ለአገሪቱ ከሥራ ዕድል ፈጠራ ባለፈ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

**ኢትዮጵያ የአገር ውስጥ ፍላጎቷን ለማሟላት ከውጭ በሚገቡ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ምርቶች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጥገኛ ነች።** በዋናነት ማሽነሪዎች፣ የሞተር ተሽከርካሪዎች እና የኤሌትሪክ መሳሪያዎች በብዛት ከውጭ ይገባሉ። ኢትዮጵያ በ2021 ብቻ ከ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ስታስገባ የንዑስ ዘርፉ ምርቶችን ለማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተጠቅሟል ። በመሆኑም ይህን ከፍተኛ ፍላጎት ለመቅረፍ በዘርፉ ልማት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራትና ገቢ ምርትን በአገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችሉ ዘዴዎችን መቅረፅ ተገቢ ነው።

**ከውጭ የሚገቡ የማሽነሪዎች እና የሜካኒካል እቃዎች እና የተሽከርካሪዎች ፍላጎት በአለም አቀፍ የገበያ ሁኔታ ምክንያት በየዓመቱ ይለዋወጣል ነገር ግን በአጠቃላይ የዘርፉ ምርቶች በሀገር ውስጥ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።** እነዚህን ምርቶች ወደ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ቁጥር የሚልኩ ሀገራት ቻይና እና ጃፓን ናቸው። ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግስት በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ በእነዚህ ዘርፎች ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል።

**በኢትዮጵያ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ውጤቶችን የማምረት ሒደት በውስን የማምረት አቅምና የቴክኖሎጂ ውስንነት ምክንያት ገና ጅምር በሚባል ደረጃ ላይ ነው።** የሀገሪቱ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ዘርፍ በዋናነት የሚያተኩረው በመሠረታዊ የብረታ ብረትና ብረት ውጤቶች፣ የግንባታ እቃዎች እና የመሠረታዊ ማሽነሪዎች ማምረት ላይ ነው። ከመሰረታዊ ማሽነሪዎች ውጭ የሆነ ማሽነሪና ተያያዥ ዕቃዎች ግን በአብዛኛው ከውጭ የሚገባ ነው። ቢሆንም ባለፉት አምስት አመታት ምርቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል።የማሽነሪና ተያያዥ ምርቶች በቀጣይ ከመሰረታዊ በብረታብረት ምርቶች ጋር የኋሊዮሽ ትስስር የመፍጠር ዓቅም አለው። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሞተር ተሽከርካሪ፣ ተጎታች እና ከፊል ተጎታች አምራች ኢንዱስትሪ በመገጣጠም ስራ አተኩሮ እየሰራ የሚገኝና ገቢ ምርትን እየተካ የሚገኝ ሲሆን ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ ገበያው እያደገ በመሆኑ ወደፊትም መልካም ዕድል አለው።ከውጭ የሚገቡ ምርቶችም የመቀነስ አዘማሚያ አሳይተዋል።

**የኢትዮጵያ መንግስት ተኪ ምርትን የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ቢያበረታታም የኢንዱስትሪዎቹ ውጤታማነት ግን ውስን ነው።** ንዑስ ዘርፉ በከፍተኛ ደረጃ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ በማስገባት ላይ ጥገኛ በመሆኑ ገቢ ምርትን መተካትንና ኣቅም አጠቃቀሙን ዝቅተኛ አድርጎታል።

**የብረታ ብረት ውጤቶች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች እና ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት መጠን እየጨመረ መጥቷል።** እ.ኤ.አ. በ2019/20፣ ፋብሪኬትድ የሆኑ ብረቶች፣

ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ተሳቢዎች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡበት መጠን 46%፣ 84% እና 65% ነበር። ይህ ከመሠረታዊ የብረት ምርት ጋር ያለውን ደካማ የኋልዮሽ ትስስር ያሳያል። መሠረታዊው ብረትን ለማምረት የሚያስፈልግ የግብዓት መጠን 72% የሚጠጋ ከውጭ የሚገባ ሲሆን ይህም የብረት ማዕድን ላይ በትኩረት መሰራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል።

**በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ የተወሰነ ዕድገት ቢኖርም በስራ ዕድል ፈጠራና በአቅም አጠቃቀም በኩል በተነጻጻሪነት አነስተኛ አፈፃፀም ያለው ንዑስ ዘርፍ ነው።** በተወሰኑ የዘርፉ አምራቾች ላይ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት አማካኝ የአቅም አጠቃቀም 27% መሆኑ ታይቷል።

**የኢትዮጵያ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ ኋላቀር እና ዘመናዊ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም ኦቶሜሽንን የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት ይጠቀማል።** የረቀቁ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎች በንዑስ ዘርፉ ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው። ንዑስ ዘርፉ በባህሪው የተራቀቁ የምርት ቴክኖሎጂዎችን የሚፈልግ ቢሆንም አሁንም ቢሆን በአብዛኛው የሚጠቀመው ኋላ ቀር በሆኑ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ነው። ስለሆነም ይህንን የቴክኖሎጂ ክፍተት ለመሙላት ጥረት ማድረግ ይጠበቃል።

**ከውጪ በሚገቡ ጥሬ-ዕቃዎች ጥገኛ መሆን እና እንዲሁም በአገር ውስጥ ያለ የማምረት ዓቅምን በሚገባ አለመጠቀም ያሉ ተግዳሮቶች እንደ ሌላው ዘርፍ በተመሳሳይ በኢትዮጵያ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ ላይ ይስተዋላሉ።** የዘርፉን እምቅ አቅም ለመጠቀም እና ከውጭ የሚገቡ የጥሬ ዕቃና መለዋወጫ ጥገኝነቶችን ለመቀነስ ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትስስርን መፍጠር ያስፈልጋል። እንዲሁም ያላደጉ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር በግብዓት አቅራቢነት ማሳተፍ ያስፈልጋል። በሀገር ውስጥ ማምረትን፣ ፈጠራን እና የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንትም በትኩረት ከተሰራ የዘርፉን እምቅ አቅም ሙሉ በሙሉ እውን ለማድረግ፣ የንግድ ሚዛን መዛባትን ለመቀነስ እና የአምራች ዘርፉ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ያለውን አስተዋፅዖ ያሻሽላል።

**ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት ባላቸው ተወዳዳሪነት/አቅም መሰረት በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ ስር ካሉ የብረታ ብረት፣ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች 18 (አስራ ስምንት) ምርቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸዋል።** በተፈጠረው የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ውስጥ በአጭር፣በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የመተካት አቅም ያላቸው ምርቶች ተለይተዋል።

### 3.2.6 ስትራቴጂያዊ ምርቶች አመራረጥ እና ዝርዝር

**ከፍተኛ የመተካት አቅም ያላቸው የምርት ምድቦችን ለመለየት የመረጃ አሰባሰብ፣ የሰነድ ግምገማ፣ የመንግስት ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ የባለሙያዎች ምክክር እና የግሉ ዘርፍ ውይይቶች ተካሂደዋል።** አንዳንድ ምርቶች በአጭር ጊዜ የመተካት አቅማቸው የተመረጡ ሲሆኑ ሌሎች ወሳኝ ምርቶች ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ ያለው ተወዳዳሪነታቸው ውስን ሊሆን ቢችልም ለተለያዩ የእሴት ሰንሰለቶች በግብአትነት ሊያበረክቱት ከሚችለው አስተዋፅዖ በመነሳት ቅድሚያ ተሰጥቷቸዋል።

**ለሀገሪቱ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶችን መለየት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ የእነዚህ ምርቶች መገኘት፣ አመራረት እና ከአጠቃላይ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ጋር መጣጣም በኢኮኖሚው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ማጤን አስፈላጊ ነው።** እነዚህ ስትራቴጅያዊ ምርቶች ተዘጋጅተው ተደራሽ እንዲሆኑ መንግሥት የምርት እድገታቸውንና የአሴት ሰንሰለት እድገታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ በእነዚህ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ኢንቬስትመንትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን መተግበር ወይም የምርት ቅልጥፍናን እና ጥራትን ለማሻሻል ለምርምር እና ልማት የገንዘብ ድጋፍ መስጠትን ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪም ስትራቴጂካዊ ምርቶችን መለየት እንደ ሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሊለያዩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአንዳንድ አገሮች እንደ ነዳጅ ያሉ ምርቶች ቁልፍ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፣ ሌሎች ደግሞ የግብርና ምርቶች ወይም የምድር ብረቶች ይበልጥ አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሌሎች ንዑስ ዘርፎችና የእሴት ሰንሰለቶች እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ፣ ያልተነካ እምቅ አቅም ያላቸው እና ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙና የሀገርን ብሄራዊ ደህንነት የሚያረጋግጡ ምርቶች ስትራቴጅያዊ ምርቶች ተብለው ተወስነዋል።

**የስትራቴጂያዊ ምርቶች አመረራጥ ስልት የእያንዳንዱን ምርት የእሴት ሰንሰለት የዕድገት ደረጃ ያማከለ ነው።** ይህም ማለት የእያንዳንዱን መርት ወቅታዊ የምርት ደረጃ፣ የግብአት አቅርቦት፣ የማምረት አቅም አጠቃቀም፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማት ብቃት፣ የገበያ ትስስር እና መጋቢ ኢንዱስትሪዎች መኖራቸውን ያካትታል። በዚህም መሰረት ስንዴ፣ ስኳር፣ የምግብ ዘይት፣ ጥጥ፣ ፕልፕ፣ ጎማ፣ መሰረታዊ ኬሚካሎች፣ ፔትሮኬሚካሎች፣ እና መሰረታዊ ብረታብረቶች እንደ ስትራቴጂያዊ ምርቶች ተመርጠዋል።

**የእነዚህን ስትራቴጂክ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ማጎልበት ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ እድገትን እውን የሚያደርጉ መካከለኛ እና ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ ምርቶችን አቅርቦት ለማሳደግ ያስችላል።** በማንኛውም ኤክስፖርት እና የተኪ ምርት ስራቴጂዎች የእነዚህን ምርቶች ልዩ ተግዳሮቶችን

መገንዘብ፣ ለውጥ የሚያመጡ ኢኒሼቲቮችን ተግባራዊ ማድረግና እውነተኛ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን መክፈት ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግም ለምርቶቹ እሴት ሰንሰለት ትኩረት የሚሰጥ አቀራረብ መውሰድና ከጫፍ እስከ ጫፍ ያላቸውን አቀነባበርን መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህም የእነዚህን ምርቶች የግብዐት ሃብት መሰረት በበቂ ሁኔታ መገምገም፣ የሀገር ውስጥ ማቀነባበሪያ እና የማምረት አቅምን ማዳበር፣ የተስተካከለ የድህረ-ምርት ሂደትና የገበያ ትስስር መዘርጋትን ያጠቃልላል።የኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ሆልዲንግስ ይዞታዎች፣ የግብርና ሚኒስቴር የስንዴና የምግብ ዘይት ውጥኖች እና የማዕድን ሚኒስቴር የሀገር አቀፍ የግብዓት ካርታ ስራዎችን በመጠቀም በእያንዳንዱ ስትራቴጂካዊ ምርት ላይ ያሉ ልዩ ማነቆዎችንና ድክመቶችን ለመፍታት የታለሙ ፕሮጀክቶችን እና ኢኒሼቲቮችን በማዘጋጀት በትኩረት መስራት ይኖርበታል።

# 4 ክፍል አራት

## 4.1 የንዑስ ዘርፍ ተግዳሮቶች

### 4.1.1 የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ

**በቂ ያልሆነ የኳልዮሽ እና ፊትዮሽ የጥሬ ዕቃና የገበያ ትስስር አለመኖር፡** በአገር ውስጥ የሚመረቱ የምግብ እና የመጠጥ ምርቶች በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን ውስንነት መኖር፣ የምርት ዕሴት ሰንሰለት ቅልጥፍና ቀጣይነት አለመኖር፣የካፒታል ኪሳራ ማሳደር፣ የደንበኞች ተለዋዋጭ መሆን፣ ተፈላጊ ምርቶች በመጠንም ሆነ በጥራት ተለዋዋጭ መሆን፣ከደረጃ በታች የሆነ የግብርና ጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ ወዘተ። ምንም እንኳን የግብርና ግብአቶች ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም አምራቾች (ፕሮሰሰሮች) በአማካይ 18% - 40% ከአቅም በታች ይሰራሉ። የግብርናው ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ ወደ ውጭ የሚላከው ምርት ብቻ ሳይሆን የአገር ውስጥ ገበያና የአገር ውስጥ አምራቾችን ማቅረብ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል።

**አስተማማኝ ያልሆነ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፡** በቂ የሆነ የሃይል አቅርቦት አለመኖር፣የኤሌክትሪክ የኃይል መዋዠቅና የትራንስፎርመር ችግር፣ የትራንስፖርት እና የቀዝቃዛ ሰንሰለት ፋሲሊቲዎች (cold-chain facilities) በምርታማነት እና በጥራት ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ ይገኛሉ። የኢንዱስትሪው አማካይ የኃይል ፍላጎት ከ 25 ኪሎ ዋት እስከ 5000 ኪሎ ዋት ይደርሳል። ሌሎች የሰራተኛ ክፍያ፣ የጄነሬተርና ናፍታ ወጪ፣ የጥገና ወጪዎች፣ የመሳሪያዎች ወጪዎች፣ የመጠባበቂያ ወጪዎች፣ የጽዳት እና የማሽነሪ ማስተካከያ ወጪዎች፣ በሂደት ላይ ያሉ እቃዎች እና የምርት ብክነት በአቅርቦት እጥረት ምክንያት ኢንዱስትሪዎቹ ለተጨማሪ ወጪዎችን መጋለጥ፣ በዚህም ኢንዱስትሪዎች በተወዳዳሪነት ለመቀጠል እና ሥራቸውን ለማስቀጠል መቸገራቸው በኢንዱስትሪዎች ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ ያሉት ዋና ዋና ማነቆዎች ናቸው።

**በቂ የማሽጊያ ዕቃዎች አቅርቦት አለመኖር፡** የግብርና ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ምርቶች ተወዳዳሪነት የማሸጊያው ጥራት 25% አስተዋፅኦ ያደርጋል። በኢትዮጵያ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ አይነት የማሸጊያ እቃዎች እያቀረቡ ይገኛሉ። ከ25-30% ኢትዮጵያ የምታመርት ቢሆንም ከሀገሪቱ የማሸጊያ ፍላጎት አንፃር ማሸግ አሁንም በዘርፉ ተወዳዳሪነት ላይ ቁልፍ ትኩረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። አብዛኛዎቹ መካከለኛ እና ትላልቅ ማቀነባበሪያ አምራች ፋብሪካዎች የማሸጊያ ቁሳቁሶችን ለማምረት ጎን ለጎን ማሸጊያ መሳሪያዎች አሏቸው። ነገር ግን ማሸጊያዎችን ለመሥራት ሁሉም ግብአቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መሆናቸው እና የውጪ ምንዛሪ አቅርቦትን የሚጠይቁ በመሆናቸው ከውጭ የሚገቡ ግብአቶችን በመተካት በዘርፉ ላይ የሚታዩ ማነቆዎችን መፍታት ያስፈልጋል።

**የሰለጠነ የሰው ሃይል ማነስ፡** የሰው ኃይል ምርታማነት አናሳ መሆን፣አነስተኛ የክፍያ ስርዓት መኖር የስራ አፈጻጸም ውስንነት መኖር፣ ከስራ መቅረት እና ደካማ የስራ ባህል መኖር፣ ሰራተኞጭ የተግባር ክህሎት ማነስ አምራቾች የሰለጡኑ ሠራተኞችን ለማግኘት ከሚገጥሟቸው ፈተናዎች ውስጥ ይገኛሉ። አምራቾች ምርታማነትን ለማሳደግ ያላቸውን ውሱን ሃብት በስራ ላይ ለከባድ እና ለስላሳ የክህሎት ስልጠናዎች ኢንቨስት ያደርጋሉ፣ነገር ግን በስራ ገበያው ስልታዊ ባህሪ ምክንያት ያልተቋረጠ ፈታኝ ሁኔታ፣ እና ይህ የሚቻለው ይህን ለማድረግ የሚያስችል አቅም ላላቸው ትላልቅ አምራቾች ብቻ ነው።

**የስራ ማስኬጃ ፋይናንስ እጥረት፡** በግብርና ማቀነባበር ስራ ላይ የተሰማሩ አምራቾች የስራ ካፒታልን በማግኘት ረገድ ተግዳሮቶች አሉባቸው። የፋይናንስ አቅርቦት በዘላቂነት አለመኖር እና የዋስትና መስፈርቶችን ማሟላት አለመቻል የብድር አቅርቦትን ይገድባል። በተጨማሪም የውጭ ምንዛሪ ክምችት እጥረት መኖር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ግብዓቶች እና ማሽኒያዎችን የሚገድቡ የገንዘብ ቁጥጥሮችን ያስከትላል፣ ወጪን ይጨምራል እና የተወዳዳሪነት አቅምን ይቀንሳል።

**ጠንካራ የገበያ ስርዓት እና የገበያ መረጋጋት አለመኖር፡** በተቋማት መካከል ደካማ የመረጃ እና የቁጥጥር ስርዓቶች ውስንነት መኖር፣ የሀገር ውስጥ ምርቶች የሚወጡና የሚዘጋጁ ደረጃዎችን በአግባቡ ተግብሮ በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነታቸውን ማስፋት አለመቻል ይታያል። የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት ሀገራዊ ደረጃዎችን የማውጣት ኃላፊነት ቢኖረውም የተቀረጹትን ደረጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ በአምራቹም ሆነ በአስተግባሪው በኩል የሚታዩ ውስንነቶች/ክፍተቶች አሉ። እነዚህን ተግዳሮቶች ለመፍታት እና የአግሮ ፕሮሰሲንግ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማስፋት ደረጃቸውን የጠበቁ ላቦራቶሪዎችን በማሟላት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ገበያ ተደራሽነትን ማስፋትና ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል ይጠይቃል፣ ጎን ለጎንም የተረጋጋ የገበያ አቅርቦትን ትስስር መፍጠር ይቻላል።

**የግብርና የታሪፍ ከለላ ስርዓት ወጥ አለመሆን፡** ለባለሀብቶች እና ለአምራቾች የተለያዩ የግብር ማበረታቻዎች አሉ ነገር ግን በንግዶች መካከል የግብር ግዴታዎችን እና መብቶችን በተመለከተ እኩል ግንዛቤ አለመኖሩ። ፍትሃዊነት እና ወጥነት የጎደለው ውድድር መኖር፣ የተጨማሪ እሴት ግብር ስርዓት በአምራቾች ላይ መኖር፣ የተርን ኦቨር ግብር ፍትሐዊ አለመሆን፣ አምራቾች የሚያነሷቸው ተጠቃሽ ዋነቆዎች ናቸው።

### 4.1.2 የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ

**በእሴት ሰንሰለቱ ኢንቨስትመንት ላይ የሚስተዋል አለመጣጣም** - በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ማምረቻ እሴት ሰንሰለት ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ የኢንቨስትመንት አለመጣጣም በጉልህ ይታይል፡፡ በዚህም ምክንያት የአልባሳት ፋብሪካዎች የተጠናቀቀ ጨርቅና ተለጣጣፊ ግብዓቶችን በውጭ ምንዛሬ እንዲያስገቡ ይገደዳሉ፡፡ ይህ አካሄድ ከላይ ያለው የእሴት ሰንሰለት (ክርና ጨርቅ) አምራቹ እንዳያድግ ከማድረጉም በላይ የውጭ ምንዛሬ ላይ ጫና እየፈጠረ የሚሄድ ሰለሆነ፤ የኢንቨስትመንት መጣጣሙ ለጨርቃጨርቁም ለአልባሳቱም እድገት ወሳኝ ነው፡፡

**የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር** - በተወሰነ ደረጃ በሀገር ወስጥ ከሚመረተው የጥጥ ምርት ውጭ ከሞላ ጎደል አብዛኛው የጨርቃጨረቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፉ ጥሬ ዕቃ የሚመጣው ከውጭ ነው፡፡ ከጥጥ አኳያም ቢሆን ካለን የማምረት አቅም ጥቅም ላይ የዋለው ከ3% ያነሰ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሰው ሰራሽ ጭረት የተሰሩ ልብሶች፣ የአልባሳት ተለጣጣፊዎች፣ ቀለማቀለሞች፣ኬሚካሎች ወዘተ በግብዓትነት ስለሚያገለግሉ ወደ ውጭ ከምንልከው ይልቅ የምናሰገባው ይበልጣል፡፡ እንደምሳሌ ብንወስድ ባለፉት አምሰት ዓመታት (ከ2017-2022 እ.አ.አ) አማካይ የገቢ ምርቶች ከወጭ ምርቶች ሲታይ 300 ፐርሰንት ብልጫ ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ጥሬ ዕቃውን ከጅምሩ በማስገባት እሴት እየተጨመረበት ከልተሸጠ በሰተቀር ያለቀለት ግብዓት ወይም የተጠናቀቀ ምርት በማምጣት እመርታዊ ለወጥ ማስመዝገብ ያዳግታል፡፡

**የክህሎት ክፍተት መኖሩ** - ምንም እንኳን በርካታ ዩኒቨርስቲዎችና ማሰልጠኛ ተቋማት በዘርፉ ውስጥ ቢኖሩም፤ ተቋማቱ የሚሰጡት የትምህርትና የስልጠና ጥራት ከኢንዱሰተሪው ፍላጎት ጋር የማይጣጣምና የፋብሪካዎችን ችግር ከስር መሰረቱ መፍታት የማይችል ነው፡፡ በተለይ በኢንሰዱስተሪውና በስልጠና ተቋማቱ ያለው ትስሰር የላላ መሆኑ ችግሮችን ተቀራረቦ መፈታት ላይ አዳጋች አድርጎታል፡፡

**የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተት** - የሚመረቱ ምርቶች በጥራትና በብዛት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ዓለም እየተጠቀመ ያለውን ቴክኖሎጂ መጠቀምና ለውጥ ማምጣት አማራጫ የለውም፡፡ ሆኖም በዚህ ረገድ መንግስት የተለየ ደጋፍ አለማድረጉ (ከአዳዲስ ኢንቨስተመንቶች በስተቀር) ፋብሪካዎችን በመለዋወጫና በቴክኖጂ ማዘማን የተለየ ዘላቂ የድጋፍ ማዕቀፍ አለማዘጋጀቱ በርካታ ፋብሪካዎች ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አድረጓል፡፡

**ኋላ ቀር የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት** - ከካቢኔ ጀምሮ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት አስፈፃሚ የዘመነ የስራ አሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፤ ይህ ሁኔታ በተለያዩ ኢንቨስተሮች ላይ ከብድር

አቅርቦት፣ ከቦታ ሊዝ፣ ከማበረታቻ አፈፃፀም፣ ከጉምሩክ አገለግሎት፣ ከኃይል አቅርቦት ወዘተ አኳያ የተንዛዛና የተተበተበ የአገልገሎት አሰጣጥ እንዲፈጠር በር የሚከፈት ነው፡፡

**ለአምራቾች የሚሰጡ ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች አሰጣጥ ትኩረት አልባና አፈፃፀማቸው የማይለኩ መሆኑ** - ደካማ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር በአምራች ኢንዱስትሪው ላይ እያመጣ ያለው ጫና፣ ለሀገር ውስጥ አምራቹ የተለየ ትኩረትና ማበረታቻ አለማግኘቱ፣ ህዝቡን የሀገር ውስጥ ምርት እንዲጠቀም የተለየ ሰራ አለመሰራቱ ወዘተ የዘርፉ አበይት ሌሎች ተጨማሪ ችግሮች ናቸው፡፡

### 4.1.3 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ

**በአያያዝ ጉድለት እና አሰባሰብ ሂደት የኢትዮጵያ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት መጓደል ይደርስበታል።** ለቆዳ ፋብሪካው ከመድረሱ በፊት የእንስሳትን ተገቢ ያልሆነ አያያዝ፣ በእርድ ወቅት የቆዳና ሌጦ በአግባቡ አለመያዙ የምርት ጥራት መጓደል ምክንያት ናቸው። በዚህም ምክንያት ዝቅተኛ የመሰብሰቢያ ዋጋ እንዲኖረው ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ያለቀለት ቆዳ ጥራት መጓደል እና በጫማ እና በቆዳ እቃዎች እጥረት ምክንያት የምርት ግብዓቶች እጥረት ያስከትላል።

**በአገር ውስጥ የሚመረቱ ኬሚካሎች አቅርቦት ውስንነት የምርት ወጪን ከመጨመር በተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ ጥገኝነቶችን ያስከትላል።** የቆዳ ኢንዱስትሪው ኬሚካልን የሚጨምር በመሆኑ ከ95% በላይ የቆዳ ማቀነባበሪያ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ይገባሉ። ይህ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለው ጥገኝነት ወደ ከፍተኛ ወጪ፣ የአክሲዮን እና የሥራ ካፒታል አቅም እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት አስፈላጊነትን ያስከትላል። የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ማሽቆልቆሉ በዘላቂ የቆዳ ምርት፣ ጥራት እና ያለቀለት የቆዳ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው።

**ቆዳና ሌጦ ለማምረት የቴክኖሎጂ እና ክህሎት ማነስ የአገር ውስጥ የቆዳ ፋብሪካዎችን የምርት እና የምርት ጥራት ይገድባል።** ያለቀለት ቆዳ አይነት እና ጥራት የገበያ ፍላጎትን የሚገድብ፣የምርቶቹን ዋጋ የሚቀንስ እና የመላኪያ ጊዜን የሚጎዳ መሳሪያ እና ክህሎት እጥረት አለ። ይህ የምርቶችን ጥራት እና ልዩነት እና ለገዢዎች ሊሰጥ የሚችለውን ክልል ይገድባል። ደካማ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እና በአገር ውስጥ ኩባንያዎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደካማ በመሆኑ፣ የአገር ውስጥ የቆዳና የቆዳ ምርቶች አቅራቢዎች ተወዳዳሪ ንዳሆኑ ያደርጋል።

**ፋይናንስ እና ኢንቨስትመንት በዋጋ ሰንሰለቱ ውስጥ የተገደቡ አምራቾች እና ለጫማ አምራቾች መለዋወጫዎች እና አካላት አቅርቦት ሁለት ተግዳሮቶች ናቸው።** ለሀገር ውስጥ ማምረቻዎች የሚስቡ ዲዛይኖች እና የቴክኖሎጂ እና ግብዓቶች እጥረት እና ከውጪ ከሚገቡ ጫማዎች ጋር መወዳደር

ባለመቻሉ የተራቀቀ እና ፈጣን ለውጥ ካለው የጫማ እና የቆዳ እቃዎች ዲዛይን ጋር መወዳደር አስቸጋሪ ነው። ውስን በሆኑ የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ክፍሎች አመራረት በመመራት ኩባንያዎች በዘመናዊ ዲዛይኖች ከማምረት ወደ ኋላ ቀርተዋል። አነስተኛ አቅም ያለው አጠቃቀም፣ ደካማ ቴክኖሎጂ እና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ውስን በመሆኑ አምራቾች ዝቅተኛ የምርት መጠን ያመርታሉ።

**በአገር ውስጥ የሚመረቱ ጫማዎች የሚታወቁት ጥቂት ኩባንያዎች ብቻ ነው።** 90% አምራቾች የምርት ስም፣ የግብይት ወይም የሽያጭ ስልቶችን በአካባቢያዊ ጎራ ውስጥ ስላልተገበሩ ጠንካራ እና ዘላቂ ግንኙነቶችን እያሳደጉ አይደሉም። አብዛኛዎቹ ኩባንያዎች የግብይት መመሪያዎች ስለሌላቸው ዘመናዊ የግብይት ስልቶችን አይከተሉም። ይህም የሀገር ውስጥ ምርቶች የገበያ ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ይህም ህብረተሰቡ ለሀገር ውስጥ ምርቶች አሉታዊ አመለካከት እንዲኖረው አድርጓል። የሀገር ውስጥ ገበያዎች በጣም የተጋለጡ እና "ማስመጣት ይሻላል" የሚለውን ትረካ የለመዱ ናቸው። ይህም የኮንትሮባንድ እና መደበኛ ያልሆኑ ገበያዎችን በማጠናከር ሸማቾች የሚመርጧቸውን ብራንዶች በዝቅተኛ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን የሚያዘባ ነው።

**የቆዳና የቆዳ ምርቶች አምራቾች በተበታተኑበት የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ የተበጣጠሱ ስብስቦች እና ማህበራት ለአገር ውስጥ አምራቾች ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ሚዛን፣ ትስስር እና የዋጋ ፈተናዎች ያስከትላሉ።** ነገር ግን አምራቾቹ የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን በዕቅድ ማከናወን አልቻሉም። ይህ በበርካታ ምክንያቶች የተነሳ ነው። አንደኛ፣ በርካታ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት የክላስተር ጥረቱን ወጥነት የጎደለው አሰራር እየፈጠሩ በመሆኑ የክላስተር ምስረታ ትክክለኛ መዋቅር የለውም። ሁለተኛ፣ ከተቋማዊ ስልጣን ጋር ተያያዥነት ባላቸው ገደቦች በተጨማሪ ቴክኒካል እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዘላቂ ኢንተርፕራይዞችን እና ስብስቦችን ምስረታ ገድበዋል። በሶስተኛ ደረጃ በኢትዮጵያ ተግባራዊ የሆኑት የክላስተር አሠራሮች ለሀገር ውስጥም ሆነ ለዓለም አቀፍ ገዥዎች ትኩረት የሚስቡ አይደሉም ምክንያቱም ለብቻ ተለይተው ስለሚቀመጡ እና የተቀናጀ የማሰባሰብ እና የምርት አቀራረብን የሚጠይቁ ትዕዛዞችን በወቅቱ ለማቅረብ አይችሉም። በመጨረሻም ማህበራት በማምረት አቅም፣ በእሴት ሰንሰለት ወይም በምርቶች የተዋቀሩ አይደሉም ይልቁንም በዘመድ አዝማድ የመስራት ሂደት አለ። ይህ ተግዳሮቶች በምርት ዓይነቶች፣ የእሴት ሰንሰለቶች እና የድርጅት ሚዛን ስለሚለያዩ ማኅበራት የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ጉዳዮች የሚፈቱባቸውን መንገዶች ይገድባል።

### 4.1.4 የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ

**የስራ ማስኬጃ ገንዘብና የዉጭ ምንዛሬ እጥረት** - ዘርፉ ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅና ከፍተኛ ጥንቄ የሚጠይቅ በመሆኑ የአበደሪዎች እምብዛም አብሮ ያለመስራት ችግር፣ የአምራቾች ለግብዓት፣

የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች የሚሆን ፋይናንስ እጥረት፤ የማዕድን ዘርፉ የግብዓት አቅርቦት ባለማደጉ ምክንያት ከ70-99% የሚደርስ ከውጭ በሚገቡ ግብአቶች ጥገኛ በመሆናቸዉ ከፍ ያለ ተፅዕኖ አለዉ።

**የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር** - የዘርፉ አብዛኛዎች ግብዓቶች በፔትሮሊዬም ተረፈ ምርትና ከማዕድናት እንዲሁም በሳይንሳዊ ቅመራ የሚገኙ በመሆናቸዉንና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቅ በመሆኑ ሰፊ የአቅርቦት ችግር አለበት።

**የክህሎት ክፍተት መኖሩ** - ይህ ዘርፍ የሰለጠነ የሰዉ ሃይልና የዘመነ ቴክኖሎጅ እጥረት ችግር ያለበት ነዉ። ለሁሉም ኢንዱስትሪዎች ማሽን ላይ በደንብ የመስራት ክህሎት፣የፖሊመር ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ ዉስንነት ያለ ሲሆን በስልጠና መሻሻል የሚችል ቢሆንም ዘርፉ ወስብስብና ግዙፍ ከመሆኑ አንፃር የከፋ ጉዳት አስተናግዷል። የከፍተኛ ትምህርት ገበያዉ የሚፈልገዉን የሰለጠነ የሰዉ ሃይል ማቅረብ አለመቻል።

**የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክፍተት** - የሚመረቱ ምርቶች በጥራትና በብዛት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ዓለም እየተጠቀመ ያለውን ቴክኖሎጂ ለመጠቀምና በመንግስት በኩል ለአምራች ዘርፍ የተለየ ደጋፍ አለማድረጉ (ከአዳዲስ ኢንቨስተመንቶች በስተቀር) በርካታ ፋብሪካዎች ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ አድረጓል።

**የኃይል እጥረት እና ቀጣይነት ያለዉ የኃይል መቆራረጥ** - በሙሉ የማምረት አቅማቸው እንዳይደርሱ በማድረግ በምርቶች ጥራት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። በንዑስ ዘርፉ ውስጥ ባሉ አምራቾች እንደተገለፀው ኢንዱስትሪዎች ምርትን የሚያፋጥኑ ጄነሬተሮችን ለመጠቀም ይገደዳሉ፣ የነዳጅና ቅባት ዋጋ እየጨመረ በመምጣቱ በምርቶች ዋጋ ላይ ጭማሪ እንዲሁም በተወዳዳሪነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።

**ሀገር በቀል የቴክኖሎጂ ዉጤት አመንጪዎች (የአካዳሚክ፣ የምርምር እና የልማት ተቋማት እና ላቦራቶሪዎች) አለመሟላት** - የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ የምርምርና ልማት ሥራዎችን ማስፋፋት ግዴታ ቢሆንም የላብራቶሪ ፋሲሊቲዎች በአብዛኛዎቹ ኢንዱስትሪዎች ያልተደራጁና ያልተሟሉ በመሆኑ የአገር ውስጥ የሰው ኃይል አቅምን በአግባቡ ለመጠቀም አልተቻለም። በአፋር ክልል ያለው የክሎር-አልካሊ እምቅ አቅም እና በሱማሌ ክልል ያለዉ የተፈጥሮ ጋዝ ሃብትና የኢትሊን ፖሊመር ማምረት እምቅ አቅም፣ ፣ በቤንቺ ሸኮ አካባቢ ያለው የተፈጥሮ ጎማ፣ በማጂ አካባቢ ያለዉ ፓልም ዛፍ የሳሙና ግብዓት የሚያሳየዉ ወደ ማርሽ ቀያሪ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሊቀየር የሚችሉ ቢሆኑም አንዳቸዉም ሳየነኩ እንደቀጠሉ ናቸዉ።

**በአገር ውስጥ ምርቶች ላይ ያለው ዝቅተኛ አመለካከት** - ከውጭ ለሚገቡ ምርቶችን ያለ በቂ ምክንያት ቅድሚያ የመስጠት ዝንባሌ፣ ለሀገር ውስጥ አምራቾች እቃዎችን ለማቅረብ የገበያ እድል አለማግኘት፣ በአገር ውስጥ ጥራት ያለዉ ምርት ማቅረብ የሚችሉ ጥቂት አምራቾች ቢኖሩም በምርታቸዉ ላይ አመኔታ ያለመጣልና በአገር ውስጥ ለሚመረቱ ምርቶች ውስን የመንግስት ጨረታ በማዉጣት ከድሉ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ ተጠቃሽ ናቸዉ።

### 4.1.5 የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ

**ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንኡስ ዘርፍ የሚመደበው የውጭ ምንዛሪ በቂ ያልሆነ እና ወቅቱን ያልጠበቀ በመሆኑ በግብአቶች፣ ማሽነሪዎች እና መለዋወጫዎች አቅርቦት ላይ ውስንነትን ፈጥሯል፡፡** ምንም እንኳን መንግስት ለአምራች ዘርፍ ትኩረት የሰጠ ቢሆንም ለንዑስ ዘርፉ የሚመደበው የውጭ ምንዛሪ ያለቀውን ምርት ከውጭ ከሚያስገቡ አስመጪዎች እጅጉን ያነሰ ነው። እንዲሁም ወደ ውጭ ምርቶቻቸውን የሚልኩ አምራቾች ከላኩት ምርት ከሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ላይ ለግብዓት መግዣ የሚፈቀድላቸው የውጭ ምንዛሪ አነስተኛና ከሌሎች አምራች ካልሆኑ ላኪዎች እኩል ነው።

**ያልዳበረ መሰረት ያለው የግብዓት ዓቅርቦት፣ ደካማ ትስስር እና የአገር ውስጥ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ውስንነት ንዑስ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ ከውጭ በሚገቡ ግበዓቶች ላይ ጥገኛ አድርጎታል፡፡** ደረጃውን ያልጠበቀ ግብዓት፣ በቂ አቅራቢ፣ ስትራቴጂክ የሆነ ግብዓት የሚያቀርብ ኢንዱስትሪ (የብረት ማዕድን) አለመኖሩ ከውጭ በሚገቡ ግብዓቶች ላይ ንዑስ ዘርፉ ጥገኛ እንዲሆን አስገድዶታል።

**ሌላው ተግዳሮት ደጋፊ ኢንዱስትሪዎች (የማሽኒያና ተያያዥ ምርቶችን የሚያመርቱ) ጥራት ያለው ምርት አለማምረት ሲሆን** ለአብነትም እንደ ቲቪ እና ሞባይል ያሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ለማሸግ በአገር ውስጥ የሚመረቱት ማሸጊያዎች ከደረጃ በታች በመሆናቸው አምራቾች የማሸጊያ ዕቃዎችን ከውጭ እያስገቡ ነው።

**የጉምሩክ ባለሙያዎች ስለ ንዑስ-ዘርፉ ግብዓቶች ምንነት ተገቢው ቴክኒካል እውቀትና መረጃ ስለሌላቸው ከጉምሩክ ጣቢያዎች ግብዓትን ለማስለቀቅ ረጅም ጊዜ በመውሰዱ ኢንዱስትሪውን ለአላስፈላጊ ወጭ ይዳርጋል ፡፡** ስለሆነም በጉምሩክ ጣቢያዎች የንዑስ-ዘርፉ ቴክኒካል ዕውቀት (ምህንድስና እውቀት) ያላቸው ባለሙያዎችም ቢሰማሩ ፈጣን ውሳኔ ለመስጠት ያስችላል፡፡

**የኢትዮጵያ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ በቂና ወቅታዊ ፋይናንስ የማግኘት ችግር አለበት፡፡** ባንኮች ለግብርና እና ሌሎች ዘርፎች የሚሰጡትን ትኩረትና ድጋፍ ለንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎች

አይሰጡም ። የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የስራ ማስኬጃ ብድር አያቀርብም ሌሎች ንግድ ባንኮች ደግሞ ለሚሰጡት ብድር ወለዳቸው ከፍ ያለ፣ ወቅቱን ያለጠበቀና የዘርፉን ባህሪ ያላገናዘበ ነው።

**ተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ የማምረት አቅምን የሚገድብ እና የምርት ወጪን ይጨምራል፡፡** በተለይ የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ባላቸው የተለየ ባህሪ ጥራት ያለው ምርት እንዲያመርቱ የማያቋርጥ የኃይል አቅርቦት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የኃይል መቆራረጥ ጥራት የሌላቸው ምርቶችን እና ብዙ ብክነት ስለሚያስከትል በአምራቾች ላይ ኪሳራ ያስከትላል፡፡

**መንግሥት የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍን ከውጭ የሚገባን ምርት ያስቀራል ብሎ እየሰራ ያለበት ሁኔታ ቢኖርም ያለው የታሪፍ አወቃቀር ግን ዘርፉን ያገናዘበና አበረታች አይደለም።** ከውጭ የሚገባ ማሽን በዜሮ ታሪፍ እየገባ ምርቱን ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶቸ አምራቹ ቀርጦ እንዲያስገባ ይገደዳል፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ዕሴት ጭማሪን ያማከለ ምንም አይነት የማበረታቻ ስርዓት የለም፡፡ አንድ አይነት ምርት የሚያመርቱ ሁሉም ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ፣ የምርት አፈፃፀም፣ የያዙት የሰው ሀይል እና ሌሎችም መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ሳይገቡ ተጃምለው ተመሳሳይ ማበረታቻን ያገኛሉ፡፡

**የመንግስት ግዥን ጨምሮ ለሀገር ውስጥ ምርቶች ያለው አሉታዊ አመለካከት የሀገር ውስጥ አምራቾች አያበረታታም። የመንግስት ግዥዎች የሀገር ውስጥ አምራቾችን እንዳያካት ተደርጎ የጨረታ ሒደት ይከናወናል፡፡** ለአብነትም "በሀገር ውስጥ ያልተገጣጠሙ "የሚል አግላይ ፍላጎት ይካተታል፡፡ እንዲሁም የመንግስት ትልቁ ተቋም ኢትዮ ቴሌኮም የቴክኖ ስልኮች በሀገር ውስጥ የሚገጣጥም ፋብሪካ እያለ ተገጣጥሞ ያለቀ ቴክኖ ሞባይልን ከቻይና ሀገር በውጭ ምንዛሪ በብዛት ያስገባል፡፡

**የኢንደስትሪውን ተወዳዳሪነት የሚያጎለብቱ ግልጽ ፖሊሲዎች አለመኖራቸው እና በኢንዱስትሪው ላይ ያተኮረ ምርምርና ልማት እጅግ ውስን መሆኑ፡፡** በሚቀጥሉት ዓመታት ዘርፉ ወዴት እንደሚሄድ አቅጣጫ የሚያመላክቱ ፖሊሲዎች በግልፅ አልተቀመጡም ። እንዲሁም በንዑስ ዘርፉ ውስጥ ጠንካራ የአምራቾች ማህበር አለመኖሩ አምራቾች በተደራጀ ሁኔታ የፖሊሲ ሀሳብ እንዳያቀርቡና እንዳያስፈፅሙ ያደረጋቸው ሲሆን እንዲሁም የምርምርና ልማት ስራዎችን ፋይናንስ በማድረግ ተቀናጅተው እንዳያከናውኑ ተግዳሮት ሆኗል።

## 4.2 ዓለም አቀፍ ተሞክሮ ዳሰሳ

**የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስልቶችን መተግበር እና የአምራች ዘርፍ አፈጻጸምን ማሳደግ የበርካታ ታዳጊ ሀገራት ትኩረትን የሚስብ ርዕስ ሆኖ ቆይቷል።** ስኬታማ የተኪ ምርት ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ካደረጉ አቻ አገሮች ቁልፍ ትምህርቶችን እና ዘዴዎችን ለመለየት እና ለማዋሃድ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ተገምግመዋል። አርጀንቲና፣ ጃፓን፣ ሩሲያ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ቬትናም እንደ አቻ አገሮች የተመረጡት የተኪ ምርት ፖሊሲ ትግበራቸው ወቅት ዓላማቸው፣ ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውና የስነ-ሕዝብ አወቃቀራቸው ጋር ተመሳሳይ ሁኔታዎች በመኖራቸው ነው። የእነዚህን አቻ ሀገራት ፖሊሲዎችና ተግባራት በመገምገም ኢትዮጵያ የራሷን የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ስትራቴጂ እና የአምራች ዘርፍ አፈጻጸምን ለማሳደግ ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ማግኘት ትችላለች።

### 4.2.1 አርጀንቲና

**በአርጀንቲና የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን በ1930ዎቹ ተቀባይነት አግኝቶ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ድረስ የተተገበረ ሲሆን ዓላማው ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ልማት በተለይም በአምራች ዘርፉን ማሳደግ ነበር።** የአርጀንቲና መንግስት እንደ ስትራቴጅካዊ ጠቀሜታ፣ የዕድገት እምቅ አቅም፣ የመተካት አቅምና የገበያ ፍላጎት የመሳሰሉትን ለአምራች ዘርፍ ተኮር መመዘኛዎች በመጠቀም የተኪ ምርት ፖሊሲዋን ነድፋለች። የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ በሚቀየርበትና አዳዲስ እድሎች በሚፈጠሩበት ወቅት መንግስት የምርቶቹን ዝርዝር እየገመገመ ያስተካክላል። በአምራች ዘርፍውስጥ ካሉት የስትራቴጂካዊ ተኪ ምርቶች መካከል ምግብ እና መጠጦች፣ ፋርማሲዩቲካል፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ መኪናዎች፣ ማሽኖች እና መሳሪያዎች ይካተታሉ። በዚህ ወቅት የአርጀንቲና ኢኮኖሚ በዓመት በአማካይ በ6% ሲያድግ የኢንዱስትሪ ምርት ከ20% ወደ 35% በማደግ በ1970ዎቹ ሀገሪቱ ጠንካራ ዕድገት አስመዝግባለች። አርጀንቲና የህን ስኬት ዕውን ለማድረግ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስልቶች ተጠቅማለች። ተግባራዊ ያደረገችባቸው አንዳንድ ቁልፍ መንገዶችን ለመጥቀስ ያህል ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ታሪፍ መጣል፣ የሀገር ውስጥ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር እንዲወዳደሩ የሚረዱ ድጎማዎች ማስቀመጥ፣ በቁልፍ ኢንዱስትሪዎች ላይ አዳዲስ ፋብሪካዎችን መገንባትና ብድር ማመቻቸት፣ እንዲሁም ለሀገር ውስጥ ገበያ ለመሸጥ የተወሰነ የምርት መቶኛ በአገር ውስጥ እንዲመረት ማስገደድ ዋናዎቹ ውስጥ ይጠቀሳሉ።

### 4.2.2 ጃፓን

**ጃፓን እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ ኢኮኖሚዋን መልሶ ለመገንባት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተኪ ምርት ስትራቴጂን ተግባራዊ አድርጋለች።** የስትራቴጂው ዋና ዓላማ አገሪቱ ከውጪ በሚገቡ

ምርቶች ላይ ያላትን ጥገኝነት መቀነስ፣ የአገር ውስጥ ምርትን ማነቃቃት፣ የሥራ ስምሪት ማሳደግ እና የኑሮ ደረጃን ማሻሻል ነበር። ይህ ስትራቴጂ ስኬታማ በመሆኑ በ1960ዎቹ አጋማሽ ጃፓን የአለም የኢኮኖሚ ሃይል እንድትሆን አስችሏታል። በተጨማሪም ሀገሪቱ ኢኮኖሚዋን እንድታሳድግና የሀገር ውስጥ አቅሟን እና የምርምር እና የልማት ጥረቶችን እንድታጠናክር አግዟል። በዚህም ምክንያት የጃፓን የገቢ ምርት ፍላጎት ከ60% ወደ 30% ሲቀንስ የሰው ኃይል ምርታማነት በ50% ጨምሯል። በ1980ዎቹም ወደ ውጭ የሚላከው ምርት በዓመት በ9 በመቶ በመጨመር የወጪ ንግድ ገቢ ከ3.2 ቢሊዮን ዶላር ወደ 121 ቢሊዮን ዶላር አድጓል። የህን ለማስፈጸም ጃፓን የተጠቀመችው ዋናዎቹን ፖሊሲዎች ለመጥቀስ ያህል አዲስ ማሽኖችን ለማምረት ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የተተገበሩ የግብር ነፃነቶች፣ ለጥናትና ምርምርና ወጪ ቅናሾችና የውጭ ምንዛሬ ማበረታቻዎችን መስጠትና እና አንዳንድ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የሚገድቡ ደንቦች መከለስ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንትን ለመሳብ እና የጋራ ቬንቸር ለመመስረት የሚያገለግል እውቀት፣ ሃብት እና የግል ድርጅቶች ቅልጥፍናን ማበረታታት፣ እንዲሁም በዋናነት ዜጎች ክህሎቶቻቸውን እና እውቀታቸውን እንዲገነቡ እና የቴክኖሎጂ እና የማምረቻ እድገታቸውን እንዲቀጥሉ የትምህርት እድሎችን ማመቻቸት ይጠቃለላሉ።

### 4.2.3 ሩስያ

**እ.ኤ.አ. በ 2021 ሩሲያ ከአለም 11ኛዋ ትልቅ ኢኮኖሚ ነበረች ፣ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቷ 1.78 ትሪሊየን ዶላር ሲመዘን ይህም የአለምን ኢኮኖሚ 0.79% ይወክላል።** በሩሲያ ውስጥ የአምራች ዘርፍ መሪው ዘርፍ ሲሆን ከጠቅላላው ምርት 55% ይይዛል። ሀገሪቱ ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያላት ጥገኝነት የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብና የሀገር ውስጥ ምርትን ለመጨመር የተኪ ምርት ስትራቴጂ ተግባራዊ አድርጋለች። እ.ኤ.አ. በ 2014 ሩሲያ በኢንዱስትሪ ልማት እና የኢንዱስትሪ ተወዳዳሪነትን ማሻሻል ላይ መርሃ ግብር በማዘጋጀት ገደቦችን የመጣል፣ ማበረታቻዎችን የመተግበር፣ እንዲሁም ማዕቀቦችና ሌሎች የንግድ ጥበቃ እርምጃዎችን የማስቀመጥ ስልት ተጠቅማለች። ይህ ጥረት አጠቃላይ የግብርና ምርትን በ 2.4 እጥፍ ጨምሯል፤ እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ የምግብ ምርቶች ድርሻ በ 2013 ከነበረው 34% በ 2019 ወደ 25% ዝቅ ብሏል። በሩሲያ የተኪ ምርት ስትራቴጂን ለማሳካት በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ ኩባኛዎችና የግል ኩባንያዎች ግዥዎችን ላይ የማስመጣት ገደቦችን በመጣል የሃገር ምርት መጠቀምን ማበረታታት፣ የግብር ቅነሳ እና የካፒታል ተደራሽነት አይነት የበጀት ማበረታቻዎች መጨመር፣ የመንግስት እና የግል አጋርነት መመስረት እና የተወሰኑ ዘርፎች ላይ የቁጥጥር እርምጃዎች ማስቀመጥ፣ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን ማቋቋምና ለስልታዊ ኢንዱስትሪዎች ልማት ቅድሚያ መስጠት እና የግል ኩባንያዎች በጥናትና ምርምር ላይ ኢንቨስት

እንዲያደርጉና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ ቴክኖሎጂቸውን እንዲያሻሽሉ ማበረታታቻዎች ማስቀመጥ አይነት ፖሊሲዎችን ተከትላለች።

### 4.2.4 ደቡብ ኮሪያ

**ደቡብ ኮሪያ ወደ 51 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ያላት ሲሆን በከፍተኛ ደረጃ የተማረ ህዝብ እና ጠንካራ የስራ ባህሪ ያላት በመሆኗ ለኢኮኖሚዋ ስኬት አስተዋጽኦ አድርጓል።** የደቡብ ኮሪያ የተኪ ስትራቴጂ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ መፍትሄ ነበር። በ1960ዎቹ እና 1970ዎቹ ደቡብ ኮሪያ የሀገር ውስጥ ተወዳዳሪነቷን ለማዳበር እንደ ኤሌክትሮኒክስ፣ ብረት፣ መርከብ ግንባታ፣ አውቶሞቢሎች እና ፔትሮኬሚካል የመሳሰሉ ኢንዱስትሪዎች የተኪ ምርት ፖሊሲን ተከትላለች። በዚህም ምክንያት በ1960ዎቹ ከ6.9 በመቶ ወደ 14.9 በመቶ፣ በ1970ዎቹ ደግሞ በ116 በመቶ በኢኮኖሚዋን በማሳደግ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ካሉ ሀገራት አንዷ ሆናለች። የህዝቡን የኑሮ ደረጃ ከፍ የማድረግና የስራ እድል ፈጠራ በማስፋፋትም ከፍትኛ እድገት አስመዝግባለች። ደቡብ ኮሪያ የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ተግባራዊ ያደረገችባቸው ቁልፍ ስልቶች ውስጥ ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል የሀገር ውስጥ ታሪፎች እና ሌሎች የንግድ ጥበቃ እርምጃዎችን መውሰድ፣ በቁልፍ ኢንዱስትሪዎች እና በመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፣ የተራቀቁ ቴክኖሎጂዎችን እና እውቀትን ለማምጣት የውጭ ኢንቬስትመንትን መሳብ፣ ለማሳደግ ጥናትና ምርምርን መደገፍ፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እንዲያድጉ እና ከውጭ ኩባንያዎች ጋር እንዲወዳደሩ ለመርዳት እንደ ድጎማ እና የግብር እፎይታ ያሉ የገንዘብ ማበረታቻዎች ማስፋፋት ይጠቃለላሉ።

### 4.2.5 ቪዬትናም

**ቪዬትናም ወደ 97 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ያላት ሲሆን በፍጥነት በማደግ ላይ ባለው ኢኮኖሚዋ ትታወቃለች።** ቪዬትናም በ 20 ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ከማስተዋወቅ ጀምሮ እንደ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ግብርና እና ቴክኖሎጂ ባሉ ቁልፍ ዘርፎች ላይ የተወሰኑ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን በመገደብ ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ ጉልህ የሆነ የኢኮኖሚ ማሻሻያ አድርጋለች። ይህ ወደ ገበያ ተኮር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር እና ከአለም ኢኮኖሚ ጋር ለመቀላቀል የቪዬትናም ሰፊ እቅድ አካል ነበር። ይህ ፖሊሲ ከሌሎች ማሻሻያዎች እና ምቹ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ጋር በቪዬትናም ውስጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር አድርጓል። ፖሊሲው በአማካይ ዓመታዊ የኢንዱስትሪ ዕድገት 13.7% በማድረስ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን አስፍቷል፤ እንዲሁም ቅድሚያ በተሰጣቸው እንደ ኤሌክትሮኒክስ፣ ጨርቃጨርቅ እና ማሽነሪዎች ያሉ ምርቶችን ጨምሯል።

**ቬትናም የተኪ ምርት ኢንዱስትሪያላይዜሽን ለማመቻቸት ከተተገበረባቸው ፖሊሲዎች እና እርምጃዎች መካከል** የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ወጪን ለመቀነስ ከድርጅት ግብር፣ ከምርት የማስመጣት ቀረጥ እና ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ማድረግ፣ ከውጭ የሚገቡትን ምርቶች ዋጋ ለመጨመር እና መጠኑን ለመገደብ ቀረጦች እና ኮታዎች ለተመረጡት ሸቀጦች ጥቅም ላይ ማዋል፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን እቃዎች መጠን እና ዓይነቶች ለመቆጣጠር ውጭ ምንዛሬ ቁጥጥር የፍቃድ መስፈርቶች ማስቀመጥ፣ ምርትን ለማሳደግ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ለአገር ውስጥ ድርጅቶች መስጠት እና ኩባንያዎች የተወሰነ የሀገር ውስጥ ግብአቶችን እንዲጠቀሙ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ከውጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንት ወደ ሀገር ውስጥ ኩባንያዎች እንዲያስተላልፉ የሚያበረታቱ ደንቦች ማስወመጥ በወነኝነት የሚነሱ ናቸው።

### 4.2.6 ጀርመን

**ምንም እንኳን ጀርመን ቀጥታ የሆነ የተኪ ምርት ተብሎ ሊመደብ የሚችል ፖሊሲ ባይኖራትም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከውጭ የሚገቡ ጥገኝነቶችን ለመቀነስ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ማልማት ላይ ትኩረት አድርጋ ነበር።** እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ በድህረ-ግንባታ ወቅት ጀርመን የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎቿን እንደገና በመገንባት እና ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ ላይ አፅንዖት ሰጥታ የምርት አቅሞችን በተለይም እንደ ከባድ ኢንዱስትሪ፣ አምራች ኢንዱስትሪ እና መሠረተ ልማት ባሉ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጋ ነበር። ይህ ጥረት እራስን መቻልን ለማሳደግ ያለመ ቢሆንም፣ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት እና ዓለም አቀፍ ንግድን ለማስፋፋት በወጪ ንግድ ተኮር ፖሊሲዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረትም ተሰጥቶ ነበር። በዚህም ምክንያት በ1950 ከ 8 በመቶ የነበረው የስራ አጥነት መጠን በ1965 ወደ 1.2 በመቶ ሲቀንስ የሰራተኛ ደሞዝ በአመት በአማካይ በ3.7 በመቶ ጨምሯል። በጀርመን የተኪ ምርት ስትራቴጂን ለማሳካት የገንዘብ ድጋፍ እና ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የሙያ ትምህርት ቤቶችን ለማቋቋም እና ኩባንያዎች ሰራተኞቻቸውን በላቁ የአምራች ኢንዱስትሪ ቴክኒኮች እንዲያሠለጥኑ ድጎማዎችን ለመስጠት ገንዘብ በመመደብና በመስጠት፣ እንዲሁም ኩባንያዎችን፣ የምርምር ተቋማትን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ለመተባበር እና እውቀትን ለመለዋወጥ እንዲያመቻቸው በገንዘብ የተደገፈ የፈጠራ ክላስተር እና ኔትወርኮች በመፍጠር ተኪ ምርት ፖሊሲዋን በተሳካ ሁኔታ መተግበር ችላለች።

### 4.2.7 አሜሪካ

**ከ18ኛው እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ድረስ አሜሪካ ኢንዱስትሪዎቿን ከውጭ ውድድር ለመጠበቅ የኢኮኖሚ ጥበቃ ስልቶች ትጠቀም ነበር።** በቅርቡም በዶናልድ ትራምፕ

አስተዳደር ጊዜ ተመሳሳይ ፖሊሲ ተግባራዊ አድርጋለች። ከእነዚህ እርምጃዎች በስተጀርባ ያለው ዓላማ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን መጠበቅ፣ የስራ ዕድሎችን መፍጠርና የውጭ ሸቀጦችን ጥገኝነት መቀነስ ነበር። በነዚህ ፖሊሲዎች ምክንያት አሜሪካ በሴሚኮንዳክተር ኢንዱስትሪ ውስጥ የዓለም መሪ ስትሆን የአለም 4ኛ ብረት አምራች በመሆን በ2020 የገበያ ድርሻዋን ከ300 ቢሊዮን ዶላር በላይ በማድረስ ወደ 400,000 ለሚጠጉ ሰዎች የስራ እድል ፈጥራለች። አሜሪካ ያለባትን የንግድ ክፍተትን ለመቀነስና ኢንዱስትሪዎችን ከኢፍትሃዊ ውድድር ለመከላከል ታሪፍ የመሰሰሉ የጥበቃ ፖሊሲዎችን በማስቀመጥ፣ እንደ "ባይ አሜሪካን" አይነት የፌደራል ኤጀንሲዎች በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን እንዲገዙ የሚገፉ ፖሊሲዎች እና የምርምር እና የሙከራ ብድር በጥናትና ምርምር ልማት ላይ ኢንቨስት ለሚያደርጉ ኩባንያዎች የግብር እፎይታ በመስጠት፣ እና ለአሜሪካ ሴሚኮንዳክተር ኩባንያዎች ጥናትና ምርምር ላይ ኢንቬስት እንዲያደርጉ፣ የምርት ሂደታቸውን እንዲያሻሽሉ፣ ስራ እንዲፈጥሩና የማስመጣት ጥገኝነትን እንዲቀንሱ ድጎማ በመስጠት ጥሩ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችላለች።

### 4.2.8 ኢትዮጵያ የምትወስዳቸው ቁልፍ ትምህርቶች

**ኢትዮጵያ የተኪ ምርት ስትራቴጂዋን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ የምታደርግበትን መንገድ ለማመቻቸት ከላይ ከተጠቀሱት ሰባት አገሮች የሃገሪቱን ሁኔታ የሚመለከቱ ቁልፍ ግንዛቤዎች ተለይተዋል።** ይህ ልየታ በቀጣይ የሚነደፉትና የሚተገበሩት የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተገቢ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ይህንም በማድረግ የተነደፉት መፍትሄ አቅጣጫዎች ከስትራቴጂው ዐውድ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉና በአገሪቱ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ገቢ ምርቶችን ለመተካት ምቹ ሁኔታን የሚያመቻቹ ይሆናሉ። የተመረጡት 10 ቁልፍ ትምህርቶች ከታች ተጠቅሰዋል፤

1. **የፖሊሲ ግልጽነትና እና የረዥም ጊዜ እይታ** - ዘላቂ ልማት ለማምጣትና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የሚያስችሉ በግልጽ የተቀመጡ፣ ሁሉን አቀፍ፣ እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ ከግልጽ ኢላማዎች እና ወጥነት ያላቸውና ተለዋዋጭ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ጋር የሚላመዱ ፖሊሲዎች መቅረጽ
2. **መሠረተ ልማት እና የሰው ሃይል ልማት**- የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ በክህሎት፣ በመሠረተ ልማት፣ በኃይል፣ በግንኙነትና እና በትራንስፖርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ

3. **ፈጠራ እና ቴክኖሎጂ ትኩረት** - በጥናትና ምርምር ውስጥ ኢንቬስትመንትን ቅድሚያ መስጠት፣ በትምህርታዊ ጥናቶችና እና በኢንዱስትሪ መካከል ትብብርን ማጠናከር እና ለፈጠራ እና ለስራ ፈጣሪነት ምቹ አካባቢን ማጎልበት
4. **የዘርፍ ትኩረት** - ገቢ ምርቶችን ለመተካት ብቻ ሳይሆን በጥናትና ምርምር ላይ ኢንቬስት ለማድረግ እና ገበያዎችን ለውጭ ክፍት በማድረግ ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በተመረጡ ዘርፎች ላይ ማተኮርና ከውጪ ከሚገቡ ዕቃዎች ላይ እንደ ዋጋ ጭማሪና ከፍተኛ ቀረጥ ያሉ የንግድ ገደቦችን የተመረጡ ምርቶች ላይ መጣል
5. **የምርቶችና ኢንዱስትሪዎች ልዩነትና ብዝሃነት** - በአንድ ገበያ/ምርት ላይ የመተማመንን አደጋ ለመቀነስ እና ተወዳዳሪነትን ለመጨመር የምርት ብዝሃነትን ማበረታታት እና አዳዲስ ገበያዎችን ማሰስ እንዲሁም የአምራችና እሴት የተጨመረባቸው ኢንዱስትሪዎች ማሳደግ እና ለንግድ ተስማሚ ፖሊሲዎችን በማውጣት የሀገሪቱን የወጪ ንግድ መሰረት ማስፋፋት
6. **የውጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንት መስህብና ጠንካራ የግብዐት ትስስር** - የውጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንትን በመሳብ የሀገር ውስጥ ግብዐት ማምረቻ ፋብሪካዎችን በመክፈት የእሴት ሰንሰለቱን እንዲያሻሽሉ ማበረታታት፤ ለነዚህም አምራቾች የታክስ እና የታክስ ያልሆኑ ማበረታቻዎች መስጠትና እና ከሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ጋር የኋላልዮሽ ትስስር መፍጠር
7. **የኢኮኖሚ ጥበቃና ነጻነትን ማመዛዘን** - ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ ውድድር ለመጠበቅ ታሪፎችን እና የተለያዩ የንግድ መስፈርቶች በሚወጡበት ወቅት ፖሊሲዎቹን የአለም አቀፍ ንግድን የሚያስተባብሩ ነጻ ፖሊሲዎች ጋር ሚዛናዊ በሆነ አቀራረብ ማስኬድ
8. **ንቁ የግል ዘርፍ ተሳትፎ** - የኢኮኖሚ እድገትን ለማነቃቃት ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እስከ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ያሉ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን መተግበር፤ ለአለም አቀፍ ውድድር ከመጋለጣቸው በፊት ጅምር እና ታዳጊ ኢንዱስትሪዎችን የሚከልሉ ፖሊሲዎችን መጠቀም
9. **ጠንካራ የመንግስት ተሳትፎ** - በፖሊሲ ትግበራ ሂደት እና የህግ ማዕቀፎች ውስጥ የመንግስት ንቁ ሚና መጫወት ለምሳሌ የህዝብ ተቋማት ግዥዎች ወቅት ለሃገር ውስጥ ምርቶች ቅድሚያ መስጠት እንዲሁም የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ ኩባንያዎች ጋር መወዳደር እንዲችሉ ማበረታቻ መስጠት፣ ግብዓቶች እና መሰረተ ልማቶችን በማቅረብ ድጋፍ መስጠት

10. **መልካም አስተዳደር እና ተቋማዊ ጥንካሬ** - ውጤታማ የፖሊሲ ትግበራን ለማረጋገጥ መልካም አስተዳደር ባላቸው ጠንካራ ተቋማት የተኪ ምርት ስትራቴጂ መጋቢ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ

# 5 ክፍል አምስት

## 5.1 የተኪ ምርት ስትራቴጂክ የመፍትሄ ሃሳቦች

**የታዩትን የተወዳዳሪነት ውስንነቶች ለመቅረፍ እና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሻሻል በ5 ጭብጥ የተከፋፈሉ 71 የመፍትሄ ሃሳቦች በዚህ ተኪ ምርት ስትራቴጂ ተለይተዋል።** የእነዚህ የመፍትሄ ሃሳቦች ዋና ዓላማ በአምስቱ ቁልፍ ንዑስ ዘርፎች ውስጥ ከውጭ የሚገቡ ተኪ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾችን ለመደገፍ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ነው። ምንም እንኳን የመፍትሄ ሃሳቡ ሁሉን አቀፍ ባይሆኑም በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚተገበሩ የስትራቴጂክ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያጠቃልላሉ። በዚሁ መሰረት አምስቱ ጭብጥ መሪ የመፍትሄ ሃሳቦች ፖሊሲ እና ቁጥጥር፣ ፊስካል እና ኢንቨስትመንት፣ ስርዓት እና መሠረተ ልማት፣ የገበያ ተደራሽነት እና ምርታማነት እንዲሁም አቅም ግንባታን ያካትታሉ። ቅድሚያ የተሰጣቸው የመፍትሄ ሃሳቦች በሁሉም መሚመለከታቸው አካላት በነባር ተቋማዊ ተግባር እና ሃላፊነቶች ስር የተቀመጡ ናቸው። ይህንንም ሲያደርጉ ስልቱ ቅድሚያ ትኩረት በሚሰጣቸው ምርቶች ላይ መደረጉን እና እድገታቸውን የሚያደናቅፉ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት ጣልቃ መግባቱን ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

**የተለዩ ስትራቴጂክ መፍትሄዎችን ለመለየት አምስት ጭብጦች ተቀምጠዋል**




## 5.2 የተለዩ ስትራቴጂክ መፍትሄዎችን ትግበራ ስልቶች

**የቀረቡት የመፍትሄ ሃሳቦች በተመረጡ የትግበራ ስልቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።** ከነዚህ ስልቶች መካከል የአምራቾች ምርታማነታቸውን፣ የምርት ጥራታቸውን እና የገበያ ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያግዙ ማበረታቻዎች፣ ስልጠናዎች፣ የመንግስት ድጋፍ ማእቀፎች ፣ የቀረጥ ጥበቃ እና ከለላዎች ፣ ኮታ ስራት፣ የቅንጅት እና የግብይት መድረኮች እና የመረጃ ስርአቶች መዘርጋትን ያካትታል። የእነዚህ ስልቶች መግለጫ ከዚህ በታች ተካቷል።

| ትግበራ ስልቶች | ገለጻ |
|---|---|
| **ማበረታቻዎች** | ምርት እና የምርቱ አምራቾች ላይ ያተኮር የፈይናንስ እና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ለተመረጡ እና ተወዳዳሪ ለሆኑ አምራቾች ማቅረብን ያካትታል። ለምሳሌ፣ ስትራቴጂክ መፍትሄ (7) በኢትዮጵያ ውስጥ በፋይበር፣ ክር፣ ጨርቃጨርቅ፣ ጌጥ እና መለዋወጫዎች ማምረቻ ላይ ትኩረት ለሚያደርጉ አምራቾች አዲስ፤ አፈጻጸምን፤ ምርተ እና ብቃትን መሰረት ያደረጉ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ለማዘጋጀት ሀሳብ ቀርቧል። |
| **አቅም ግንባታ** | የአምራቾችን እና የመንግስት አግልግሎት አቅራቢዎችን፤ ስራ አፈጻሚዎችን እና ባለሙያዎችን ክህሎት በማዳበር የአፈጻጸም አቅምን መገንባት እንዲሁም ፈጠራን እና የእውቀት ሽግግርን ማሳለጥ የምርታማነት ጥራትን እና አገራዊ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል ይረዳል። ለምሳሌ የመፍትሄ ሃሳብ (40) የዩኒቨርሲቲ/የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተማሪዎችን ከአምራቾች ጋር የተግባር ሥልጠና ወይም ኢንተርፕርነርሽፕ ሥልጠናዎችን በመስጠት የተወዳዳሪነት አቅምን ማሳደግ አንዱ የቀረበ የመፍትሄ ሃሳብ ነው። |
| **የመንግስት ድጋፍ** | የመንግስትን ትኩረት በተለዩት ምርቶች ላይ በማድረግ የቁጥጥር መመሪያዎችን፣ የህግ ማእቀፎችን እና ሎእሎችንም አሰራሮች ባማዘጋጀት ለተመረጡ የአምራቾ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ማድረግን ይይዛል ። ለምሳሌ በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ ደረጃ በሚገኙ የጉምሩክ ቢሮዎች ውስጥ የባለሙያዎች ድጋፍ መገኘቱን ለማረጋገጥ በዘርፉ ልዩ የሆነ ባለአንድ መስኮት ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ አገልግሎት ስርአት እንዘረጋ እና አገልግሎት እንዲሰጥ የሚለው የመፍትሄ ሃሳብ አንዱ ማሳያ ነው። |
| **የታሪፍ ከለላ** | ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ለመጠበቅ በጊዜ ገደብ የተቀመጥ የታክስ እና የቀረጥ ከለላ እንዲሁም ዉጤታማነቱን በወቅት መከታተልን ያካትታል። ለምሳሌ የመፍትሄ ሃሳብ (59) የአምራቾችን የማምረቻ ወጪን ለመቀነስ ተወዳዳሪ የኤሌክትሪክ እቃዎችን የሚያመርቱ አምራቾች ለመደገፍ በእቃዎቹ አይንት የታሪፍ መጠኑን በጥናት መከለስ ሌላኛው የቀረብ የታሪፍ ከለላ ጋር የተገናኘ ስትራቴጂክ መፍትሄ ነው። |
| **ኮታ** | በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሀገር ውስጥ ሊገባ የሚችለውን መጠን መገደብን ይመለከታል። ለምሳሌ የመፍትሄ ሃሳብ (14) የአገር ውስጥ አምራቾች ለማበረታታት የአገር ውስጥ ተወዳዳሪ የማምረት አቅም ባላቸው በተመረጡ ምርቶች ላይ እና የሸማቾችን ፍላጎትን የማይጎዱ የንግድ ኮታዎችን ለመጣል ሀሳብ ያቀርባል ። በሌላ በኩል (የምርት ምርጫው በዚህ የስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ በተገለጹት 95 ተወዳዳሪ ምርቶች ምትክ መሰረት ከሆነ ለምሳሌ፣ የመፍትሄ ሃሳብ (22) ያለቀለት ቆዳ በኮታ ሥርዓት ለመገደብ ሐሳብ ያቀርባል። |

| | |
|---|---|
| **የግብይት እና የመረጃ ስርዓት ዝርጋታ** | አምራቾች የሀገር ውስጥ የገበያ መዳረሻን እንዲለዩ እና እንዲያውቁ፣ የንግድ ኔትወርኮችን እና ስምምነቶች እንዲመሰርቱ እና የዲጂታል መድረኮችን መፍጠር የመሰሰሉትን ይይዛል። ለምሳሌ, የመፍትሄ ሃሳብ (24) አምራቾች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ ብሔራዊ ኤግዚቢሽኖችን እና ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን ለማዘጋጀት ሐሳብ ያቀርባል። |
| **ግንዛቤ እና የቅስቀሻ ስራዎች** | ስለ የሀገር ውስጥ ምርቶች ጥራት እና ተወዳዳሪነት በማስተወወቅ በማህበረሰብ፣ በመንግስትር እና በግለሰብ ደረጃ ያሉ ሸማቾችን አመለካከት ለሀገር ውስጥ ማርት ያለዉን ጥሩ ያልሆነ አመለካከት ለመቀየር እና በአዲስ መልክ ለመቅረፅ ያሰበ ነው። ለምሳሌ የመንግስት ግዥ ፕሮቶኮሎችን በመከለስ መፍትሄ (36) የመንግስ ሸማች የሚፈልጋቸዉን ምርቶች ካልተገኙ ወይም ደረጃቸውን የጠበቁ ካልሆኑ በስተቀር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለማስቀረት በመንግስት ተቋማት ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ ምርቶች ግዥን ለማስፈጸም የመንግስት ግዥ ሂደቶችን ማሻሻል እንደ አንድ ሀሳብ ቀርቧል። |
| **የዋጋ ትመና እና ድጎማ** | ተወዳዳሪ ለሆኑ አምራቾች፤ መካከለኛ የካፒታል ዕቃዎችን ለሚያመርቱ፤ ከአቅም በላይ ወይም ዝቅተኛ የፍላጎት አቅርቦትን ለማስተካከል እንዲሁም ዋጋን ለማረጋጋት በጥንቃቄ የገበያ ግምገማ እና እቅድ በማውጣት አነስተኛ የገበያ መጨሻ የዋጋ ተመን እና ድጎማዎችን የገቢያ ጣልቃ ገብነቶችን ያካተታል።. ለምሳሌ፣ የመፍትሄ ሃሳብ (19) ህብረተሰቡ በእርድ ወቅት ቁሳቁሶችን በአግባቡ እንዲይዝ ለማበረታታት የ RHS የመጀመሪያ ደረጃ ሰብሳቢዎችን ድጎማ የቆዳ ዘርፉን ከመደገፉ አንጻር እንደ መፍትሄ ሀሳብ ቀርቧል። |
| **የግል እና የመንግስት ኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ** | የሀገር ውስጥ እና/ወይም የውጭ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ እና በመንግስት እና በግል አካላት መካከል ያለውን አጋርነት በማመቻቸት የማኑፋክቸሪንግ ፕሮጄክቶችን በገንዘብ መደገፍን ያካትታል። በተጨማሪም በጋራ ሽርክና እና ሌሎች የኢንቨስትመንት አይነቶችን በመጠቀም ስትራቴጂካዊ በተለይ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ግባት የሚውሉ ምርቶችን ማሳደግን ያካትታል። |

## 5.3 ስትራቴጂውን ከአዲሱ የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ እና የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ጋር መጣጣም

**የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አዲስ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ በቀድሞው ፖሊሲ ያጋጠሙትን ቁልፍ ተግዳሮቶች የሚፈታ እና ከሀገራዊና ከዘርፎች ልማታዊ ግቦች ጋር የተጣጣመ ነው።** ኢትዮጵያን በአፍሪካ ቀዳሚ የአምራች ኢንዱስትሪ ማዕከል የማድረግ ራዕይ በመያዝ አዲሱ ፖሊሲ የአምራች ኢንዱስትሪውን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳደግና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማድረግ ተነድፏል። ተወዳዳሪ ምርቶችን ለመተካት የተገለጹት 71 የመፍትሄ አቅጣጫዎች በአዲሱ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ አራት ዋና የውጤት ዘርፎች ስር የተዋቀሩ ናቸው። 44 መፍትሄዎች በፖሊሲው ውስጥ ከተዘረዘሩት ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥታ የሚጣጣሙ ሲሆን ቀሪዎቹ 27 መፍትሄዎች

በአራቱ ቁልፍ የውጤት መስኮች ሊመደቡ የሚችሉ ሲሆን በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አስተባባሪነት በቅንጅት ለመተግበር በሚመች መልኩ ተነድፈዋል።

## 5.4 የተኪ ምርት ስትራቴጂ ማስተባበሪያ እና የክትትልና ድጋፍ ማዕቀፍ

**የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በስሩ ያሉትን ኢኒሼቲቮች እና የአዲሱን የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ ፕሮጀክቶችን ለማስተባበር የጠነሰሰው መዋቅርን በመጠቀም የተኪ ምርት ስትራቴጂውን ለማስተባበርና ለማስተዳደር ታቅዷል።** በስትራቴጂው ስር የታቀፉ ተግባራት አጠቃላይ አመራር፣ ዕቅድ ማፅደቅ፣ ክትትልና ድጋፍ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር የሚመራው የአምራች ዘርፍ ልማት አስተባባሪ ኮሚቴ ይመራል። የኢትዮጵያ ታምራት ንቅናቄ ጽ/ቤት የተጠናከረ የትግበራ ትኩረት እና ቅንጅት በመገንባት እና ጠንካራ ማእከላዊ ቁጥጥሮችን በመዘርጋት የተለዩትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች አፈጻጸምና ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ይሰራል። በንቅናቄው ስር ክላስተር ኮሚቴዎች በስድስት መሪ ሃሳቦች ማለትም በፋይናንስና ጉምሩክ፣ በመሠረተ ልማት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በአቅም ግንባታና ምርምር፣ በኢንቨስትመንትና ግሉ ዘርፍ፣ እና በክልል እና በከተማ አስተዳደር ላይ ተደራጅተዋል። እነዚህ የክላስተር ኮሚቴዎች የአስተባባሪ ኮሚቴው በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማቀድ፣ በመከታተልና በማስተባበር የመፍትሄ አቅጣጫዎች ትግበራን ያረጋግጣሉ። በመጨረሻም የቴክኒክ ባለሙያዎችን ያቀፉ ልዩ የክላስተር ኮሚቴዎች ስር ያሉ የቴክኒክ ኮሚቴዎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን/ፕሮጀክቶችን በመምራት የቴክኒክ ሥራ የሚጠይቁ ልዩ ጉዳዮችን ይመለከታሉ።

**የኢትዮጵያ ታምርት ጽህፈት ቤት የተኪ ምርት ስትራቴጂውን ከአዲሱ የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ ጋር በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ይመራል።** ጽህፈት ቤቱ በተጨማሪም ትግበራን ለማፋጠን እና ስትራቴጂካዊ ዓላማዎችን ትርጉም ባለው መልኩ ለማራመድ ቅንጅታዊ እና የአስተዳደር መዋቅሩን ይመራል። ጽህፈት ቤቱ ከዋና ባለድርሻ አካላት እና ልማታዊ አጋሮች ጋር የተሳትፎ ወሰን፣ ሚናዎች፣ ኃላፊነቶች እና የሚጠበቁ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እና ለማስተካከል የቅንጅት ጥረቶችን ያስተባብራል። በተጨማሪም የፕሮጀክት አፈጻጸምን በወቅቱ ለማረጋገጥ እና የክትትል፣ የቁጥጥር እና የሪፖርት አቀራረብ ስራዎችን ከክላስተር/የቴክኒክ ኮሚቴዎች እና ፈጻሚ አጋሮች ጋር ለማድረግ መረጃ እና ትንታኔ በሚያስፈልግባቸው አካባቢዎች ቡድኖቹን ይደግፋል። ከዚህም ባለፈ ጽህፈት ቤቱ ዓመታዊ የዕቅድ እና የአፈጻጸም ግምገማ ተግባራትን ለመደገፍ፣ የዕቅድ እና የሪፖርት ማቅረቢያ አብነቶችን ለመጠቀም፣ እና ሁሉንም ተግባራት በዲጂታል ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ላይ ለማቀድ፣ ለመከታተል እና ሪፖርት ለማድረግ

ራሱን የቻለ የክትትልና ድጋፍ አስፈጻሚ ቡድን ይኖረዋል። እነዚህን እርምጃዎች በመውሰድ የስትራቴጂው የተቀናጀ አፈፃፀም ይረጋገጣል።

**የተኪ ምርት ስትራቴጂው በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን ውጤታማ ራሱን የቻለ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል።** የክትትልና ግምገማ ማዕቀፉ የኢትዮጵያ ታምርት ማዕቀፍ እየተካሄደበት ባለው ስልት መሰረት የሚቀረጽ ሲሆን በውስጡ በርካታ ዓላማዎችን ይይዛል፤ ይህም የስትራቴጂውን የአፈፃፀም ሂደትን መግለጽ እንዲሁም ከአዲሱ የአምራች ዘርፍ ፖሊሲ እና ከኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ጋር ያለውን ቅንጅት ማስተባበርን ያካትታል። የዚህ ስትራቴጂ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ የሚነደፈው በዝርዝር የትግበራ እቅድ ወቅት ሲሆን ይህም የፕሮጀክቱን ተግባራት፣ ወሰን፣ ፈጻሚዎች፣ ቅድሚያ የተሰጣቸው ምርቶችና የመፍትሄ አቅጣጫዎች፣ የበጀት መስፈርቶች፣ ኢላማ እና የጊዜ ሰሌዳን ያካትታል። እነዚህ ተግባራት ከተጠናቀቁ በኋላ አጠቃላይ የክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ መርሃ ግብሮች የአፈጻጸም ሂደቱ ላይ ለመወያይትና ለመወሰን ይዘጋጃሉ፤ መርሃ ግብሮቹም የመረጃ አሰባሰብ፣ የትንተና፣ እና የሪፖርት አፈጻጸምና ስርጭት ዕቅዶችን ያካትታሉ።

## 5.5 የበጀት ማሰባሰብ መስፈርት

**የትኛውንም ስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሀብት ማሰባሰብ ስትራቴጂ መንደፍ አስፈላጊ ነው።** ይህ ስትራቴጂ በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የሶስት አመት እቅድ ውስጥ የተቀመጡትን በጀቶች በመጠቀም የመፍትሄዎችን አቅጣጫዎችን ከነባር ኢኒሼቲቮች ጋር በማጣጣም ለመተግበር ታቅዷል። በተጨማሪም ነባር በጀት ለሌላቸው መፍትሄዎች የእቅድና የበጀት ልየታ ስራዎች እንዲሰሩ ታቅዷል። ያለውን በጀት በውጤታማነት በመጠቀም እና የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት አዳዲስ መንገዶችን በመፈለግ ስትራቴጂው የአጠቃላይ የየመፍትሄ አቅጣጫዎችን ውጤታማነት ለማሳደግ ያልማል። በስትራቴጂክ እቅድ እና በበጀት ልየታ ላይ ትኩረት በማድረግ ለስኬታማ ትግበራ እና የተፈለገውን ውጤት ለማሳካት ያዘጋጃል።

**በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የሶስት አመት እቅድ ውስጥ ከተገለጸው የበጀት ድልድል ጋር የሚጣጣሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለመተግበር 18,753,904.18 ዶላር የሚገመት መጠን ተለይቷል።** ይህ የእነዚህን የመፍትሄ አቅጣጫዎች አተገባበር ከእንቅስቃሴው አጠቃላይ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል። በንቅናቄው ስር በተለዩት ሰፊ የፕሮግራም ዘርፎች ውስጥ ከነበሩ ኢኒሼቲቮች ጋር በቀጥታ የማይናበቡ የመፍትሄ አቅጣጫዎች በሚቀጥለው ምዕራፍ ዝርዝር የትግበራ እቅድ ይዘጋጅላቸዋል።

**ሠንጠረዥ፡ ከኢትዮጵያ ታምርት ፕሮጀክቶች ጋር የተጣጣሙ የመፍትሄ አቅጣጫዎች የበጀት ይዘት**

| የኢትዮጵያ ታምርት ፕሮግራሞች | 3 ዐመት በጀት *(በ ብር)* | | | | ጠቅላላ በጀት *(በ ዶላር)* |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2016 | 2017 | 2018 | ጠቅላላ በጀት | |
| **ጠቅላላ በጀት** | 351,723,683 | 351,510,746 | 340,262,806 | **1,043,497,235** | **18,753,904.18** |
| የግብዐት ልማትን ማሳደግ | 206,753,845 | 213,100,209 | 186,932,297 | **606,786,350** | **10,905,264.23** |
| ተደራሽ መሠረተ ልማት እና የመንግስት አገልግሎቶች | 8,261,002 | 4,923,998 | 880,000 | **14,065,000** | **252,778.50** |
| የአምራች ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳደግ | 3,899,500 | 992,750 | - | **4,892,250** | **87,924.32** |
| የሰው ኃይል ልማት | 621,720 | 725,340 | 725,340 | **2,072,400** | **37,245.51** |
| የምርት ተኮር የኢንዱስትሪ ክላስተር | 44,000,000 | 33,000,000 | 33,000,000 | **110,000,000** | **1,976,938.12** |
| የአገር ውስጥ የማምረቻ ኢንዱስትሪ ልማት | 20,087,210 | 19,036,710 | 18,752,580 | **57,876,500** | **1,040,165.99** |
| ውጤት-ተኮር ማበረታቻ | 1,035,418 | 7,695,366 | 27,936,216 | **36,667,000** | **658,985.36** |
| የጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማሻሻል | 49,545,813 | 57,559,506 | 57,559,506 | **164,664,825** | **2,959,383.36** |
| ስትራቴጂያዊ ተኪ ምርቶችን መጨመር | 16,204,675 | 13,948,867 | 13,948,867 | **44,102,410** | **792,615.78** |
| ዘላቂ እና አረንጓዴ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት | 1,314,500 | 528,000 | 528,000 | **2,370,500** | **42,603.02** |

**የመንግስት ድጋፍን በብቃት ለማስተባበር እና በጀት ለመመደብ ስትራቴጂው በንቅናቄው ስር የተቋቋሙትን ስድስቱን የሀገር አቀፍ ክላስተር መዋቅሮችን አስፈላጊነት ተገንዝቧል።** እነዚህ የክላስተር አወቃቀሮች የስትራቴጂውን አፈፃፀም ለመምራት እና ለመከታተል ጠቃሚ ዘዴዎች ሆነው ሲያገለግሉ እንደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ያሉ የመንግስት አካላት ጥረታቸውን ለማስተባበር እና የስትራቴጂውን ስኬታማነት ለማረጋገጥ እነዚህን ክላስተር አወቃቀሮች ይጠቀማሉ።

**የኢንዱስትሪ ልማትን የበለጠ ለማሳደግ ስትራቴጂው የስትራቴጂያዊ ሀብቶችን አቅም ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን አፅንዖት ይሰጣል።** ግቡ ከእነዚህ ዘርፎች ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የእውቀት ሽግግርን በማጎልበት የስትራቴጂያዊ ምርቶችን የእሴት ሰንሰለቶች እንዲጎለብቱ ማድረግ ነው። ለእነዚህ ምርቶች የግብአት ፍላጎታቸው እና እምቅ ችሎታቸው አጠቃላይ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ መሆኑን

ለማረጋገጥ ጥልቅ ጥናቶች ታቅደዋል። የጋራ ስራዎችን በማጎልበት መንግስትና የግሉ ዘርፍ የረዥም ጊዜ ፕሮጀክቶችን በማስፈጸም የምርት አቅምን ማሳደግ ስለሚችሉም ይህ የትብብር አካሄድ ለኢኮኖሚ እና ለአምራች ማህበረሰብ እድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።

# 6 አባሪ

## 1. አባሪ ፤ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች ዝርዝር፣ የመተካት የጊዜ ሰሌዳዎች

### i. የምግብ እና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ሰብል | ብቅል | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ሰብል | ፓስታ እና ማካሮኒ | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ስኳር | ስኳር፣ ጣፋጭ ምግቦች | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | የቅባት ዕህሎች | የምግብ ዘይት | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | አትክልና ፍራፍሬ | የፍራፍሬ ጭማቂ፣ የማንጎ ፐልፕ፣ የማንጎ ኮንሰንትሬት | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | የምግብ ዝግጅት | የምግብ ዝግጅት* | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ሰብል | የበቆሎ ዱቄት፣ በቆሎ ፍሌክስ፣ በቆሎ ስታርች እና በቆሎ ስናክ | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ሰብል | የዳቦ መጋገሪያ ምርቶች፣ ብስኩት፣ ኩኪስ | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ሰብል | የስንዴ ወይም የሜስሊን ዱቄት | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ተረፈ ምርት | የእንስሳት መኖ | | | | | | | | | | |
| **ምግብ እና መጠጥ** | ተረፈ ምርት | የበለጸጉ ምግቦች (CSB⁺፣ CSB⁺⁺፣ famix) | | | | | | | | | | |

## ii. የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | መካከለኛ *(4 – 7)* | ረጅም *(8 – 10)* |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ሱሪ፣ ቁታ፣ ቁምጣ | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | የወንዶች ወይም የወንድ ልጅ የውስጥ ሱሪ (አጫጭር፣ ቦክሰር፣ ሱሪዎች፣ ወዘተ) | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | እንደ ጃምፕሱት፣ ሮምፐርስ፣ ታንክ ቶፕ እና ሙሉ ልብሶች (ባለ3 ፣ ባለ5 ፣ ባለ 7 ፣ ወዘተ ብዛት ያለው) ከጥጥ እና ከሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ የህፃናት ወይም የጨቅላ ልብሶች፣ | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ከጥጥ የተሰሩ ቲሸርቶች፣ ነጠላ ጫማዎች፣ ታንክ ቶፖች እና ሌሎች እጅጌ የሌላቸው የላይኛው ልብሶች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ረጅም ወይም አጭር ስቶኪንጎች፣ ካልሲዎች እና ተመሳሳይ የስቶኪንጎችን አይነቶች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመኑ ጨርቆች የተሰሩ የምሽት ልብሶች እና ፒጃማዎች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሱፍ ያልተሰራ የሱፍ አይነት ኮትና እና ጃኬት | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሠሩ የወንዶች ወይም የወንድ ሸሚዞች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ አንገት ወይም ትከሻ ላይ የሚለበሱ ስካርሾች እና ተመሳሳይ ነገሮች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ካልተሸመኑ የተሠሩ ልብሶች | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ሰው ሰራሽ ብትን ጭረቶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ካርድ ያልተደረጉ ፣ ክር ያልሆኑ ወይም በሌላ መንገድ ያልተሰሩ አጫጭር የፖሌስተር ጭረቶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | የጥጥ ተረፈ ምርቶች (የክርና የተሰበሰበ የአልባሳት) ተረፈ ምርቶችን ሳይጨምር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ሰው ሰራሽ የአሲቴት ብትን ጭረቶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ጭረቶች) | ያለተበጠረና ያልተላገ ጥጥ | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ሸካራማ የፖሊስተር ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከረጃጅም ፖሌስተር ጭረቶች የተሰራ ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከአይሪሊክ ወይም ከሞዳክሪሊክ ጭረቶች ተሰርቶ የተቀለመና በኬብል መልክ የተሰራ ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከፖሌስተር ጭረቶች የተሰራ በኬብል መልክ የተሰራ/የተገመደ ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከረጃጅም የፖሌስተር ጭረቶች የተሰራ ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ክር) | ከሰው ሠራሽ ጭረቶች የተሰራ የሰፌት ክር | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ≥ 85% ቴክስቸርድ እና ቴክስቸርድ ያልሆነ ፖሊስተር ጭረቶች የተሰሩ ጨርቆች | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | መካከለኛ *(4 – 7)* | ረጅም *(8 – 10)* |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ከተለያዩ ከፍተኛ ጥንካሬ ካላቸው ሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ሽምን ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ሽምን ጨርቅ) | ከ85% በሚበልጡ ቴክስቸራይዝድ ፖሊስተር የተሰሩ የተቀለሙ የተሰሩ ሽምን ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከጥጥና ከሰው ሰራሽ ጭረቶች ውጭ የተሰሩ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከተለጣጭ ጭረቶች የተሰሩ የተሸረቡ ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | የተሸረቡ ረጅም ፀጉራም ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ተለጣጭ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም እትም ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ተለጣጭ የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም የተቀለሙ ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (የተሸረበ ጨርቅ) | የተሸረቡ ወይም ባለ ፀጉራም ረጃጅም ሉፖች ያሏቸው ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ያልተሸመነ ጨርቅ) | ከ25-150 ግ/ሜ$^2$ የሚገዝፉ ከሰውሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ ያልተሸመኑ ጨርቆች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በተፍቲንግ፣ በመርፌ፣ በመንጠቆ፣ ወዘተ የቴክኒኮች አይነቶች የተሰሩ ምንጣፎች | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በፒቪሲ የተሸፈነ/የተለበጠ ጨርቅ | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | የጎማ ገመድ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከእንስሳት ፀጉር ክሮች የተሠሩ ምንጣፎች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከ30 ሴ.ሜ ወርድ ያልለጡ ከተለጣጭ/የጎማ ክር ና ያለ ወይም የለ እነዚህ የተሰሩ ጠባብ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በፕላስቲክ የተለበጡ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከ30 ሴ.ሜ ወርድ ያልበለጡ እና በጥጥ ወይም ሰው ሰራሽ ጭረቶች ያልተሰሩ ጠባብ ጨርቆች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከዕፅዋት ጭረቶች ወይም ከወፍራም የእንስሳት ፀጉር የተሠሩ ምንጣፎች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ከጥጥ የተሰራ እና ለህክምና አገልግሎት የሚውል ቀላል ክብደት ያለው ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | በቁጥርጥር የተሰሩ የምንጣፍ ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ቴክኒካል ቴክስታይል (ከሚለበስ ውጭ ለሆነ አገልግሎት) | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | ጨርቃጨርቅ (ልዩ ጨርቅ) | ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ክሮች፣ ጭረቶች፣ ወዘተ በመሃል ሽመና የተሰራ የተጠለፈ ጨርቅ | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ከጥጥ ውጭ የተሰሩ ቲሸርቶች፣ ጃፖኒዎች፣ ታንክ ቶፖች እና ሌሎች ሌሎች እጅጌ አልባ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | የሱፍ እና የእንስሳት ፀጉር ውጭ የሆኑ የስፖርት ቲሸርቶች፣ እጅጌ የሌላቸው ቲሸርቶች፣ ከፈያ ያላቸው ወይም ከፈያ የሌላቸው ሹራቦች፣ ካርዲጋኖች (ሹራብ ጃኬቶች) | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | **አጭር** *(1 – 3)* | | | **መካከለኛ** *(4 – 7)* | | | | **ረጅም** *(8 – 10)* | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | በሱፍ እና የእንስሳት ፀጉር የተሰሩ የስፖርት ቲሸርቶች፣ እጅጌ የሌላቸው ቲሸርቶች፣ ኮፈያ ያላቸው ወይም ኮፈያ የሌላቸው ሹራቦች፣ ካርዲጋኖች (ሹራብ ጃኬቶች) | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ከጥጥ እና ሰው ከሠራሽ ጭረቶች ያልተሰሩ እንደ ጃምፕሱት፣ ሮምፐርስ፣ ታንክ ቶፕ፣ ሙሉ ልብሶች (ባለ 3፣በለ 5 እና በለ 7 ብዛት ወዘተ) ያሉ የተለያዩ የጨቅላ ወይም የጨቅላ አልባሳት | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | የስፖርት ሱሪ እና ጃኬት በሴት | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸረበ) | ጃኬት የሚመስሉ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ሱሪ፣ ቁምጣ፣ ቱታ ወይም አጠቃላይ ከተሸመነ ጨርቅ የተሰራ ልብስ | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ የስፖርት ሱሪዎች እና ጃኬቶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሰው ሰራሽ ጭረቶች የተሰሩ አልባሳት | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመነ ጨርቅ የተሠሩ ጃኬት የሚመስሉ ልብሶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከሱፍ፣ ከሐር፣ ከሐር ተረፈ ምርት፣ ወዘተ የተሰሩና በአንገት ወይም በትከሻ ላይ የሚለበሱ ስካርቮች፣ ከላይ ተለባሾች እና መሰል ነገሮች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመኑ ጨርቆች የተሰሩ የስፖርት ሱሪዎች እና ጃኬቶች | | | | | | | | | | |
| **ጨርቃጨርቅና አልባሳት** | አልባሳት (የተሸመነ) | ከተሸመነ ጥጥ የተሰራ ሱሪ፣ ቁምጣ፣ ቱታ | | | | | | | | | | |

### iii. የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የጫማ ምርቶች | የቆዳ ጫማዎች (የቆዳ የተለመደ ጫማ እና የቅንጦት ጫማ) | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የጫማ ምርቶች | ሌሎች ጫማዎች (የሴቶች ጫማ ፣ የቆዳ ያልሆነ ጫማ ፣ የስፖርት ጫማ ፣ የደህንነት ጫማ) | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የጫማ ምርቶች | ሌሎች የጎማ ወይም የፕላስቲክ ጫማዎች | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የቆዳ እቃዎች | የቆዳ እቃዎች | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የቆዳ እቃዎች | ሴንቴቲክና ከጨርቅ የተሰሩ እቃዎች | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | የጫማ ምርቶች | የላይኛው ጫማ | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | አክሰሰሪዎች (መለዋወጫዎች) | የጫማ ሶል፣ ላስት (ፎርም) እና ሞልድ | | | | | | | | | | |
| **የቆዳና የቆዳ ውጤቶች** | አክሰሰሪዎች (መለዋወጫዎች) | ሌሎች አክሰሰሪዎች እና ኮምፖነንቶች | | | | | | | | | | |

### iv. የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ንዑስ ዘርፍ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | **የሚተኩበት ጊዜ** *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | **አጭር** *(1 – 3)* | | | **መካከለኛ** *(4 – 7)* | | | | **ረጅም** *(8 – 10)* | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | ደረቅና ፈሳሽ ሳሙና | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | ቀለምና ቫርኒሽ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | የንፅህና እቃ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | ሶልቨንትና ማቅጠኛዎች | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | መሰረታዊ ኬሚካል | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ኬሚካል | ማጣበቂያና ሌሎች የኮንስትራክሽን ኬሚካሎች | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የፕላስቲክ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የፕላስቲክ ዝርጎችች፣ ሴሉላር ያልሆኑ እና ያልጠናከሩ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | የፕላስቲክ ቱቦዎች እና ፊቲንጎች | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች ፕላስቲክ ዝርጎች፣ጥፍጣፎች ወዘተ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ፖሊአስቴል | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ሌሎች የቮልካናይዝድ ረበር/ጎማ ዕቃዎች | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-ኢንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ፎም | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | የመኪና ጎማና ጥርሱ የተቀየረ ጎማ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ብዕር/እስክሪቢቶ | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | ፖሊፕሮፕሊን ከረጢት | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፕላስቲክና ጎማ | የፕላስቲክ ፊልም ማሸጊያዎች | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | እንጨትና የእንጨት ውጤቶች | መክደኛና መያዣዎች | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | እንጨትና የእንጨት ውጤቶች | የእንጨት ውጤቶችና ክፍሎች | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፐልፕና ወረቀት | የካርቶን ማሸጊያዎች | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፐልፕና ወረቀት | የሴቶች ንፅህና መጠበቂያዎች፣ዳፐርና ፊት መጥረጊያ/ ወይፐር | | | | | | | | | | |
| **የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች** | ፐልፕና ወረቀት | ፐልፕና ወረቀት | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች | መስታዎት | ብርጭቆና ጠርሞሶች | | | | | | | | | | |

## v. ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ-ዘርፍ ቅድሚያ የተሰጣቸው ምርቶች

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | ተገጣጣሚ የህንፃ መስሪያዎች እና ክፍሎቻቸው፣ ከብረት ወይም ዐረብ ብረት የተሰሩ | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | የአሉሚኒየም ወፍራምና ቀጭን ዘንጎች | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | በጠፍጣፋው የተዳመጡ የብረት ወይም አሎይ ያልሆኑ የአረብ ብረት ውጤቶች፣ ወርዳቸው 600 ሚ.ሜ ወይም ከዚህ የበለጠ፣ የለበሱ፣ የተነከሩ ወይም የተቀቡ፡፡ | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | በጠፍጣፋው የተዳመጡ የብረት ወይም አሎይ ያልሆኑ የዓረብ ብረት ውጤቶች፣ ወርዳቸው ከ600 ሚ.ሜ ያነሰ፣ | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | ማጠራቂሚያዎች፣ ጋኖች፣ ገንዳዎች እና ለማናቸውም ነገር የሚሆኑ መያዣዎች /ከእምቅ ወይም ከፈሳሽ ጋዝ መያዣዎች ሌላ/፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | ጥቅጥቅ ወንፊት /ክብ ስራዎች ጭምር/፣ ፍርግርግ፣ ለመረብ እና ለአጥር የሚሆኑ፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት ሽቦ የተሠሩ፤ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠራ ሰፋፊ ቀዳዳ ያለው ዝርግ ሜታል፡፡ | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | **የሚተኩበት ጊዜ** *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | **አጭር** *(1 – 3)* | | | **መካከለኛ** *(4 – 7)* | | | | **ረጅም** *(8 – 10)* | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ብረትና ዐረብ ብረት | ሌሎች ቱቦዎች ቧንቧዎች እና ውስጠ ክፍት ፕሮፋይልስ /ለምሣሌ፣ የተያያዙ ወይም የተበየዱ፣ በሪቬት የተያያዙ ወይም በተመሣሣይ ሁኔታ የተያያዙ/፣ ከብረት ወይም ከዐረብ ብረት የተሠሩ። | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ተሽከርካሪ | የአይሮፕላን አካላት | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ተሽከርካሪ | የባለሞተር ተሽከርካሪ አካላት | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ተሽከርካሪ | ባለሞተር ተሽከርካሪ | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመር | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ሴንትሪፊጋል ፓምፖች | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ሰሌዳዎች/ቦርዶች | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የኤሌክትሪክ ሞተር፣ ጄኔሬተር | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ለኢንጂን የኤሌክትሪክ እሳት መስጫ/ማስነሻ መሳሪያዎች | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ፓምፖችና ኮምፕረሰሮች | | | | | | | | | | |

| ንዑስ-ዘርፍ | ንዑስ-አንዱስትሪ | ዕሴት ሰንሰለት (HS4 Product Category) | የሚተኩበት ጊዜ *(በአመታት)* | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አጭር *(1 – 3)* | | | መካከለኛ *(4 – 7)* | | | | ረጅም *(8 – 10)* | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | ኢንሱሌትድ/የተለበጡ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች/ኬብሎች | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ማሽኖችና ክፍሎቻቸው፣ | | | | | | | | | | |
| **ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ** | ማሽነሪና ኢኩፕመንት | የምግብና መጠጥ ማሽነሪዎች | | | | | | | | | | |

## 2. አባሪ II፡ በሁሉም ንዑስ ዘርፎች ውስጥ ገደቦች እና ተዛማጅ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ዝርዝር

### i. የምግብና መጠጥ ንዑስ ዘርፍ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| **የኳልዮሽ እና ፊትዮሽ ትስስር አለመኖር** | በቂ ያልሆነ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት (ዝቅተኛ ጥራት፣ መጠን እና የግብርና ግብአቶች ወቅታዊነት)፡ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ሊደረስበት የሚችል ክትተል፣ ግልጽ እና ሊተነበይ የሚችል የጥሬ | (1) ለቅድሚያ እና ለስልታዊ ምርቶች የመሰብሰቢያ እና የመጋዘን ደረሰኝ ስርዓትን ማስተዋወቅ - የምግብ ዘይት ፣ስኳር፣ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ የበለፀጉ ምግቦች ፣ ብቅል ፣ የፍራፍሬ ጭማቂ | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ግብርና ሚኒስቴርና የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፡--** የትስስር እና የመጋዘን ደረሰኝ አሰራርን ማስጀመር፣ ማስተዋወቅ እና ትግበራን ይቆጣጠራል<br>**ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፡-** ስርዓቱ ከንግድ ደንቦች ጋር የተጣጣመ መሆኑን እና የሸቀጦችን ግብይት እና ስርጭትን ይደግፋል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | | | የመካከለኛ (4 – 7) | | | | የረጅም (8 – 10) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ዕቃ ገበያ ሥርዓት አለመኖር | | | | | | | | | | | | | **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር/ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡-** ለተመረጡ የማምረቻ ምርቶች የመጋዘን ደረሰኝ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ ግ/ሚን እና ግ/ት/ኢን መደገፍ |
| | | (2) ሰፋፊ የግብርና እርሻን ማስፋፋት (አዲስ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት) በተነጣጠሩ ማበረታቻዎች እና ከአምራቾች ጋር በቀጥታ በተገናኘ ለስልታዊ ምርቶች (ስኳር፣ ስንዴ (ዳቦ እና ዱረም)፣ የምግብ ዘይት) | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ግብርና ሚኒስቴር፡** ሰፋፊ የግብርና እርሻ ልማዶችን ለማስፋት መመሪያ እና ድጋፍ በመስጠት በዘርፉ የአገር ውስጥና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ከአርሶ አደሩ ጋር የተያያዙ እቅዶችን በመተግበር አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እና ከአዳጊ ዕቅዶች ጋር ለመደገፍ የታለሙ ማበረታቻዎችን ይሰጣል።<br>**ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅራቢ ልማት ድርጅት፡-** የስትራቴጂክ ሸቀጣ ሸቀጦች አምራቾችን በመለየት እና በማገናኘት ከአርሶ አደሮች ጋር በማገናኘት ግ/ሚን ይደግፋሉ።<br>**አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡-** ለግ/ሚ እና ኢ/ሚ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር (1 – 3) | | | የመካከለኛ (4 – 7) | | | | የረጅም (8 – 10) | | | |
| | | (3) ለገበያ ትስስር (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት እና የአለም አቀፍ/ክልላዊ ገዥዎች) የእሴት ሰንሰለት ጥምረት መፍጠር እና አቅራቢዎች (አምራቾች ወይም የማህበር ተወካዮች) በአገር ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶች እንዲገዙ ማበረታታት ያስፈልጋል | ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | **የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፡** --<br>ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የምርት አምራቾችን ለማካተት አሁን ያሉትን የእሴት ሰንሰለት ትስስር መድረኮችን መጠቀም/ቢጠቀሙ<br><br>**ግብርና ሚኒስቴር፡-** አቅራቢዎችን (ገበሬዎችን) መለየት እና ከግብርና ቅድሚያዎች ጋር መጣጣምን ያረጋግጣል<br><br>**ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር/ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡-** አምራቾችን አሁን ባለው የእሴት ሰንሰለት ጥምረት ውስጥ እንዲካተቱ እና/ወይም አዲሶች እንዲፈጠሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ የህዝብ ተቋማት እና ከአለም አቀፍ/ክልላዊ ገዥዎች ጋር በመሳተፍ ማመቻቸት። |
| | | (4) በኢትዮጵያ ምርት ገበያ አንድ መስኮት የግብይት ሥርዓት መሠረት ከውጪ የሚተኩ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ቢያካትቱ | ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፡-** ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች በአንድ መስኮት የግብይት ሥርዓት ውስጥ ማካተት መጀመር እና መከታተል<br><br>**የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፡-** የአንድ መስኮት የግብይት ሥርዓትን ከሚመለከታቸው |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የማስመጣት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እቃዎች ማካተት |
| **ጊዜ ያለፈበት የማሽን አጠቃቀም ለስትራቴጂክ ምርት አምራቾች (ለምሳሌ የስኳር ፋብሪካዎች)** | የተሻሻለ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የተገደበ የባለቤትነት አማራጭ የገንዘብ ምንጮችን መገደብ (ከ50 ዓመታት በፊት የተቋቋሙ ስኳር የሚያመርቱ የመንግስት መር ድርጅቶች ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ ይጠቀማሉ - ከስኳር ኮርፖሬሽን የተወሰነ ድጋፍ) | (5) የውጭ ኩባንያዎች በነባር አምራቾች በተለይም በስኳር ፋብሪካዎች ክህሎት/ቴክኖሎጅ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆለዲንግ የኢንቨስትመንት መስህብ ጥረቶችን ማፋጠን | ፕሮጀክት | | | | **ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ:** በነባር የስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ ያሉ የኢንቨስትመንት እድሎችን መለየት የኢንቨስትመንት መስህብ ጥረቶችን ይመራል፣የሽርክና ስራዎችን ያስተዋውቃል እና የውጭ ኩባንያዎች በስኳር ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት።<br>**ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፡-** ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ እና የኢንቨስትመንት እድልን መለየት፣ ማመቻቸትና መደገፍ<br>**አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡-** በስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ ያሉ እድሎችን በመለየት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት |
| **ውስን የገበያ ደረጃ (ያልተስተካከለ የገበያ ዋጋ መለዋወጥ)** | ያልዳበረ የግብይት ሥርዓት | (6) ለስትራቴጂክ የግብርና ምርቶች ዝቅተኛውን የገበያ ዋጋ መወሰን፣ ተደጋጋሚ የገበያ ዋጋ ግምገማ ማካሄድ እና የገበያ ትርፍን ለመቆጣጠር አማራጮችን | ህጋዊ/ ፕሮግራም | | | | **ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፡-** ከግ/ሚ ጋር በመተባበር ለስልታዊ የግብርና ምርቶች ዝቅተኛውን የገበያ ዋጋ ይወስኑ እና ተደጋጋሚ የገበያ ዋጋ ግምገማ ያካሂዳሉ። |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | |
| | | በመለየት ለአምራቾች ጥሬ ዕቃ አቅርቦት እና ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ተገቢውን ክፍያ ማግኘት/መስጠት | | | | | **ኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት፡-** ዝቅተኛ ደረጃዎችናን ዋጋዎችን ከደረጃው አንፃር ይገመግማሉ እና ተደጋጋሚ የገበያ ዋጋና ምርት ደረጃዎችን ግምገማ ያካሂዳሉ<br>**ግብርና ሚኒስቴር፡-** ለአነስተኛ ይዞታ ገበሬዎች ተገቢውን ክፍያ ለማረጋገጥ አነስተኛውን የገበያ ዋጋ በመከታተል እና በማስፈጸም ን/ቀ/ት/ሚን መደገፍ<br>**ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር/ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፡--** ከን/ቀ/ት/ሚ ጋር በመተባበር ለአምራቾች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን ለማረጋገጥ እንደ ኤክስፖርት ማስተዋወቅ ወይም የአገር ውስጥ እሴት መጨመር የመሳሰሉ የገበያ ትርፍን ለማስተዳደር አማራጮችን ይለያሉ። |

### ii. የጨርቃጨርቅና አልባሳት ንዑስ ዘርፍ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | |
| **ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ትስስር አለመኖር** | በጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ማምረቻ እሴት | (7) በጭረት፣ በክር፣ በጨርቃጨርቅ፣ ተለጣጣፊና መለዋወጫዎች | መመሪያ | | | | **ኢ/ሚ፡-** ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰንሰለት ላይ የሚሰተዋል ያልተመጣጠነ ኢንቨስትመንት | ማምረቻ ላይ ለሚያተኮሩ አምራቾች አፈፃፀማቸውን መሰረተ ያደረገ አዲስ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን መተግበር፣ | | | | | ተቀራርቦ በመስራት፣ ነባር ማበረታቻዎችን በመገምገም አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን መንደፍ፣<br>**ገ/ሚ፡-** በአፈፃፀም ላይ ለሚመሰረቱ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ሙያዊ እገዛ ማድረግ፣<br>**አ/ኢ/ል/ኢ፡-** በአዳዲስ ማበረታቻዎች ግምገማ እና ዲዛይን ሂደት ውስጥ በተለዩ ምርቶች ላይ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ |
| | | (8) የጨርቃጨርቅና ጭረቶች ላይ ከፍተኛ የማምረት አቅም እና የተለያዩ የምርት ስብጥር ለሚኖራቸው ኢንቨስትመንቶች ለመሳብ የሚያስችል የገበያ ማስተዋወቂያ ስትራቴጂን ማዘጋጀት፣ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ኢ/ኮ ፡-** ከትናንሽ እስከ ከፍተኛ የማምረት አቅም ያላቸውን ጥጥ እና ሌሎች የጨርቃጨርቅ አመራቾችና አረሶ አደሮችን ያነጣጠረ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቂያ ስትራቴጂ እና የማበረታቻ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት፣<br>**ኢ/ሚ(አ/ኢ/ል/ኢ)**፡-- አጠቃላይ ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የምርት መጠን፣ ጥራት፣ መለኪያዎች ወዘተ ማዘጋጀት፣<br>**ን/ቀ/ት/ሚ**፡- ከኢ/ሚ እና ግ/ሚ ጋር በመመካከር የተፈጥሮ ጭረቶችን ንግድን መቆጣጠር |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | (9) በጨርቃጨርቅ ማምረቻ (ጥጥ እና ሌሎች የተፈጥሮ ጭረት አምራች አካባቢዎች) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት በጂኦግራፊያዊ የማምረት አቅም ላይ የተመሰረተ የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት የኢንዱስትሪ መንደር ማቋቋም | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ**፦ ከሚመለከታቸው የክልል ባለስልጣናት እና የኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከክልሎች ጂኦግራፊያዊ እምቅ አቅም ላይ ተመስርተው የጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪያዊ ክላስተሮችን ለማቋቋም የማስተባበር፣ የማመቻቸት እና የፍቃድ አሰጣጥ ሂደቶችን ይመራሉ፣<br>**ኢ/ኢ/ኮ**፦ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ ክላስተሮችን ለማቋቋም, የሚያግዝ ኢንቬስትመንትን ያመቻቻል፣ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ |
| **የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ችግር** | በቂና ጥራት ያለው ግብዓት ማምረት አለመቻል፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊመረቱ የማይችሉ ወሳኝ ግብዓቶችን በጊዜያዊነት ለማስገባት ልዩ ትኩረት አለመስጠት። | (10) ከመካከለኛ እስከ ረጅም ጊዜ የሚቆይ ከግ/ሚ ጋር በመተባበር እንደ ጥጥ ያሉ የተፈጥሮ ጭረቶችን በበቂ መጠንና ጥራት ለማምረት የሚያስችል ስትራቴጂ እና መርሃ ግብር መንደፍ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ እና ግ/ሚ**፦ የተፈጥሮ ጭረቶችን ለማምረት ስትራቴጂ ያዘጋጃል በተጨማሪም ከመካከለኛ እስከ ረጅም ጊዜ የሚቆየውን የስትራቴጂ ትግበራ ፕሮግራም በጋራ ያዘጋጃል፣<br>**አ/ኢ/ል/ኢ**፦ ስትራቴጂውን እና መርሃ ግብሩን ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ፍላጎቶች ጋር መጣጣሙን በማረጋገጥ ኢ/ሚንስቴርን ይደግፋል፣ |
| | | (11) ለግል የጥጥ አርቢዎች፣ ተመራማሪዎች እና ጥጥ ላይ እሴት | ስትራቴጂ | | | | **ግ/ሚ**፦ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የጥጥ ዝርያዎችን ለማምረት፤ ለግል የጥጥ አርቢዎች፣ ተመራማሪዎች እና ጥጥ እሴት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | ለሚጨምሩ አልሚዎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የጥጥ ዝርያዎች ለማምረት ማበረታቻ መፍጠር፤ | | | | | ለሚጨመሩ አልሚዎች የማበረታቻ መርሃ ግብር መንደፍ፤ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ድጋፍ እና መመሪያ መስጠት፣<br>**ኢ/ሚ፣ አ/ኢ/ል/ኢ**፡- ማበረታቻዎቹ ከጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ ፍላጎቶች ጋር እንዲጣጣሙ እና ተወዳዳሪ የእሴት ሰንሰለት ስለመፍጠሩ ያረጋግጣሉ፣<br>**ገ/ሚ**፡- የማበረታቻ ፕሮግራሙን ማረጋገጥ፣ መደገፍ እና መተግበር |
| **የዘርፉን የእሴት ሰንሰለት እምቅ አቅም ለመጠቀም የሚያስችል የቴክኖሎጂ እጥረት** | ወሳኝ በሆኑ የእሴት ሰንሰለቶች (የምርት ሰብጥር ላይ ጉልህ ሚና ያላቸው የጨርቃጨርቅ አምራቾች) በብዛት አለመኖርና በዚህ ዙሪያ ያለው የቴክኖሎጂ ክፍተት | 12) የተቀናጁ የእሴት ሰንሰለቶችን የማጎልበት አቅም ያላቸውን አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በመሳብ እና የተራቀቁ ቴክኖሎጂዎችን በማምጣት ተወዳዳሪ ምርቶችን ማምረት፣ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ ከኢ/ኢ/ኮን** ጋር በመተባበር የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪውን ፍላጎቶች የሚያሟላ s እና ኢ/ሚ/ን ይደግፋል፣ |
| **በሀገር ምርት አለመኩራት** | በሀገር ውሰጥ ሸማቾች የሚታይ የሀገር ውስጥ ምርቶችን 'ዝቅተኛ ጥራት' ያላቸው አድረጎ የመቁጠር ልምድ | (13) በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ለመጠቀም እና ለማስተዋወቅ ማህበረሰቦችን እና ገዥዎችን ለመድረስ ሀገራዊ፣ ክልላዊ እና ከተማ አቀፍ የዘመቻ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ፡-** አምራቾችን እና ገዢዎችን በብቃት ለመድረስ መድረክን በመፍጠር አገር አቀፍ ዘመቻውን ማመቻቸት፣<br>**አ/ኢ/ል/ኢ ከአምራች ማህበራተ ጋር በመተባበር** በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን ለማስተዋወቅ፣ ለመጠቀም እና ለማበረታታት የሀገር አቀፍ፣ ክልላዊ እና |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ከተማ አቀፍ የዘመቻ መርሃ ግብሮችን ቀርጾ ትግበራን ያመቻቻል። <br> **አምራች ማህበራት፡-** ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ምርቶች አምራቾች ጋር በማስተሳሰር እና በመገናኘት የማስተዋወቂያ ዘመቻውን ያመቻቻል፣ |
| | | (14) የተጠቃሚዎችን ፍለጎት ያማከለ በአገር ውስጥ ተወዳዳሪ የማምረት አቅም ባላቸው የተመረጡ ዕቃዎች ላይ የንግድ ኮታ መጣል፣ | የህግ ማዕቀፍ | | | | **ኢ/ሚ –** ከኢ/ጉ/ኮ ጋር በጋራ፣ በአገር ውስጥ ተወዳዳሪ የማምረት አቅም ባላቸው በተመረጡ ዕቃዎች ላይ የንግድ ኮታ ያዘጋጃል፣ <br> **የጉ/ኮ** - የአገር ውስጥ አምራቾችን ለመደገፍ እና ለመጠበቅ የንግድ ኮታውን ይቆጣጠራል ያሰፈፅማል፣ |

### iii. የቆዳና ቆዳ ምርቶች ንዑስ ዘርፍ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ጥራት ያለው የጥሬ ቆዳና ሌጦ እጥረት** | የኃላና የፊት የእሴት ሰንሰለት ትስስር አለመኖር፣ ፣ከእርድ በፊት እና በኃላ የአያያዝ | (15) በጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎችና በቆዳ ፋብሪካዎች መካከል የረጅም ጊዜ የኮንትራት ገበያ ትስስር ዘዴዎችን መፍጠር | ፕሮጀክት | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የረጅም ጊዜ የኮንትራት ገበያ ትስስር ስርዓትን ማዳበር እና በሰቤሳቢዎችና በቆዳ ፋብሪካዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ማመቻቸት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍተት፣ የቆዳ አሰባሰብ እና አያያዝ ክፍተት፣ የእንስሳቶቹ መጠን ማነስ | | | | | | **ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የኢንዱስትሪ እውቀት እና መመሪያ መስጠትና ውጤታማ የገበያ ትስስር ዘዴዎችን ማቋቋም<br><br>**የኢ.ቆ.ኢ.ማ** - የቆዳ ሰብሳቢዎችን እና የቆዳ ፋብሪካዎችን ፍላጎቶች በመወከል የገበያ ትስስር ስርዓቱን ለመፍጠር ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ድጋፍ መስጠት |
| | | (16) የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራት እና ጥበቃን ለማሳደግ በፋይናንስ፣ በስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎችን ማበረታታት | ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የጥሬ ቆዳና ሌጦ ጥራትን እና ጥበቃን ለማሻሻል ለዋና የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሰብሳቢዎች የአቅም ግንባታ የስልጠና ፕሮግራም መንደፍ<br><br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - ከኢ.ቆ.ኢ.ማ በመተባበር ለቆዳ ሰብሳቢዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ከፋብሪካዎች ጋር ግኑኝነት መፍጠር እና የቆዳ ጥራትን ማሻሻያ ፕሮግራም ማዘጋጀት |
| | | (17) ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ በማቋቋም ጥሬ ቆዳና ሌጦ በትራና በስፋት እንዲመረት በማድረግ የዋጋ ተወዳዳሪነት መጨመር | ፕሮጀክት/ፕሮግራም | | | | **የግብርና ሚንስቴር** - ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ማቋቋምና ለአርቢዎች ድጋፍ መስጠት፣<br><br>**ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የጥሬ ቆዳና ሌጦ የዋጋ ተመን በማዘጋጀት የድጎማ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | መርሃ ግብር መንደፍና ድጎማዎችን ለተጠቃሚዎች ማከፋፈልን<br><br>**የገንዘብ ሚንስቴር** - የድጎማ ፕሮግራም መገምገም እና የማስፈጽሚያ ገንዘብ መመደብ<br><br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የተለዩ ተጠቃሚዎችን መለየትና ተገቢውን የድጎማ ድጋፍ |
| | | (18) የ2006 ዓ.ም የወጣውን አዋጅ አንቀጽ 814/2013 መከለስና የቆዳ አምራቾችን እንደ ዋና ሰብሳቢ ማድረግ | የህግ ማእቀፍ | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የ2006 ዓ.ም የወጣውን አዋጅ አንቀጽ 814/2013 የማሻሻያ ሂደትን ይመራል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር አምራቾች እንደ ቀዳሚ ገዥ የጥሬ ቆዳ ሰብሳቢ በማድረግ የቆዳ ዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ<br><br>**ንግድና ቀጠናዊ ትስስር** - የተሻሻለው አንቀጽ ከንግድ ፖሊሲዎች እና ደንቦች ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል<br><br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የተሻሻለውን/የተሻሻለውን አዋጅ ለማዘጋጀት ለኢንዱስትሪ ሚንስቴር የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | | | | | | **የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**- የክለሳ ማሻሻያ ገምግሞ ማጽደቅ |
| | | (19) ህብረተሰቡ በእርድ ወቅት ቆዳን በአግባቡ እንዲይዝ ለማበረታታት የጥሬ ቆዳና ሌጦ የመግዣ ዋጋ መተመን እና የገንዘብ ድጎማ ማድረግ | የህግ ማእቀፍ | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - ለየጥሬ ቆዳና ሌጦ ዝቅተኛ ዋጋዎችን በማዘጋጀት የድጎማ መርሃ ግብር መንደፍ እና ድጎማዎችን ለተጠቃሚዎች ማከፋፈልን ይቆጣጠራል<br>**የገንዘብ ሚንስቴር** - የታቀደውን የድጎማ ፕሮግራም መገምገም እና ገንዘብ መመደብ እና ከተፈቀደ በኋላ አስፈላጊ ሀብቶችን ያቅርቡ<br><br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የታለሙ ተጠቃሚዎችን እና ተገቢውን የድጎማ መጠን ለመለየት ድጋፍ ማድረግ |
| | | (20) ከመካከለኛና ትላልቅ አምራቾች ጋር ትስስር በመፍጠር እና ሼዶች፣ የሊዝ ፋይናንስ፣ የስራ ካፒታል ተደራሽነት እና በሌሎች ፋሲሊቲዎች ድጋፍ በማቅረብ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ | ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የመርሃ ግብሩን አጠቃላይ አተገባበር ይቆጣጠራል, መመሪያዎችን ማዘጋጀት, እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ተቋማዊ ማዕቀፎችን እና የአቅም ግንባታ እርምጃዎችን ማዘጋጀትን ያካትታል.<br>**ኢንዱስትሪ ሚንስቴር እና ኢ.ኢ.ል.ኢ** - አነስተኛ ከመካከለኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍተሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | | | የመካከለኛ (4 – 7) | | | | የረጅም (8 – 10) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | እስከ ከትላልቅ አምራቾች ጋር ትስስር መፍጠር<br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - በቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለጥቃቅንና አነስተኛ ባለሙያዎች የቴክኒክ ድጋፍ እና ስልጠና መስጠት<br>**የኢትዮፕያ ኢኒንተርፕራይዞች ልማት** - ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነታቸውን ለማሻሻል እና ከትላልቅ አምራቾች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማመቻቸት የድጋፍ እና የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን መስጠት<br>**የገንዘብ ሚንስቴር** - የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለፕሮግራሙ ለአነስተኛ ድርጅቶች የሊዝ ፋይናንሲንግ እና የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ድጋፍ ማድረግ |
| | | (21) የክላስተር ልማት ጥረቶችን ማጠናከር፣ የክላስተር ፅንሰ-ሀሳብ ለአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ለትላልቅ አምራቾች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር እና የቆዳ ማህበራት በማጠናከር በእሴት ጭማሪ ላይ የንግድ | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የክላስተር ልማት ጥረቶችን ይመራል ፣ ግንዛቤን በመፍጠር እና በክላስተር ጽንሰ-ሀሳብ ላይ ለሚሳተፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መመሪያ ይሰጣል<br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረቶች እና ተስማሚ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ትስስር እና የአቅርቦት ሰንሰለት ተግዳሮቶችን መቀነስ | | | | | የእሴት ሰንሰለት ትስስርን ለማረጋገጥ የቴክኒክ ድጋፍን ይሰጣል<br>**የኢ.ቆ.ኢ.ማ** - በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ የንግድ ግንኙነቶችን በማሰባሰብ እና በማመቻቸት በአባሎቻቸው መካከል ግንዛቤን መፍጠር |
| **የግብዓት እጥረት (አክሰሰሪ፣ ኮምፖነንት፣ ያለቀለት ቆዳ, ወዘተ), ቴክኖሎጂ እና ክህሎት ክፍተት** | ያለቀለት የቆዳ ስብጥር እጥረት፣ በተቋማትና በኢንዱስትሪዎች የሥልጠና እጥረት፣ ለቴክኖሎጂ የፋይናንስ ውስንነት፣ አዲስ ቴክኖሎጂ አለመተግበር | (22) የቆዳ አምራቾች ችግሮችን በመቅረፍ የሀገር ውስጥ ያለቀለት ቆዳ ጥራትና አቅርቦት በማሳደግ ያለቀለት ቆዳ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ በኮታ ስርዓት መገደብ | የህግ ማእቀፍ | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - ያለቀለት ቆዳ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የሚከለክል የኮታ ስርዓቱን ይጀምራል፣ ይህም ከንግድ ፖሊሲዎች እና ደንቦች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል።<br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የኮታ ስርዓቱን ውጤቶች በመለየት ኢንዱስትሪ ሚንስቴር ይደግፋል።<br>**የገንዘብ ሚንስቴር** - የኮታ ስርዓቱን ይገመግማል፣ ያረጋግጣል፣ ይደግፋል<br>**የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን** - ያለቀለት ቆዳ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ የሚገድበውን ኮታ ይተገብራል |
| | | (23) የሀገር ውስጥ ጫማዎችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የምርት | ፕሮጀክት | | | | **ኢ.ኢ.ል.ኢ** - በቆዳ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለውን የምርት ስብጥር፣ የምርት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍተሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ስብጥር፣ የምርት ብራንድ ማሳደግ፣ የመከታተያ ችሎታን ማዳበር | | | | | ብራንድ እና የመከታተያ ሁኔታ ላይ ጥናት ያካሂዳል<br>**ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ከኢንዱስትሪ ማህበራት ጋር በመተባበር በአገር ውስጥ የጫማ ኢንዱስትሪ ውስጥ የምርት ስብጥር፣ የምርት ብራንድ እና ክትትልን ለማሳደግ ፕሮጀክት ማዘጋጀት። |
| **ዝቅተኛ የገበያ ትስስር እና ከፍተኛ የኮንትሮባንድ ገበያ** | ዝቅተኛ የምርት ስብጥር፣ ዝቅተኛ የንድፍና ዲዛይን ክህሎት ውስንነት፣ የንግድ ምልክት (ብራንድ) ግንዛቤ እጥረት፣ በኤግዚቢሽን እና በንግድ ትርኢት ላይ አለመሳተፍ፣ አነስተኛ የክላስተር አሰራር፣ ውስን የገበያ ትስስር መድረኮች፣ ዝቅተኛ የግብይት ስትራቴጂ፣ | (24) የአገር አስጥ አምራቾች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ እና የሀገር ውስጥ ምርትን ተጠቃሚነት የሚያበረታታ ሀገር አቀፍ ኤግዚቢሽንና የንግድ ትርኢቶች ማዘጋጀት | ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የሀገር ውስጥ ምርትን ለማስተዋወቅ ሀገራዊ ኤግዚቢሽኖችን እና የንግድ ትርኢቶችን ማዘጋጀት<br>**የኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ኮሚሽን** – የኢትዮጵያን የቆዳ ኢንዱስትሪ ለማስተዋወቅ እና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶችን ያዘጋጃል።<br>**የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የኢ.ቆ.ኢ.ማ** - በኢትዮጵያ ውስጥ የተሰሩ ምርቶችን በአገር ውስጥ ገዥዎች ዘንድ ያስተዋውቃል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍተሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከፍተኛ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች | (25) ኤግዚቢሽኖችን፣ የንግድ ትርዒቶችን እና ሌሎች ዝግጅቶችን በመሰተፍ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መካከለኛና ትላልቅ ኢንተርፕራይዞች መካከል የንግድ ትስስር መፍጠር። | ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር፣ ኢ.ኢ.ል.ኢ እና የኢትዮፕያ ኢኒንተርፕራይዞች ልማት** - ለአነስተኛ ተቋማት ምቹ ሁኔታን መፍጠር እና በኤግዚቢሽኖች እና በንግድ ትርኢቶች ላይ እንዲሳተፉ ማመቻቸት፤ በጥቃቅንና አነስተኛ እና መካከለኛ እና ትላልቅ ኢንተርፕራይዞች መካከል ትስስር መፍጠር |
| **የክላስተር እና የቆዳ ማህበር ስርዓት ጠንካራ አለመሆን** | ስለ ክላስተር እውቀትና የጋራ ግብ ማነስ፣ የአመለካከት ጉድለት፣ የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ፣ ስለ ክላስተር የግንዛቤ ማነስ፣ የመንግስት ትኩረት ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ መስጠት፣ የሼድ እጥረት እና ግልጽ ያልሆነ የሼድ አቅርቦት | (26) የክላስተር ልማት ጥረቶችን ማጠናከር እና ፅንሰ-ሀሳብን በመደመር ለአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ትልቅ አምራቾች ማህበራትን ጨምሮ በእሴት ሰንሰለቱ ላይ የንግድ ትስስር ለመፍጠር እና የአቅርቦት ሰንሰለት ተግዳሮቶችን ለመቀነስ ግንዛቤን መፍጠር | ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚንስቴር** - የክላስተር ልማት ጥረቶችን ይመራል ፣ ግንዛቤን በመፍጠር እና በክላስተር ጽንሰ-ሀሳብ ላይ ለሚሳተፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት መመሪያ ይሰጣል<br>**ኢ.ኢ.ል.ኢ** - የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥረቶች እና ተስማሚ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የእሴት ሰንሰለት ትስስርን ለማረጋገጥ የቴክኒክ ድጋፍን ይሰጣል<br>**የኢ.ቆ.ኢ.ማ** - በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ የንግድ ግንኙነቶችን በማሰባሰብ እና በማመቻቸት በአባሎቻቸው መካከል ግንዛቤን መፍጠር |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የመካከለኛ (4 – 7) | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | (27) የክላስተር አደረጃጀት በማጠናከር የኮታ አመራረት ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ፣ አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ትላልቅ አምራቾች የንግድ ትስስር መፍጠር እና የአቅርቦት ሰንሰለት ተግዳሮቶችን ለመቀነስ የክላስተር ፅንሰ-ሀሳብ ግንዛቤን መፍጠር | የህግ ማእቀፍ/ ፕሮግራም | | | | **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፡-** በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ የንግድ ግንኙነቶችን ግንዛቤን መፍጠር፣<br>**የኢ.ቆ.ኢ.ማ፡-** የኮታ አመራረት ስርዓቱን መንደፍ፣ ማስጀመር እና መተግበር<br>**አ.ኢ.ል.ኢ** - ለኢንዱስትሪዎች ተገቢውን የኮታ ደረጃ መለየት እና ከኤልአይኤ ጋር በመሆን የኮታውን አተገባበር ቴክኒካል ድጋፍ ይሰጣል |
| | | (28) በጥቃቅን፣ በመካከለኛና በትልቅ ደረጃ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪዎች በተለይም ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የምርት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ማህበራትን በማቋቋም ችግሮቻቸው መፍታት | የህግ ማእቀፍ/ ፕሮጀክት | | | | **የኢ.ቆ.ኢ.ማ** - ለቆዳ እና ለቆዳ ምርት ኢንዱስትሪዎች አዲሱን የምርት ሚዛን ላይ የተመሰረቱ ማህበራትን ማቋቋም<br>**ኢንዱስትሪ ሚንስቴር፣ አ.ኢ.ል.ኢ እና የኢትዮጵያ ኢኔንተርፕራይዞች ልማት** - የጥቃቅንና አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ትላልቅ ማህበራትን በማቋቋም የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር |

### iv. በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ንዑስ ዘርፍ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የኬሚካል፣ፕላስቲክና ጎማ ንዑስ ዘርፍ ዝቅተኛ ምርታማነት** | ዝቅተኛ የፊትና ኋልዮሽ ትስስር፣ዝቅተኛ የምርት መጠን(ምሳሌ ላብሳ)፣ ዝቅተኛ በገበያ ዉስጥ የሚደረግ ቁጥጥር፣ ዝቅተኛ ቴክኖሎጅ አጠቃቀምና ማላመድ | (28) የሃገር ዉስጥ ግብዓቶች ላይ ጥናት ማድረግ- በሀገር ዉስጥ ያለዉን የፖሊመር ሃብት ለመለየት እንደ ታዳሽ ፒኢቲ፣ታዳሽ ፒኢ፣ታዳሽ ፒፒ ከኢታኖል ማምረት፣ የማቅለሚያና ማለስለሻ ኬሚካሎች፣ የመካከለኛና ረጅም ጊዜ ፕሮግራም በመቀየስ ኬሚካል አቀናባሪዎችንና ተጠቃሚዎችን ማስተሳሰር ምሳሌ ፒቪሲ ኮምፓዉንድ የሚሰሩትን ከፓይፕ አምራቾች ጋር | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** – ባለድርሻ አካላትን ማስተባበር እና ከጥናትጋር ለማጣጣም እና የጥናት እና የፕሮግራም ልማት ሂደቱን ለመቆጣጠር የማስተሳሰሪያ ወይይት መድረክ መፍጠር<br>**ማ/ሚ** – አቅም ይሆናሉ ተብለዉ በተለዩ ላይ ጥናት ማካሄድ<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – በጥናት መሰረት ፕሮግራም በመቅረፅ ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመደጋገፍ የአምራች ዘርፉን የገበያ ስርጭት፣ተፈላጊነትና አቅርቦት መለየትና የዘርፉን ምርታመነት ሁኔታን መለካት<br>**ኢ/ኢ/ኮ** – የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ስራ ከኢ/ሚ ጋር በመተባበር |
| | | (29) በጋራ ማልማትን ጨምሮ የዉጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በመሳብ እንደ ፐልፕ ማምረቻ፣ጎማ፣ ላብሳ እና ሌሎች ስትራቴጃዊ ጠቀሜታ ያላቸዉን ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በማቋቋም ለሌሎች ግብዓት ተቀባይ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ኢ/ኮ –** ቅድሚያ ተብለዉ በተለዩት ላይ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅና መሳብ<br>**ኢ/ሚ** – ፕሮግራም በመቅረፅ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸዉ ዘርፎች ላይ ከኢ/ኢ/ኮ ጋር በመተባበር የፈቃድ አሰጣጥ ስራዎችና የህዝብ ኢንቨስትመንቶችን ማሳለጥ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እንዱስትሪዎች ፍትሃዊ ዉድድርና አቅርቦት እንዲኖራቸዉ ማድረግ | | | | | **አ/ኢ/ል/ኢ** – የማስተባበር ስራዎችን መደገፍና የአዋጭነት ጥናት ቴክኒካል ስራዎችን ማከናዎን |
| **የመኪና ጎማ የሚያድሱ የታክስ አከፋፈል ጫና** | ምክንያታዊና አሳማኝ ያልሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ በአሮጌ ጎማ እድሳት ንዑስ ዘርፍ አምራቾች ላይ መጣልና ማበረታቻ አለመኖር | (30) ግልፅና ተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ክለሳ ማድረግ | የህግ | | | | **ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢ**– ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የተጨማሪ እሴት ታክስተፅዕኖ በጎማ እደሳት ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች ላይ ግብዓት በመስጠት፣የዉይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለአዋጅ ክለሳ ግብዓት የሚሆኑ መነሻ ሃሳቦችን በማቅረብ<br><br>**ፖ/ጥ/ኢ –** የተጨማሪ እሴት ታክስ በጎማ እድሳት አምራቾች ላይ ያለዉን ተፅዕኖ በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶጸ ምክንያታዊ ና ተጨባጭ ማስረጃችን ይዞ ምክረ ኃሳብ በማቅረብ አዋጁ እንዲሻሻል በማድረግ በኩል ኢ/ሚን ማገዝ<br><br>**ገ/ሚ**– መገምገም ማረጋገጥና ለህ/ተ/ም/ቤት እንዲፀድቅ ማቅረብ,<br><br>**ህ/ተ/ም/ቤት**– መገምገም ማረጋገጥና ለትግበራ ማፀደቅ<br><br>**ገቢዎች ሚንስቴር** – በጎማ ዕድሳት ዘርፍ አምራቾች ላይ የሚሻሻለዉን የተጨማሪ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | እሴት ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ስራ ላይ ማዋልና ተግባራዊነቱን መከታተል |

## v. ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ የመፍትሄ አቅጣጫዎች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የንዑስ ዘርፉ ኢንዱስትሪዎች ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ከውጭ በሚገባ ግብዓት ላይ ጥገኛ መሆን** | ወሳኝ የሆኑ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት የሚረዱ ስልቶች/ስትራቴጂዎች የሉም | (31) በጊምቢ ከተማ እና በሰቆጣ የሚገኘውን የማግኔታይት-ኢልመኒት የብረት ማዕድን እና የብረት ፎስፌት ክምችትን በመለየት በኮረም ከተማ በሰቆጣ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የማግኔት-ኢልመኒት የብረት ማዕድን እና የብረት ፎስፌት ክምችትን በመለየት የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በማጥናት ከመካከለኛ እስከ ረጅም ጊዜ የሚቆይ መርሃ ግብር በመንደፍ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ከብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት ለመመስረት ለምሳሌ ከ ብረት ማቀነባበሪያዎች - በማዕድን | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** – ባለድርሻ አካላትን ለማሰባሰብ የግንኙነት መድረክ ማመቻቸትና ማስተባበር<br>**ማ/ሚ** – የብረት ማዕድን ለማውጣት የተዘጋጀውን ቅድመ-አዋጭነት ጥናትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰሩ ተግባራትን በባለቤትነት መምራት<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ በጣም የሚፈለጉ ምርቶችን በመለየት የገበያ ስርጭትን፣ ፍላጎትን እና አቅርቦትን በማጥናት እና ተለይተው የሚታወቁትን ምርቶች የምርታማነት ደረጃ በመለካት እና በጥናት ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ ለማዕድን ሚኒስቴር ድጋፍ ያደርጋል። |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሚኒስቴር ባለቤትነት የተያዘውን የብረት ማዕድን ማውጣት ቅድመ-አዋጭነት ጥናትን ወደ ተግባር መለወጥ. | | | | | **ን/ቀ/ት/ሚ** – ፍትሀዊ የሆነ የግብይትና የማከፋፈል ስርዓትን ይዘረጋል፡፡<br>**ኢ/ኢ/ኮ** – ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን የኢንቨስትመንቱን የማስተዋወቅ ስራን ይመራል |
| | | (32)የውድቅዳቂ ብረት አሰባሰብ፣ አለያየትና አሰረጫጨት ፖሊሲና የቁጥጥር ስርዓትን ማዘጋጀት | ስትራቴጂ/ህግ | | | | **ኢ/ሚ** – ከባለድርሻ ጋር በመወያየት ለብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ የውድቅዳቂ ብረት አሰባሰብ፣ አለያየትና አሰረጫጨት ፖሊሲና የቁጥጥር ስርዓትን ያዘጋጃል<br>**ኢ/ስ/ኢ** – ለብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፍ የውድቅዳቂ ብረት አሰባሰብ፣ አለያየትና አሰረጫጨት በተመለከት ስታንዳርድና መመሪያ ያወጣል<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት ውድቅዳቂ ብረትን በተመለተ ቴክኒካል ድጋፍና ስልጠና ይሰጣል፡፡<br>**የዘርፍ ማኅበራት** – የፖሊሲው እና የቁጥጥር ማዕቀፉ በኢንዱስትሪው ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ ላይ ግብአት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | |
| | | | | | | | መስጠት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለውጦች እንዲደረጉ መጠየቅ |
| | | (33) እንደ ፕሪንትድ ሰርኪዩት ቦርድ እና ሌሎች ስልታዊ (ስትራቴጂክ) ምርቶችን ለማምረት እና የነዚህን ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል ስትራቴጂ ማዘጋጀት | ስትራቴጂ | | | | **ኢ/ሚ** –እንደ ፕሪንትድ ሰርኪዩት ቦርድ እና ሌሎች ስልታዊ (ስትራቴጂክ) ምርቶችን ለማምረት እና የነዚህን ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል የስትራቴጂ ሀሳብ ማመንጨትና ማዘጋጀት፡፡<br>**ኢ/ኢ/ኮ** –እንደ ፕሪንትድ ሰርኪዩት ቦርድ እና ሌሎች ስልታዊ (ስትራቴጂክ) ምርቶችን ለማምረት የሚችሉ ኢንቨስትመንትን መሳብ<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ለስትራቴጂ ዝግጅቱ ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት |
| | | እያደገ ያለውን የአውቶሞቢል ኢንዱስትሪ ለማጠናከር ሀገር ውስጥ ለሚገጣጥሙ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን የአውቶሞቢል አካላትን ኤሌክትሮሜካኒካል ዕቃዎችን የሚያመርቱ የሀገር ውስጥ፣ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ኢ/ኮ** – ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች  ኢንቨስትመንት መሳብን ኃላፊነት ወስዶ ይሰራል<br>**ኢ/ሚ** – ለግሉ ሴክተር ኢንቨስትመንት ከ ኢ/ኢ/ኮ ጋር የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ ሌሎች የማመቻቸት ወዘተ ስራዎችን ይሰራል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የውጭና የጥምረት ባለሀብቶችን ኢንቨስትመንት መሳብ | | | | | **አ/ኢ/ል/ኢ –** በቅንጅት ቴክኒካል ድጋፍ ይሰጣልለባለሀብቶች የእሴት ፕሮፖሲሽን ቴክኒካል ድጋፍ መስጠት |
| **አንድ ኩባንያ የምርቱን እያንዳንዱን ክፍል ሙሉ ለሙሉ ብቻውን ማምረት አይችልም። የአቅርቦት ሰንሰለቱ ግን ትኩረት አልተሰጠውም።** | ለትላልቅ ኢንዱስትሪዎች የምርት ክፍልን በማምረት ለሚያቀርቡ ኢንዱስትሪዎች ምንም ዓይነት የማበረታቻ ስርዓት አልተዘረጋም | (35) የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማዘጋጀት | ፖሊሲ | | | | **ኢ/ሚ** – የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማዘጋጀትና አተገባበሩን መከታተል<br><br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ዝግጅት እና አተገባበር ላይ ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ<br><br>**ኢ/ኢ/ኮ** – የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪውን በማስተዋወቅ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ።<br><br>**ን/ቀ/ት/ሚ** – ፖሊሲው ከሌሎች የንግድ ህጎችና ስምምነቶች ጋር የማይጋጭ መሆኑን ማረጋገጥና የ አውቶሞቲቭ ምርቶችን ግብይት ማሳለጥ።<br><br>**ኢ/ስ/ኢ** – ለአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪው የምርት እንዲሁም የሴፍቲና የጥራት ስታንዳርድ ማዘጋጀት።<br><br>**ገ/ሚ** – ፖሊሲውን ከኢትዮጵያ የግብር መዋቅር ጋር መጣጣሙን ይከታተላል |

## vi. የጋራ ተግዳሮቶች

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍተሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ግንዛቤ** | በአገር ውስጥ የሚመረተውን ምርት ላለመግዛት በመንግስት ግዥዎች የጨረታ ሰነደ ላይ የሚቀመጡ መስፈርቶች፤ በሀገር ውስጥ ለተመረቱ እቃዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውዝቅተኛ ግንዛቤ | (36) በመንግስት ተቋማት ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ ምርቶች ግዥን ለማስፈጸም የመንግስት ግዥ አሰራርን ማሻሻል (ለአምስቱ ዘርፎች እና በተኪ ምርት ስትራቴጂ ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተኪ ምርቶች) ከውጭ የሚገዙት የሀገር ውስጥ ምርቶችን ደረጃቸውን ያልጠበቁ ሲሆን ብቻ መሆን ይገባዋል | ህግ | ✓ | ✓ | | **ኢ/ሚ** – በመንግስት ግዥ አሰራር ላይ የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ ያቀርባል<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – የተሻሻሉ የግዥ ሂደቶችን በማዘጋጀት እና በመተግበር ረገድ ቴክኒካል ግብዓት እና ድጋፍ በመስጠት፤ ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ ምርቶችን በመለየት በመንግስት ተቋማት የሚደረጉ ግዥዎችን ማስፈጸምን ጨምሮ።<br>**ኢ/ስ/ኢ** –የሀገር ውስጥ ምርቶች የደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና እነዚህን መመዘኛዎች እንዲያሟሉ ለአገር ውስጥ አምራቾች መመሪያዎችን ማዘጋጀትና እና ድጋፍ መስጠት።<br>**PPPA** –በመንግስት ተቋማት ተወዳዳሪ የሀገር ውስጥ ምርቶች ግዥን ለማስፈጸም የመንግስት ግዥ ሂደቶችን ማሻሻል<br>**ፌ/ስ/ጸ/ኮ** –የተሻሻለው የግዥ አሰራር ግልፅ እና ከሙስና የፀዳ መሆኑን ማረጋገጥ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | **ፋ/ሚ** – የተሸሻለው የግዥ አሰራር ከገንዘብ ነክ ደንቦችና ጋር መናበቡን ያረጋግጣል አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡ |
| | | (37)) ስለ ሀገር ውስጥ ተወዳዳሪ ምርቶች ግንዛቤ መፍጠር (ለአምስቱ ዘርፎች እና በተኪ ምርት ስትራቴጅ ላይ ቅድሚያ ለተሰጣቸው ምርቶች) ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች - ጎማ ፣ ፕላስቲክ እና ወረቀት ፣ እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉ ምርቶች ፣ ብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ) የፕላስቲክ እና የወረቀት መልሶ ጥቅም ላይ መዋል ቴክኖሎጂን እና ደረጃውን የጠበቀ እንደገና ጥቅም ላይ የዋለ ፕላስቲክ እና ወረቀት ለማምረት (ለአምስቱ ዘርፎች) | ህግ/ ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** –ለሀገር ውስጥ ተወዳዳሪ ምርቶች ወቅታዊ የቴክኖሎጂ አቅም ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ንቅናቄዎችን ማዘጋጀት እና እንደገና ጥቅም ላይ የዋለ የፕላስቲክ እና የወረቀት አጠቃቀምን አመራረትን ማስተዋወቅ፡፡<br>**የአካባቢ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን** –የፕላስቲክ እና የወረቀት አዲስ የቴክኖሎጂ አቅም እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እና እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን አጠቃቀምንና ማምረት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማስቻል፡፡<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** - የፕላስቲክ እና የወረቀት አዲስ የቴክኖሎጂ አቅም እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል እና እንደገና ጥቅም ላይ በዋሉ ቁሳቁሶች ደረጃውን የጠበቀ ምርትን ማምረትን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ላይ ቴክኒካል ድጋፍ ያደርጋል፡፡ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | **ኢ/ስ/ኢ** – በማምረቻው ውስጥ እንደገና ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን ለመጠቀም ደረጃዎችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ የሀገር ውስጥ ምርቶች የደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡<br>**ኢ/ቴ/ሚ** –ስለ ቁሳቁስ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወቅታዊው የቴክኖሎጂ አቅም ላየ ምርምር በማከናወን መረጃ መስጠት እና ለአካባቢ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና ሂደቶችን መጠቀምን ማስተዋወቅ<br>**የዘርፍ ማኅበራት** – ስለ ወቅታዊ የቴክኖሎጂ አቅም እና ቁሳቁስን እንደገና ጥቅም ላይ ስለማዋል ቴክኖሎጂ ለአባል አምራቾች መረጃን ይሰጣሉ፡፡ |
| | | (38) በነባር ማበረታቻዎች - የግብአት አቅራቢዎች ፣ ማቀነባበሪያዎች እና የፓኬጂንግ ኢንዱስትሪዎች ላይ ለሁሉም 5 ሴክተሮች ከዋጋ ሰንሰለታቸው አንፃር ቅድሚያ ለሚሰጡ ግብዓት | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** – ቅድሚያ ለተሰጣቸው ምርት አምራቾች የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀት እና መተግበር ከሌሎች የመንግስት አካላት እና የኢንዱስትሪ ማህበራት ጋር በመተባበር ስለነባሩ ማበረታቻዎች ማሳወቅ እና ማሳተፍ፡፡ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አቅራቢዎች የግንዛቤ ፈጠራ ፕሮግራሞችን መንደፍ) | | | | | **አ/ኢ/ል/ኢ** – የአምራቾችን ቴክኒካዊ ግብዓት እና እይታን በማቅረብ ፕሮግራሙን እንዲዘጋጅ ኢ/ሚን ይደግፉ<br>**ኢ/ኢ/ኮ** –በነበሩት ማበረታቻዎች ላይ በመመስረት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንቨስትመንትን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ዘርፉን ማስፋፋትና በመደገፍ።<br>**የዘርፍ ማኅበራት** – ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች ያሉ የነባር ማበረታቻዎች መረጃን ያስተላልፋሉ |
| **ችሎታ/ክህሎት** | ጊዜው ያለፈበት የሥልጠና ሥርዓት ትምህርት፤ ክህሎት ላይ የተግባር ሥልጠና ዕጥረት፣ ፣የልዩ ሥልጠና እጥረት | (39) የዩኒቨርሲቲዎችና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ስርዓተ ትምህርትን ከአምስቱ ንዑስ ዘርፎች አንፃር ተገቢ ባለሙያዎችንና ባለድርሻዎችን በማሳተፍ መገምገምና መከለስ | ፕሮጀክት | | | | **ኢ/ሚ** – በሚፈለገውና ባለው ክህሎት መካከል ያለውን ክፍተት ከባለድርሻ ጋር በመቀናጀት መለየት<br>**ስ/ክ/ሚ** እና **ት/ሚ** – ከ ኢ/ሚ የተገኙትን ውጤቶች በመለየት ከግሉ ዘርፍ፣ ከኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከላት እና ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ዩኒቨርሲቲዎችንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርትን ከአምስቱም ዘርፎች አንፃር |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | | | | | | በመገምገምና በመከለስ ከገበያ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ<br><br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – በክህሎት ክፍተት መለየት እና በቴክኖሎጂ ደረጃ ግምገማ ደረጃዎች በሙሉ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ማማከር፣ እና በስርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮጀክት ወቅት ፈጻሚ ተቋማትን ይደግፋሉ። |
| | | (40) ለአምስቱም ሴክተሮች አምራቾች የተግባር ስልጠናዎችን ወይም ልምምዶችን ማሳደግ በተለይም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተኪ ምርቶችን ለሚያመርቱ አምራቾች | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** –ከአምራቾች ጋር በመወያየት የተግባር ልምምድ እና ክህሎትን ለማሳደግ ፕሮግራምን ማስተዋወቅ እና መንደፍ<br><br>**ት/ሚ እና ስ/ት/ሚ** – የተግባር ስልጠናዎችን፣ የትምህርት ላይ ልምምዶችን ከዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎች ስርአተ ትምህርት ጋር በማዋሃድ እና ለተማሪዎች እንደዚህ አይነት እድሎችን እንዲያገኙ ድጋፍ ለማድረግ።<br><br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች አምራቾች ፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ማመቻቸት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | | | | | | የተግባር ስልጠና እና ልምምድ እንዲያገኙ ትስስር መፍጠር። <br> **የዘርፍ ማኅበራት** – ከዩኒቨርሲቲዎች እና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የተሻለ ችሎታ ያለቸውን ሰልጣኞች ለማፍራት ልምምዶች ክህሎትና ብቃቶች ላይ ግብአት መስጠት <br> **የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት** – ከአምራቾች ጋር ተግባቦት በመፍጠር ለተማሪዎቻቸው ስልጠናና የኢንዱስትሪ ስልጠና ማመቻቸት። |
| | | (41)) በሠራተኛ፣ በአመራርና በአምራቾች መካከል እኩልና ምቹ የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር የሠራተኛ ሕጉን ማሻሻል እና ኢንዱስትሪዎች ተግባራዊ መዋቅር እንዲመሰርቱ ማበረታታት (በአምራቾች እና በሠራተኞች መካከል ግንኙነት መፍጠር እና ማኅበራትን ማቋቋምን ማበረታታት) | ህግ | | | | **ኢ/ሚ** –በሥራ ላይ ባለው የሠራተኛ ሕግ ውስጥ ያሉትን ክፍተቶች ከ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ለመፍታት ጥናት ማካሄድ እና ማሻሻያዎችን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር እኩል እና ምቹ የሥራ ግንኙነቶችን መፍጠር; እና ኢንዱስትሪዎች እንደ ማህበራት ማደራጀት ያሉ ተግባራዊ መዋቅር እንዲመሰርቱ ማበረታታት <br> **ሴ/ማኅ/ሚ** –በሠራተኞችና በአምራቾች መካከል ፍትሀዊ እና ምቹ የሆነ የሥራ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | ግንኙነት ለመፍጠር የሠራተኛ ሕጉን ማሻሻያ ይመራል፡፡<br>**ፍ/ሚ** – ህጉ ከተሻሻለ በኋላ የተሻሻለውን የሠራተኛ ሕግ መገምገም ፣ ማፅደቅ እና መተግበሩን ይቆጣጠራል፡፡ |
| | | (42) ዝቅተኛ የደሞዝ ወለል ደንብን መከለስ፣ እና ደሞዝን በአፈፃፀምና በምርታማነት ላይ በመመርኮዝ መወሰን | ህግ | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** –ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አሁን ያለው የዝቅተኛ ክፍያ መዋቅር በሠራተኞች እና በአምራቾች ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ እና በአፈጻጸም ላይ ከተመሰረቱት የደመወዝ አወሳሰን ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞች ለመለየት ጥናት ያካሂዱ፡፡<br>**ሴ/ማጉ/ሚ** – በጥናቱ ግኝቶች ላይ በመመስረት የዝቅተኛውን የደመወዝ ደንብ ክለሳ እና ማሻሻያ በመምራት ደመወዝ በአፈፃፀም/በምርታማነት ላይ በመመስረት እንደሚከፈል ማረጋገጥ፡፡ |
| | | (43) በንግድ አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸውን | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** –በቢዝነስ አስተዳደር ላይ የአቅም ግንባታ መርሃ ግብር በመንደፍ ከፍተኛ አፈፃፀም ላስመዘገቡ የስትራቴጂክ ምርቶች |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የተመረጡ ስትራቴጂካዊ ምርቶችን ለመደገፍ ፕሮግራም መንደፍ | | | | | አምራቾች ግብዓቶችን በማቅረብ ተወዳዳሪነታቸውን ማሳደግ<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ከሴክተሩ ጋር በተገናኘ እና ከፍተኛ አፈፃፀም ያላቸውን አምራቾች በመለየት እና በመምረጥ በስልጠና አመራር ላይ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን ይደግፋል፡፡ |
| | | (44) የአቅም ክፍተት ምዘና ይካሄዳል፣ እና ለቁልፍ የዘርፍ አመራር ቦታዎች የአቅም ግንባታ መርሃ ግብር ተነድፎ መዘርጋት | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** –በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በተጠሪ ተቋማት ውስጥ ያሉ ቁልፍ የዘርፍ አመራር የአቅም ክፍተት ግምገማ ማካሄድ፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ውስጥ የአመራር ክህሎትን በማጠናከር ላይ በማተኮር ለቁልፍ የዘርፍ አመራር ቦታዎች የአቅም ግንባታ መርሃ ግብር ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ |
| **ቴክኖሎጂ** | ከፍተኛ ካፒታል ስለሚስፈልግ ጊዜውን ያልዋጀ ተክኖሎጂ መጠቀም | (45) የቴክኖሎጂ ማሻሻያ ፈንድ ከልማት አጋሮች ጋር በመግባባት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ጊዜ ያለፈባቸው ለመቀየር የካፒታል ወጪን መጋራት | ፕሮጀክት | | | | **ኢ/ሚ** – ከገንዘብ ሚኒስቴርና ፣ ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከኢንዱስትሪ ማህበራት እና የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂና ዲዛይን ማሻሻያ እቅድን ማቅረብ፡፡<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ኢንዱስትሪዎች እና ቴክኖሎጂዎችን በማሻሻል ረገድ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈጻሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ቴክኖሎጂዎች በመለየት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት<br>**ፋ/ሚ** –ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ፈንድ ለማግኘት ከልማት አጋሮች ጋር መተባበር |
| **ምርምርና ልማት** | ለምርምር ተቋማት ተገቢውን ድጋፍ አለማድረግ | (46) የምርምር ተቋማትን እና ማዕከላትን በተገቢው ላቦራቶሪዎች፣ ቴክኖሎጂ እና መሳሪያዎች ማጠናከር | ፕሮጀክት | | | | **አ/ኢ/ል/ኢ** – የፍላጎት ግምገማ በማካሄድ በተቋሙ እና በእያንዳንዱ የምርምር ማዕከላት ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የድጋፍና የግብዓት መስፈርቶችን የሚለይ ግልፅ ፕሮጀክት ማዘጋጀት<br>**ኢ/ሚ** – ከአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሳይንሳዊ ምርምርና ቴክኖሎጂ ልማትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ለምርምር ተቋማትና ማዕከላት የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ እና አስፈላጊውን ቤተ ሙከራ፣ ቴክኖሎጂ እና መሳሪያ ማሟላት። |
| **ስታንዳርድ** | በቂ ያልሆነ ምርመራ፣ ቁጥጥር፣ የ GMP የምስክር ወረቀት ስርዓት ለአገር ውስጥ በአግሮ- | (47) ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚያቀርቡ አምራቾች ኢ/ስ/ኢ እና ኢ/ተ/ም/ድ (የተስማሚነት) የምግብ ምርመራ/ላቦራቶሪ፣ የምስክር | ፕሮጀክት | | | | **ኢ/ስ/ኢ** እና **ኢ/ተ/ም/ድ** –የፍላጎት ምዘና ማካሄድ እና በየተቋማቱ ያሉ ክፍተቶችን በመለየት የድጋፍና የሀብት መስፈርቶችን የሚለይ ግልጽ ፕሮጀክት ማዘጋጀት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተቀነባበሩ ምግቦች አምራቾች። | ወረቀት እና የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ማጠናከር - ቅድሚያ ለተሰጣቸው ምርት አምራቾች | | | | | **ኢ/ሚ** እና **አ/ኢ/ል/ኢ** – የፍላጎት ዳሰሳውን መሰረት በማድረግ ባለድርሻ አካላትን የሚያስተባብር ፕሮጀክት ነድፎ እና ግብአቶችን በጋራ በማሰባሰብ ኢ/ስ/ኢ እና ኢ/ተ/ም/ድ መደገፍ<br>**ኢ/ም/መ/ባ** – ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች የጤና፣ ደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን ማውጣትና እና ማስፈጸም እና እንዲሁም የደህንነት ፍተሻዎችን እና ኦዲቶችን መቆጣጠር |
| | | (48) በ FDA እና በአምራቾች መካከል ክትትል እና ቁጥጥር ጨምሮ በመልካም የማምረት ልምድ ላይ መደበኛ ቁጥጥር እና ምክክር ለማድረግ ፕሮግራም መንደፍ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ም/መ/ባ** –ፕሮግራሙን መንደፍ እና መተግበር, የፍተሻ ፕሮቶኮሎችን ማዘጋጀት፣ ተቆጣጣሪዎችን ማሰልጠን እና የማምረቻ ተቋማትን መደበኛ ቁጥጥር ማድረግ፤ የስትራቴጂካዊ ሽቀጦችን የመልካም የማምረቻ ልምድ (GMP) ደረጃዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር፣ እና እነዚህን መመዘኛዎች እንዴት እንደሚያከብሩ አምራቾችን ማማከር<br>**ኢ/ስ/ኢ** – መስፈርቶችን በማዘጋጀት እና በማስፈጸም፣ እና ለ FDA እና ለአምራቾች ቴክኒካዊ መመሪያ እና ድጋፍን ይሰጣሉ። |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | | | | | | **ኢ/ሚ እና ን/ቀ/ት/ሚ** –አምራቾች የGMP መስፈርቶችን እንዲያከብሩ እና የማያሟሉ አምራቾች ላይ ቅጣቶችን መተላለፋቸውን ያረጋግጡ<br><br>**ግ/ሚ** –የግብርና ተግባራት የደህንነት እና የጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ እና በ GMP ደረጃዎች ላይ ለገበሬዎች መመሪያ እና ድጋፍ መስጠት። |
| **ፋይናንስ – የስራ ማስኬጃ ካታል** | የሥራ ካፒታል እጥረት/አለመኖር፣ ደካማ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት | (49) ቅድሚያ የሚሰጣቸውና ተኪ ምርት በማምረት ላይ ለተሰማሩ አምራቾች የአምራች ብድር አቅርቦት ኮታ፣ የብድር አከፋፈል እና ክፍያ ድልድል መቆጣጠር | ህግ | | | | **ኢ/ብ/ባ** – ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የተኪ ምርቶችን በማምረት ላይ የተሰማሩ አምራቾችን ለመደገፍ፤ ለሁሉም ንግድ ባንኮች የአምራች ብድር አቅርቦት ኮታ ማዘጋጀትና በበሄራዊ ባንኩ ስር የሚተዳደሩትን የብድር አከፋፈል እና የገንዘብ ተመላሽ መጠን ቁጥጥር እንዲኖር ማስቻል<br><br>**ገ/ሚ** – የብድር አቅርቦት ኮታ መርሃ ግብር ትግበራን ማስተባበር እና ብሄራዊ ባንክ የብድር ክፍያን እና ለአምራቾች የሚከፈልበትን መስፈርት በማዘጋጀት ይደግፋል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| | | | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** – የብድር አቅርቦት ኮታ መርሃ ግብር ትግበራን ማስተባበር እና ብሄራዊ ባንክ የብድር ክፍያን እና ለአምራቾች የሚከፈልበትን መስፈርት በማዘጋጀት ይደግፋል<br><br>**ኢ/ል/ባ እና ንግድ ባነኮች** – የ ብሄራዊ ባንክ መመሪያን በማክበር ለአምራቾች ብድር መስጠትን እና የብድር ፈንዶች ለታለመላቸው ዓላማ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ |
| | | (50) ለአምራቾች እንደ ምርታቸው ሁኔታ የተመደበውን የሥራ ማሰኬጃ ካፒታል መመለሻ፣ የወለድ ምጣኔና ጊዜ ማሰተካከል በተለይም ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የአገር ውስጥ አምራቾች ዝቅተኛውን የወለድ ተመን እንዲሆን ማድረግ | ህግ | | | | | | | | | | **ኢ/ብ/ባ** – አሁን ያለው የብድር እቅድ ተፅእኖን በመገምገም የተሻሻለ የወለድ ተመን ፖሊሲን ከብሔራዊ የገንዘብ ፖሊሲዎች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በመተግበር ለአምራቾች የሚከፈለውን እና የሚከፈልበትን ካፒታል ማስተዳደር<br><br>**ገ/ሚ** – የተሻሻለውን የወለድ ተመን ፖሊሲ አፈፃፀም ማስተባበር እና ብሄራዊ ባንክ ለአምራቾች የወለድ ተመኖችን እና የመመለሻ ጊዜዎችን ለመወሰን መመዘኛዎችን በማዘጋጀት መደገፍ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ –ማ/ኢ/ል/ኢ-** ከአምራቾች/ኢንዱስትሪዎች መረጃን በመሰብሰብ በተፅዕኖ ግምገማው ላይ ድጋፍ በማድረግ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን እና ሸቀጦችን በመለየት ቅድሚያ በመስጠት የወለድ ተመን ክለሳ እንዲደረግ ማስቻል |
| **ፋይናንስ – የውጭ ምንዛሬ** | ግልጽ ያልሆነ የውጭ ምንዛሬ ድልድል መርሃ ግብሮች እና ስርዓቶች፣ ወጥነት የሌላቸው መመሪያዎች፣ከላኪዎች የመነጨ የውጭ ምንዛሬ የሚጠቀሙበት ኮታ | (51) በሁሉም የንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ ድልድልን ለመቆጣጠር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር FXD/77/2021 ተግባራዊ ለማድረግ ግልጽ አሰራርን መዘርጋት፣ ማስፈጸም፣ መቆጣጠር | ፕሮሲጀር | | | | | | | | | | | **ኢ/ብ/ባ** – የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶችን እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ጨምሮ በሁሉም የንግድ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ድልድልን ለመቆጣጠር የአሰራር ሂደቱን መንደፍ እና መተግበር; መመሪያውን ማስፈጸም እና የንግድ ባንኮች የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ማክበራቸውን ማረጋገጥ<br>**ገ/ሚ** – ለብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር እና መመሪያ መስጠት፣ ደጋፉም ከአገራዊ የበጀት ፖሊሲዎች እና ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | | | | | | | **ኢ/ሚ** – የአሰራር ሂደቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መጀመር |
| | | (52) ከራሳቸው ወደ ውጭ ለሚላኩ አምራቾች የተገኘውን የውጭ ምንዛሪ ድልድል መቶኛ ለመጨመር የ20/80 ፖሊሲን ማሻሻል | ህግ | | | | **ኢ/ብ/ባ** – ከአምራቾች ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ መጠን በመቶኛ ለመወሰን መመዘኛዎችን ማሻሻል እና የንግድ ባንኮች ድንጋጌዎችን እንዲያከብሩ ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ |
| **አጋዥ ኢንዱስትሪዎች** | አጋዥ ግብአቶች አለመኖር እና ዝቅተኛ ጥራት (የወረቀት / ካርቶን ማሸጊያ ፣የቀዝቃዛ ሰንሰለት መጓጓዣ); አጋዥ እና አካል ማምረቻ ላይ ኢንቨስትመንት አለደመድረጉ፣ የቴክኖሎጂ እጥረት፣ ክህሎት እና የግብአት አቅርቦት ችግር | 53) አጋዥ ምርቶች ማምረት ላይ የተሰማሩ አዳዲስ ኢንቨስትመንትን መሳብ - ለምሳሌ መለዋወጫዎች፣ ክፍሎች እና ማሸጊያ እቃዎች እንዲሁም እያደገ ያለውን የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እና ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያዎች ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል እሴት በማዘጋጀት የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማስተዋወቅ | ፕሮጀክት | | | | **ኢ/ኢ/ኮ** –ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ዘርፎች የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር የኢንቨስትመንት መስህብ እንዲኖር መምራት<br><br>**ኢ/ሚ** – ከኢ/ኢ/ኮ ጋር በመሆን ለግሉ ሴክተር የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የማመቻቸት ወዘተ ስራዎችን ማመቻቸት<br><br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ለኢ/ኢ/ኮ ለባለሀብቶች የእሴት ፕሮፖዛል ልማት እና ለቴክኖሎጂ ሽግግር በሚያጠኑበት ጊዜ የቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | (54) ለማኑፋክቸሪንግ ሴክተር የእሴት ሰንሰለቶች ለምሳሌ የቀዝቃዛ ሰንሰለት ማጓጓዣ እና ሎጂስቲክስ ሥርዓቶችን ፣ የጨርቃጨርቅ እና ቆዳ መለዋወጫዎችን ፣ ሞልዶችን ፣ ላስቶችን እና ጫማ ሶሎችን ፣ የብረት ማሽጊያዎች | ስትራቴጂ | | | | **ኢ/ሚ -አ/ኢ/ል/ኢ፡-** ከአስፈላጊው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአጋዥ ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂን በማውጣትና በመተግበር፣ ንዑሳን ዘርፎችን በመለየት ቅድሚያ በመስጠት እና ከአምራቾች ጋር በመስራት ለኢንዱስትሪዎች አጋዥ ዕቃዎችን ሀገራዊ ፍላጎት የሚያሟሉ የምርት ዕቅዶችን ማዘጋጀት |
| **የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ** | ውጤታማ ያልሆነ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ፣ ትክክለኛ ስርዓቶች እና የተግባበት መስመሮች አለመኖር፣ የተንዛዛ የጉምሩክ ስራ፣ በዚህ ዙሪያ ያለው የእውቀት እና የክህሎት ክፍተት | (55) ለጉምሩክ ኮሚሽን ባለሙያዎች በአምስቱም ዘርፎች የስልጠና እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስትራቴጂክ እቅድ በማውጣት በኢንዱስትሪዎች የመስክ ጉብኝት በማድረግ ወይም የሴክተር ባለሙያዎችን እንደ ቴክኒክ አማካሪነት በመቅጠር ማብቃት | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ጉ/ኮ** – የኮሚሽኑ ባለሙያዎችን የሥልጠና ፍላጎት መለየት፣ ለባለሙያዎች የሥልጠናና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ የሥልጠናና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ማስተባበር<br><br>**ኢ/ሚ – አ/ኢ/ል/ኢ፡-** ከክልል መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ለአጭር ጊዜ ምክክር የቴክኒክ ባለሙያዎችን በመመደብና ስልጠና በማዘጋጀት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እገዛ ማድረግ |
| | | (56)ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በፌዴራል፣ በክልል እና በከተማ ደረጃ ባሉ የጉምሩክ መሥሪያ ቤቶች | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ-አ/ኢ/ል/ኢ፡-** ከክልል መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የኢ/ጉ/ኮ ሞዴልን መሠረት በማድረግ የአንድ መስኮት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በዘርፉ ልዩ የሆነ እና በቴክኖሎጂ የተደራጀ ባለአንድ መስኮት አገልግሎት ማቋቋም | | | | | አገልግሎት ሥርዓት በመንደፍ ቢሮዎችን በማሰልጠን አገልግሎቶቹን ተግባራዊ ማድረግ |
| | | (57) ለአምራቾች የሚሰጠው አገልግሎት የስራ አፈጻጸም መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማስቻል | ህግ/ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** – ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአምራቾችን ፍላጎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የመንግስትን የስራ አፈጻጸም ለማሻሻል የምክክር መድረክ መፍጠር |
| **ፖሊሲ** | ለብረታ ብረት እና ኬሚካል ንዑስ ዘርፎች የፖሊሲ ወጥነት አለመኖር | (58) ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች እና ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንዑስ ዘርፎች የተተገበሩ ፖሊሲዎችን እና ማበረታቻዎችን የሚመራ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ማዘጋጀት | ስትራቴጂ | | | | **ኢ/ሚ-አ/ኢ/ል/ኢ**– ወቅታዊ የማበረታቻ አወቃቀሮችን በመገምገም ጥልቅ ጥናት በማካሄድ ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች እንዲሁም ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ንኡስ ዘርፎች የሚተገበሩ ፖሊሲዎችንና ማበረታቻዎችን የሚመራ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ማዘጋጀት<br>**ኢ/ሚ** – የስትራቴጂውን ትግበራ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር ማስተባበር<br>**ገ/ሚ**–ለሁለቱም ሴክተሮች ወቅታዊ እና ተፈላጊ የማበረታቻ አወቃቀሮችን በተመለከተ ግብአቶችን እና ግንዛቤዎችን |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | መስጠት እና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂውን ተግባራዊ ማድረግ<br>**ኢ/ኢ/ኮ** – አሁን ባለው የማበረታቻ መዋቅሮች ላይ ግብአት መስጠት እና በባለሀብቶች ተሳትፎ ላይ ተመስርተው ወደፊት እንዴት መሄድ እንዳለበት መንገዶችን መጠቆም |
| **መሰረተ ልማት** | ዝቅተኛ የኤሌትሪክ ማከፋፈያ አቅም፣ የኤሌትሪክ ኃይል አጠቃቀም ውጤታማ አለመሆን፣ አሮጌ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመር፣ ለኢንዱስትሪው የተለየ የኤሌክትሪክ መስመር አለመኖር፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት አስተዳደር ደካማነት | 59) ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች የሚያመርቱ የተመረጡ አምራቾች የምርት ወጪን ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ዋጋዎችን ማሻሻል | ህግ | | | | **ኢ/ሚ-አ/ኢ/ል/ኢ**– ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች የሚያመርቱ አምራቾችን በመለየት የማኑፋክቸሪንግ ወጪዎችን ለመቀነስና ተወዳዳሪ የታሪፍ ተመንን ለመተገበር ለኢ/ኤ/አ ደጋፍ መሰጠት<br>**ዉ/ኢ/ሚ** – የታሪፍ ተመኖችን አተገባበር እና ተጽዕኖውን መቆጣጠር<br>**ኢ/ኤ/አ** – ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ኢንዱስትሪዎች የምርት ወጪዎችን ለመቀነስ ተወዳዳሪ የኤሌክትሪክ ታሪፍ ዋጋዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር |
| | | 60) ለከባድ ኢንዱስትሪዎች (የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብአት አምራቾች፣ የብረታ ብረትና | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ**– ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በማስተባበር መርሃ ግብሩን ማስጀመር፣ በተሰሩት የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ኢንጂነሪንግ አምራቾች) እና በ2ቱም ሴክተሮች ውስጥ ስትራቴጂያዊ ምርቶችን ለሚያነርቱ አምራቾች የብቻ እና ያልተቆራረጠ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ማቋቋም | | | | | | | | | | | | መስመሮች ተጠቃሚ የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎችንና ስትራቴጂክ ምርቶችን ለሚያመርቱ አመራቾችን በመለየት ለፕሮግራሙ ትግበራ ድጋፍ ማድረግ<br>**ው/ኢ/ሚ** -ለከባድ ኢንዱስትሪዎች የተሰጡ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን ማቋቋም እና መስመሮቹ እንደ አስፈላጊነቱ እንዲጠበቁ እና እንዲሻሻሉ የኢ/ኤ/ኃ ን መደገፍ<br>**ኢ/ኤ/ኃ**– የተለዩ እና ያልተቆራረጠ የሃይል ማስተላለፊያ መስመር መገንባት እና ማሰራት እንዲሁም የማስተላለፊያ መስመሮቹ አስተማማኝ እና ቀልጣፋ መሆናቸውን ማረጋገጥ |
| | | (61) ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ የአገር ውስጥ አምራቾች የተቀናጀ እና አስተማማኝ መሠረተ ልማት ማቅረብ | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** –ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ የማምረቻ ክላስተሮችን በመለየት የተቀናጀ የመሰረተ ልማት እቅድ በማውጣትና በመተግበር በእቅድ እና ትግበራ ደረጃዎች ሁሉንም አስፈላጊ ባለድርሻ አካላት በማስተባበር መተግበር<br>**አ/ኢ/ል/ኢ** – ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ክላስተሮች በመለየት እና የመሠረተ ልማት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | አቅርቦት ዕቅድን በማዘጋጀት ለኢ/ሚ፣ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት |
| | | (62) ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች ወይም የኢንዱስትሪ ኮሪደሮች የዲጂታል መሠረተ ልማት አቅርቦት ከኢትዮቴል ጋር በመተባበር ለሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንቶች ማቅረብ | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ** – ጥራት ያለው ዲጂታል መሠረተ ልማት እና አገልግሎት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ባለሀብቶች ለማቅረብ ከኢ/ቴ/ሚ እና እና ከኢትዮቴሌኮም ጋር ትብብር መፍጠር፣ በዲጂታል መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶች አቅርቦት ተጠቃሚ የሚሆኑ አምራቾችን ወይም የኢንዱስትሪ ኮሪደሮችን መለየት<br><br>**ኢ/ቴ/ሚ** – ለዲጂታል መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶች አስተዳደር ፖሊሲዎች እና መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና የደጋፉን ትግበራውን ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበረ መስራት<br><br>**ኢትዮቴሌኮም**- የዲጂታል አገልግሎቱን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች ወይም የኢንዱስትሪ ኮሪደሮች ማድረስ |
| **የአምራች ማህበራት** | በቂ ያልሆነ የማህበራት መዋቅር፣ የ ካፒታል፣ የቴክሊክ፣ በጋራ | 63) አሁን ያለውን የማኑፋክቸሪንግ ማህበር በአሰራር ስርዓት፣ ከአምራቾች እና ተቋማት ጋር | ህግ/ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢ** – ሁሉንም ማኅበራት በሁሉም ንዑስ ዘርፎች የሚመራ ከፍተኛ ተቋም ወይም ኮንፌዴሬሽን |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | |
| | የመስራት እና የአስተዳደር ውስንነት | ያለውን ግንኙነት እና ቴክኒካዊ እና የአስተዳደር ችሎታዎችን ማጠናከር፣ የአምራች ኮን/ፌዴሬሽን በማቋቋም ድርጅታዊ ተሰሚነቱን ማጠንከር | | | | | ለመመሥረት የሚያስችል ሁኔታ /መደላድል መፍጠር<br>**የዘርፍ ማኅበራት፡-የ**ሚመለከታቸው ንዑስ ዘርፎች ሁሉ አዲሱን ከፍተኛ አካል ለማቋቋም ድጋፍ መስጠት/መሳተፍ |
| **ግብር እና ማበረታቻዎች** | ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ አዋጅና መመሪያ ሲወጣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ውስንነት | 64) ቅድሚያ በተሰጣቸው ምርቶች ላይ በመመስረት፣ በሚመረቱ ምርቶች ላይ የተጣሉትን የግብር አይነቶችን መከለስ ፣ ለሁሉም አምራቾች ድርብ የታክስ ቦታዎችን ማስወገድ (የጥሬ ዕቃ ግብር፣ የማምረት እና የተመረተ ምርት ወዘተ ግብሮች) | ህግ | | | | **ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢ፡-** ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቅድሚያ በሚሰጡ ምርቶች ላይ ያሉትን ታክሶች እንዲገመገም ያደርጋል/ያስተባብራል<br>**ፋ/ሚ** – ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች ወቅታዊ እና የሚፈለጉትን የታክስ አወቃቀሮችን በተመለከተ ግብአቶችን እና ግንዛቤዎችን መስጠት እና የተሻሻለው የግብር አወጣጥ እቅድ አፈፃፀምን ይደግፋል<br>**ገ/ሚ** እና **ኢ/ጉ/ኮ** – ወቅታዊ የግብር አወቃቀሮችን በሚገመገምበት ወቅት አስፈላጊ መረጃዎችን እና ግንዛቤዎችን በመስጠት የተሻሻለውን የግብር አደረጃጀት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ምርቶች ላይ እንዲተገበሩ ያመቻቻል |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| | | (65) 5ቱንም ንኡስ ዘርፎች የሚወክል ግብር እና የዋጋ አወጣጥ አማካሪ ቡድኖችን ማቋቋም | ፕሮግራም | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ** – የመንግስት አካላትን በታክስ እና የዋጋ አወጣጥ ህጎች ላይ የማማከር ሃላፊነት ያለው ከፋ/ሚ፣ ከገ/ሚ፣ ከኢ/ጉ/ኮ፣ ከን/ቀ/ት/ሚ፣ ከኢ/ኢ/ኮ፣ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማህበራት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በየሩብ/ሁለት ጊዜ የሚሰበሰቡ አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም |
| | | (66) በ5ቱ ንኡስ ሴክተሮች ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ኬሚካሎችን እና ሌሎች ግብአቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች በአፈጻጸም ላይ የተመሰረተ ማበረታቻ እና የገንዘብ ድጋፍ ማዳበር | ህግ/ፕሮጀክት | | | | | | | | | | | **ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢ** – የማህበራትን ፍላጎቶች በመለየት ስርዓቶቻቸውን ፣ ግንኙነታቸውን እና ከአምራቾች እና ተቋማት ጋር ቅንጅት እና የቴክኒክ እና የአስተዳደር አቅሞችን ለማጠናከር ድጋፍ መስጠት<br><br>**ኢ/ሚ** – የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪውን ጥቅም ለማስተዋወቅ የአምራች ኮንፌዴሬሽን ማቋቋሚያ ለመወያየት ከማህበር ተወካዮች ጋር የውይይት መድረክ መፍጠር እና በስምምነት ላይ ተመስርቶ እንዲቋቋም ቅስቀሳ ማድረግ<br><br>**ኢ/ቻ/ኮ/** – በፕሮጀክቱ ግምገማ እና የኮን/ፌዴሬሽን ማቋቋሚያ ምዕራፍ ወቅት |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | በሚኒስቴሩ እና በአባላት ማህበር መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማመቻቸት |
| | | 67) ለሚያበረታቱ አምራቾች በተቀናጀ ኦዲት የሚመራ ግልጽ ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | ፕሮሲጀር | | | | **ኢ/ሚ፡-** ማበረታቻ የሚደረግላቸው አምራቾችን መለየት እና መደበኛ የኦዲት ሂደት ማስጀመር<br><br>**ገ/ሚ እና ኢ/ጉ/ኮ** – አሁን ባለው የኦዲት ሂደት ውስጥ ያለውን ክፍተት መገምገም (ለመዘግየት፣ ግልጽነት የጎደለው የታክስ እና ታክስ ቅንጅት መንስኤዎች)፣ የኦዲት ስርዓቱን ማሳደግ፤ ፈጣን፣ መደበኛ፣ ግልጽ እና የተቀናጀ የኦዲት ሂደት ማቅረብ ፡፡ ማበረታቻ የተደረገላቸው አምራቾች ለሚያቀረቡት ቅሬታም በመረጃ ላይ በመመርኮዝ የታክስ/የግብር ግዴታቸውን እንዲወጡ ማድረግ |
| | | (68) ለየትኛዎቹ እቃዎች ምን ማበረታቻዎች እንደተዘጋጁ እና እነማን/የትኞቹ አካላት እነዛን ምርቶች እንደሚያበረታቱ በቀላሉ ለመለየት በሁሉም የማበረታቻ ሰጭ አካላት መካከል መናበብ መፍጠር | ፕሮሲጀር | | | | **ፋ/ሚ**– ማበረታቻዎችን በሁሉም የመንግስት አካላት ማቀናጀት እና ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን በማውጣት በቦርዱ ውስጥ ባሉ የማበረታቻ አቅርቦቶች ውስጥ ወጥነት ያለው እና ግልጽነት እንዲኖረው ማድረግ |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* የአጭር *(1 – 3)* | የመካከለኛ *(4 – 7)* | የረጅም *(8 – 10)* | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | (የማበረታቻ ሰጪ አካላትን ማንዴት ግልጽ ማድረግ) | | | | | **ኢ/ሚ** – ማበረታቻ የሚሰጣቸውን ምርቶች መለየት እና ከመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የማበረታቻ አቅርቦቶችን በማስተባበር ለገ/ሚ ድጋፍ ማድረግ |
| | | (69) በ5ቱም ንዑስ ዘርፎች አሴት ሰንሰለቱ ውስጥ (ከጥሬ ዕቃ እስከ ግብይት) ቅደሚያ ለሚሰጣቸው የተኪ-ምርት አምራቾች ከዚህ ቀደም የነበሩ የኤክሰፖርት ማበረታቻዎችን መገምገም እና ለተኪ ምርት አምራቾች እንዲሆኑ ማሻሻል፤ ማበረታቻዎቹ በአምራቾች ላይ ያላቸውን ተፅእኖ መገምገም | ፕሮግራም | | | | **ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢ** - አሁን ያለውን የኤክስፖርት ማበረታቻዎች ተጽኗቸውን በመገምገም ቅድሚያ ላላቸው ተኪ ምርቶችን ትምህርት ወሰዶ ለተኪ ምርቶች ማበረታቻነት ዲዛይን መነሻ መድረግ<br>**ፋ/ሚ** - ማበረታቻዎቹ በአምራቾች ላይ ያሰደሩትን ተፅዕኖ ለመገምገም የግምገማ ዘዴን በማዘጋጀት ኢ/ሚ እና አ/ኢ/ል/ኢን መደገፍ<br>**ኢ/ኢ/ኮ** :- የአሁኑን የማበረታቻ መርሃ ግብር እና የቀደሙትን ማበረታቻዎች ተፅእኖ ለመገምገም ባለሀብቶች እና አምራቾች በቅንጅት ኢ/ሚን እንዲደግፉ ማድረግ |
| **ኮንትሮባንድ** | የኮንትሮባንድ መሰፋፋት | (70) ኃላፊነት የሚሰማው ኮሚሽን በማቋቋም በተለያዩ ፈጻሚ አካላት ተበታትነው እተፈፀሙ ያሉ የፀረ- | ህግ | | | | **ን/ቀ/ት/ሚ** - ፀረ-ውድድር ድርጊቶችን ለመቆጣጠር ኃላፊነት ያለው ኮሚሽን ማቋቋም እና የተለያዩ አስፈፃሚ አካላትን ሚናዎች ማስተባበር |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ (ዓመት) | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር (1 – 3) | የመካከለኛ (4 – 7) | የረጅም (8 – 10) | |
| | | ውድድር የንግድ ቁጥጥር ሥራዎችን በማቀናጀት ፀረ ውድድር አሠራሮችን የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለበት አዋጅ ቁጥር 329/2003 በሥራ ላይ ማዋል፤ አንደ አይነት ስራዎችን በተደራራቢነት በአንድ ላይ የሚፈፅሙ ተቋማትን ማስቆም | | | | | **ፍ/ሚ** - ኮሚሽኑ ሲቋቋም እና አዋጅ ቁጥር 329/2003 ሲተገበር የህግ ድጋፍ እና መመሪያ ይሰጣል<br>**ገ/ሚ እና ኢ/ጉ/ኮ** - ኮሚሽኑን ሲማቋቋም በወጣው ደንብ መሰረት የደንቡ አፈፃፀም ውጤታማ መሆኑን እና የንግድ ስራ ያላቸው ሁሉ ትክክለኛ ሂደቶች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል |
| | | (71) በሕገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በቴክኖሎጂ እንዳይሰሩ ወይም ጥቅም አንዳይሰጡ ለመከላከል (ለአንዳንድ ሸቀጦች ለምሳሌ ሞባይል ስልኮች) ሥርዓት መተግበር | ህግ | | | | **ን/ቀ/ት/ሚ**– በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በቴክኖሎጂ እንዳይሰሩ ወይም ጥቅም አንዳይሰጡ ለማድረግ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከሸቀጦች ማስመጣት ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን እና ደንቦችን ማውጣት<br>**ኢ/ጉ/ኮ** – ህገ-ወጥ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትን በተመለከተ ፖሊሲዎችን እና ደንቦችን ማስከበር እና ስርዓቱን ለመተግበር ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር መስራት<br>**ኢ/ቴሌኮም** በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ የቴክኖሎጂ ምርቶችን |

| ዋና ዋና ማነቆዎች | መነሻ ምክንያቶች | መፍትሄዎች | መፍትሄው የሚሰጥበት መንገድ | የትግበራ ጊዜ *(ዓመት)* | | | | | | | | | | ፈፃሚ አካላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የአጭር *(1 – 3)* | | | የመካከለኛ *(4 – 7)* | | | | የረጅም *(8 – 10)* | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | እንዳይሰሩ ለማድረግ ወይም ለመከላከል የቴክኖሎጂ ስርዓቱን ተግባራዊ ማድረግ |